ምዕራፍ አንድ

1. የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ትርጉም (ምንነት) እና አስፈላጊነት

1.1 ቤተ ክርስቲያን

ቤተክርስቲያን ሦስት ትርጉም ያለው በዘርፍና በባለቤትነት የተቀመጠ ስም ነው። አንደኛው ትርጉም የክርስቲያን ቤት፣ የክርስቲያን መሰብሰቢያ፣ የክርስቲያን መገናኛ ማለት ነው። ይህም ማለት ክርስቲያኖች በአንድነት በመሰብሰብ የሚጸልዩበት፣ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣ የሚሰግዱበት፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቦታና የጸሎት ቤት ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ቤተ ጸሎት ናት። (ኢሳ 56፣7፣ ኤር 7፣ 10-11፣ ማቴ 21፣13፣ ማር 1፣17፣ ሉቃ 19፣46)

ቤተ ክርስቲያን ሕፃን፣ ሽማግሌ፣ ድሀ፣ ሀብታም፣ ወንድ፣ ሴት፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ በመባባል ሳንለያይ በአንዲት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነት ያለን ምእመናን የምንሰበሰብበት ቃለ እግዚአብሔር የምንማርበት ሥርዓተ አምልኮአችንን የምንፈጽምበት፣ ስጋ ወደሙ የሚፈተትበት ቅዱስ ቦታ ነው። ቤተክርስቲያን ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቢሰበሰቡ በዚያ ቦታ እግዚአብሔር አብሮ ሊገኝ ቃል ኪዳን የተሰጠ ቦታ ነው። (ማቴ 18፣20) የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የራሳቸውን የጸሎት ቤት በተወሰነ ቦታ አላደረጉም፣ የተለያየ ሕንፃ አላሠሩም ነበር፤ ነገር ግን ወደ አይሁድ ቤተ መቅደስ በመሄድ ይጸልዩ ነበር፤ እንዲሁም በግል የክርስቲያን ቤቶች እየተገኙ በተለያዩ ክፍሎች እየተሰበሰቡ ይጸልዩ፣ ቅዱስ ቁርባንንም ያዘጋጁ፣ ማዕድንም ይባርኩ ነበር። ክርስትና እየተስፋፋና እየታወቀ ከሄደ በኋላ ቤተክርስቲያንም በፊልጵስዮስ በመጀመሪያ ጊዜ በጌታችን ፈቃድ ከተሠራ በኋላ ክርስቲያኖች ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉት በቤተክርስቲያን ብቻ መሆን ጀመረ። ከዚያ በፊት የነበሩ መቅደስና ምኩራብም አገልግሎታቸውን ለቤተክርስቲያን አስረክበ ዳን 9፣ 26-27 ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራው ክርስቲያኖች በጎበረት ሊጸልዩበት ሥጋውንና ደሙን ሊቀበሉት በአጠቃላይ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሊጠቀሙበት ነው። (1 ቆሮ 15፥9፣ 12፥27)

በቅዱሳት መጻሕፍት ሕንፃ ቤተ መቅደስ የቅዱስ ስሙ መጠሪያ ስለ መሆኑ ተገልጾል ‹‹ጸሎትህን ሰምቻለሁ ይህንም ሥፍራ ለራሴ ለመስዋዕት ቤት መርጫለሁ። ... አሁንም ስሜ ለዘለዓለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህንን ቤት መርጫለሁ›› እንዲል 2 ዜና መዋ 7፥15

ሁለተኛው ትርጉም የክርስቲያን ወገን፣ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሚጠራበት ስም ነው። ‹‹ቤተ እሥራኤል፣ ቤተ ያዕቆብ፣ ቤተ አሮን›› ሲል የእሥራኤል ወገን፣ የያዕቆብ ወገን፣ የአሮን ወገን ማለት ነውና። (መዝ 117፥3፣ 113፥1፣ ማቴ 16፥18፣ ማቴ 18፥17፣ የሐዋ 18፥22፣ የሐዋ 20፣28)

በሦስተኛ ደረጃም ቤተክርስቲያን ሲል የሚወክለው ምእመናንን ነው። ክርስቲያኖች የክርስቶስ ማደሪያዎች ስለሆኑ ክርስቲያን የሚለው ቃል ከክርስቶስ የተገኘ ስለሆነ ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ማደሪያ የሆኑ ክርስቲያኖች (የክርስቲያኖችን ሰውነት) የሚያመለክት ነው። ብርሃነ ዓለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ (ቤተ መቅደስ) እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡. ‹‹የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን›› /1ኛ ቆሮ 3፥16/፣ ‹‹ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን›› 1ኛ ቆሮ

6፥19። ስለዚህ የአንድ ምዕመን ሰውነት የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነ እያንዳንዱ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ይባላል። ጌታችን ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ›› እንዳለ የአማንያን ሰውነት የክርስቶስ ቤት ነው።

1.2 ሥርዓት

ሥርዓት ‹‹ሠርዐ›› ሠራ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ስም ነው። ትርጉሙም ሕግ፣ ደንብ፣ አሠራር፣ መርሐ ግብር ማለት ነው።

ስለዚህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ወይም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ስንል የቤተ ክርስቲያን ሕግ፣ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና የቤተ ክርስቲያን የአሠራር መርሐ ግብር ወይንም ደንብ ማለታችን ነው።

1.3 ሥርዓት ለምን ያስፈልጋል?

1. ማንኛውንም ሥራ ወጥና ዘላቂ በሆነ መልኩ ለመስራት አንድ ሥራ ከየት ተጀምሮ ወዴት እንደሚሄድ ወጥ የሆነ አካሄድ (ሥርዓት) ከሌለው አሠራሩ የተዘበራረቀ ይሆንና ፍጻሜው አያምርም እግዚአብሔር እንኳ ዓለሙን የፈጠረውን የሚያስተዳድረው በሥርዓት ነው። መዝ 103። ስለሆነም በቤተክርስቲያንም የሚፈጸሙ አገልግሎቶች ሁሉ ወጥና አንድ ዓይነት በሆነ ሁኔታ እንዲፈጸሙ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል ‹‹ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን›› እንደተባለ። 1ኛ ቆሮ 14፥40
2. አንድ ሀሳብና አንድ ልብ ለመሆን አንድ ዓይነት ሥርዓት ያስፈልጋል።

   አንድ ማኅበር በአንድ ዓይነት ሥርዓት ካልተዳደረና ካልኖረ እርስ በእርሷ እንደምትለያይ መንግሥት መፍረሱ አይቀርም። ማኅበርን በአንድነት ከሚያኖሩት አንዱ ከዓላማ ባሻገር ወጥ ሥርዓት ነው። ያለ አንድ ዓይነት ሥርዓት አንዱ ሲጀምር አንዱ የሚጨርስ፣ አንዱ ሲዘምር ሌላው የሚያስተምር ከሆነ መለያየትን ያመጣል። ስለሆነም በማኅበር ምእመናን ሐዋርያው እንደ ተናገረ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ አንድ ዓይነት ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋል። ብዙ ስንሆን አንድ ልብና አንድ ሀሳብ የሚያደርገን ሥርዓት ነውና ኤፌ 4፥3፣ የሐዋ 4፥32፣ ሮሜ 15፥5-6
3. የሃይማኖት ምሥጢራትን ለመፈጸም፣ ሥርዓት የሃይማኖት መገለጫ ነው። ጥምቀት፣ ቁርባን፣ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት ወዘተ በማመን ብቻ የሚያበቁ ሳይሆን የአፈጻጸምና አተገባበር መንገድ (ሥርዓት) ያስፈልጋቸዋል የእነዚህ ሁሉ ዝርዝር አፈጻጸም በሥርዓት ውስጥ ይካተታል። ሥርዓት በመሠረተ እምነት (ዶግማ) የምናምናቸውን በተግባር የምንገልጽበትና ገቢራው የምናደርግበት መንገድ ስለሆነ ሥርዓቱ ሲሠራና ሲፈጸም። ሃይማኖታዊ አንድምታና ነጸብራቅ ይኖረዋል።

1.4 ሥርዓተ ቤተክርስቲያን መማር ለምን ይጠቅማል?

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በሚገባ የተማረና ያወቀ ክርስቲያን

- የቤተክርስቲያንን ንዋያተ ቅዱሳት ከሌሎች ይለያል፣
- ለንዋያተ ቅዱሳት የሚገባቸውን ክብር ይሰጣል፣
- የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅዱሳት ትውፊት ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚገባውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ያስችለዋል።

በአጠቃላይ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የተማረ ሰው በቤተ ክርስቲያን ያለውን መብትና ግዴታ በማወቅ ግዴታውን ይፈጽማል፤ መብቱንም ይጠቀምበታል።

1.5 ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የምንለው ምኑን ነው?

ከላይ ቤተክርስቲያን የምንለው ሕንፃውን፣ የክርስቲያኖች አንድነት (ጉባኤ) እንዲሁም የምእመኑን ሰውነት እንደሆነ ተመልክተናል። ስለዚህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የምንለውም በሦስቱም ላይ የተሠራውን ሥርዓት እንደሆነ ማስተዋል ይገባል።

ቤተክርስቲያን ሕንፃው ነው ካልን ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ስንል ለሕንፃውም ሥርዓት ያስፈልገዋል ማለታችን እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህንም ማስፈጸም የሚችለው ግን ሰው ነው። ቤተክርስቲያን ግለሰቡ (የምእመኑ ሰውነት) ነው ብለን እስከ ተማማርን ድረስም ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የምንለው የምእመኑን ሥርዓት የተከተለ ሕይወት ማለት ነው ቤተክርስቲያን የምእመናን አንድነት ጉባኤ ነው ስላልንም ሥርዓተ ቤተክርስቲያንም በምእመናን ጸንታ የምትኖርበት ያለመለያየት አንዲት መሆኗ የሚታወቅበት አንድ መንገድ ማለታችን ነው።

ምዕራፍ ሁለት

2. የሥርዓተ ቤተክርስቲያን ምንጮች (መሠረቶች)

ምንጭ ማለት ውኃ በመሬት ውስጥ ለውስጥ ሔዶ ከተራራ ወይንም ከኮረብታ ወይንም ከጉባ መሬት ዝቅ ካለ ረባዳ መሬት ላይ ሲደርስ ከመሬት ውስጥ ወደ ውጭ ወጥቶ የሚፈስ ውኃ ነው። ከምንጭ ውኃ ወንዝ ይፈጠራል፤ ወንዝም እያደገ ሲሄድ ሆኖ ወደ ባሕር ይገባል።

እንዲሁም በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ምንጮች የተባሉት መጻሕፍት ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የተጻፈባቸውና ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን ትምህርትም መነሻዎች ሆነው ስለሚያገለግሉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መጻሕፍት ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን በምንጭነት ወይም በመነሻነት የሚያገለግሉ ናቸው።

2.1 መጽሐፍ ቅዱስ

ለማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት መሠረታዊ ምንጭና ቀዳማዊ ተጠቃሽ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለሆነም ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘና የተወሰደ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሥርዓቶችን እናገኛለን ከብሉይ ኪዳን እንኳን ብንጀምር እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ላይ እንዲወጡ ሲፈቅድ ለእነርሱ ከተሰጡት ሥርዓቶች መካከል የፋሲካውን የበግ ሥርዓት ማስታወስ ይቻላል። እስራኤል በጉን ካረዱ በኋላ ደሙን በበራቸው ጉበን (መቃን) ላይ እንዲቀቡ የታዘዙት ቀሳፊው መልዓክ እስራኤልን ከግብፁውያን መለየት ስለማይችል ወይንም ወይንም እግዚአብሔር ሌላ መንገድ ማዘጋጀት ስለማይችል አይደለም። መዳናቸው ከእግዚአብሔር ቢሆንም የሚፈጸመውን ጸጋውም የሚገኘው ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ሥርዓት መሆኑን እንዲያውቁ ነው።

እግዚአብሔር ከግብፅም ካወጣቸው በኋላ አርባ ዓመታት ሙሉ ከሰማይ የሚያወርድላቸውን መና በአፍ እየሰፈረ ይመግባቸው የነበረ መናው አንሶት ወይንም ሰስቶለት ሳይሆን በሥርዓተ መኖርን፣ መሠራት መቀጣትን እንዲለምዱ ነው።

ወደ ደብተራ ኦሪትም ከመሸጋገሩ በፊት በደብረ ሲና ሥርዓትን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል። ወደ ተራራውም ለመውጣት የሦስት ቀን የመንጻት ዝግጅት እንዲያደርጉ፣ ከወጡም በኋላ እስከ ተራራው ግርጌ (እግረ ደብር) እንዲደርሱ እንጂ ተራራው ላይ እንዲወጡ አልተፈቀደላቸውም። በዚህ ካለማመዳቸው በኋላ ሰማያዊውን ሥርዓት በድንኳን እንዲፈጽሙ አዘዛቸው። ሙሴንም በሰማይ ካየው በቀር በራሱ ሀሳብ እንዲሰራ አስጠነቀቀው ዕብ 8፥5፣ ዘጸ 25፥40 ከዚህ በኋላም የመንጻቱን፣ የመሥዋዕቱን፣ የአመጋገቡን ሌላውንም ሁሉ ሥርዓተ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረ፤ ከዚያ በኋላ ለኢያሱ ከዚህ በኋላ የተነሡት ነቢያት ሁሉ በየጊዜያቸው ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ፈጸሙ፤ አስፈጸሙም።

በሐዲስ ኪዳንም ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቤተ መቅደስን በመዋዕለ ሥጋዊው ከፈጸመ በኋላ አዲሲቷን ኪዳን ሲመሠርትም በደም እንደመረቃት ሁሉ በሥርዓት አጽንቷታል። ማቴ 5፥17፣ ዕብ 9፥18

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ያስተማረው ከመሞቱና ከመነሣቱ በፊትም በኋላም ነው። በፊት ካስተማረው ውስጥ ከፊሉን በወንጌላትና በሐዋርያት መልእክታት ልናገኘው እንችላለን። ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ያለውን ደግሞ በስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የሥርዓተ መጻሕፍት ይልቁንም ደግሞ በመጻሕፍተ ኪዳን እናገኘዋለን። ከመሞቱ በፊት ከሠራቸው ሥርዓቶች መካከልም የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው።

ጌታችን በቤተ አልአዛር ሥርዓተ ቁርባንን በጌቴ ሴማኒ ሥርዓተ ጸሎትንና ስግደትን፣ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 6 እንደተጻፈውም በተራራው ስብከት ላይ የጸሎትን የምጽዋትንና የጾምን አፈጻጸም (ሥርዓት) ሠርቶአል። እንዲሁም ሐዋርያትን የምንግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፣ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፣ ግን የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል እንዳለ በእነርሱ ባደረ መንፈስ ቅዱስ እነርሱም ብዙ ሥርዓቶችን ሠርተዋል። ጌታችን ከሠራቸው ሥርዓቶች የቀጠሉና ሌሎች ተወራራሽና ተዛማጅ የሆኑ ሥርዓቶች ሠርተዋል። ከእነዚህም ለአብነት፡-

- በጸሎት ጊዜ ለወንዶችና ለሴቶች ምን ማድረግ እንዲገባ (1ኛ ቆሮ 11)
- ስለ ድንግልናና ጋብቻ ሁኔታ (1ኛ ቆሮ 7)
- በማኅበር (በጉባኤ) ጊዜ ምን መደረግ እንዳለበት (1ኛ ቆሮ 14፥26 እስከ ፍጻሜ)
- ስለ አዛዥና ታዛዥ ኤፌ 6፥5
- ስለ ዲቁናና ቅስና አhDhDም 1ኛ ጢሞ 3፥1-11
- ስለ ባልና ሚስት 1ኛ ጴጥ 3፥1-7
- ስለ አለባበስ 1ኛ ጴጥ 3፥1-6
- የቤተ እግዚአብሔር ሥራ ቤተ ክርስቲያን ከተሠራ በኋላ በሜሮን እንደሚከበር (ዘፍ 28፥18)
- ለቤተ እግዚአብሔር አሥራት ማውጣት እንዲገባ (ዘፍ 28፥ 20-22፤ 14፣20)
- ሰንበትን ማክበር በሥርዓት እንዴት እንደሚፈጸም (ዘጸ 16፥29፣ ዘጸ 20፥10፣ የሐዋ 1፥12፣ ዘጸ 34፥21፥ ነህ 13፥22)
- በጻድቃን በሰማዕታት ስም ቤተ ክርስቲያን የማነጽን ሥርዓት ያሳያናል (ኢሳ 56፥4)

- ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲበሉ ጌታ መደንገጉን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጽፏል። (ማቴ 10፣11፣ 1ኛ ቆሮ 9፥14)
- ስለ ሲኖዶስ (በጉባኤ ቤተክርስቲያን) ይናገራል (የሐዋ 15፡6-29)
- ስለ ሥርዓተ ጋብቻ በ1ኛ ቆሮ 7፥10 (ማቴ 19፥1-12)
- ስለ ክህነት አሰጣጥ (ዮሐ 20፥22 ፤ ማቴ 28፥20፣ የሐዋ ሥ. 9፥12፤ 1፥15-26፤ 6፥1-7፤ ማቴ 16፥17-19፣ የሐዋ ሥራ 9፥12፤ዮሐ 21፥ 15-17)

በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተገለፀ ሥርዓት የለም። ይሁን እንጂ ሁሉም ሥርዓት አልቋል ማለት አይቻልም።

2.2 <u>የሲኖዶስ (የቅዱሳን አባቶች ጉባኤዎች) ውሳኔዎች</u>

ሲኖዶስ ማለት ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጓሜውም ስብሰባ ወይም ጉባኤ ማለት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትንና በእነርሱ እግር የሚተኩትን አባቶች እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ብሎ በማይታበል ቃሉ በሰጠው ተስፋ መሰረት ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ቅዱሳን አባቶችም ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር ነበሩና የተለያዩ ሥርዓቶችን መሥራት ይችላሉ፤ ሠርተዋልም ማቴ 28፥20 የሥርዓት ዋና ዓላማ ቤተ ክርስቲያን በሰላም እንድትገዝ ማድረግ ስለሆነ በየጊዜው ለሚነሡ የተለያዩ ጉዳዮችና ችግሮች እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሲኖዶስ ውሳኔዎችን ይወስናሉ፤ ይደነግጋሉ። ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ እንዳለ 1ኛ ቆሮ 11፥34 ምክንያቱም በእርሱ አድሮ የሚሠራና የሚናገር ክርስቶስ ነውና።(1ኛ ቆሮ 13፥2-3)

በዚህም መሠረት የአባቶቻችን የሐዋርያትን የሥርዓት መጻሕፍት እንደሚከተለው በመጠኑ እንቃኛቸዋለን።

2.3 <u>የሐዋርያት ሲኖዶሶች</u>

ሐዋርያት ሲኖዶሶች ተብለው የሚጠሩት ሦስት ናቸው። እነዚህም፦

- ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ (ዓይን)
- ትእዛዝ ሲኖዶስ (ረሰጠአ)
- ግጽው ሲኖዶስ (ረሰጠጅ)
- አብጥሊስ ሲኖዶስ (ረሰጣ ወይም ረሰጠአ)
- ዲዲስቅልያ
- ቀሌምንጦስ ናቸው።

ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት ለሐዋርያት ያስተማራቸውን ሁለቱን ኪዳናት (መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ እና መጽሐፈ ኪዳን ካልዕን) ከጨመርን ደግሞ ስምንት ይሆናሉ። ብዙ ጊዜ ግን ሲኖዶስ እየተባሉ የሚጠሩት የመጀመሪያዎቹ አራቱ ብቻ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት የቤተክርስቲያናችን የሥርዓት ምንጮች ናቸው።

ሦስቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስ እጅግ ብዙ አንቀጾችን የያዙ ናቸው

ትእዛዝ ሲኖዶስ - 72 አንቀጾች

ግጽው ሲኖዶስ - 57 አንቀጾች

አብጥሊስ ሲኖዶስ - 82 አንቀጾች

<u>ሥርዓተ ጽዮን (ዓይን)</u>

ቀኖናት ሐዋርያዉያት ከተባሉት ቀኖናዎች መካከል የመጀመሪውን ክፍል ይዘው ከሚገኙ ቀኖናተ ሐዋርያት ወይም ትምህርተ ሐዋርያት አንዱ ሥርዓተ ጽዮን ነው።

ቀኖናተ ሐዋርያት ከክርስቶስ ዕርገትና ርደተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ወደ ዓለም ከመበተናቸው በፊት በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠሩአቸውና የደነገጓቸው ቀኖናት ናቸው። "ሥርዓተ ጽዮን"የተባለውም ለዚህ ነው። መሪ ምልክቱ ወይም ትምእርተ ጥቅሱ "ዓይን" ነው። የሥርዓተ ጽዮን ቀኖናት ቁጥራቸው ፴ ነው ሥርዓተ ጽዮን የተጻፈበት ቋንቋ ዕርዕ ነው። ኋላ ግን ወደ ሱርስት፤ ወደ ዓረብኛና ወደ ግእዝ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

የሥርዓተ ጽዮን ቀኖናት ይዘት በዝርዝር ሲታይ፦

1. የሥርዓተ ቅዳሴ ይዘት ትዕዛዝ

- ፊትን ወደ ምሥራቅ አዙሮ መጸለይ (ቀኖና 1)
- በእሑድ ቀን ስለሚደረግ ጸሎት (ቀኖና 2)
- ረቡዕ ቀን ስለሚደረግ ጸሎት (ቀኖና 3)
- ዐርብ ቀን ስለሚደረግ ጸሎት (ቀኖና 4)
- ስለ በዓለ ልደት (ቀኖና 8)
- ስለ በዓለ ኤጲፋንያ (ጥምቀት) (ቀኖና 9)
- ስለ ጾመ ፶ ቅድመ ፋሲካ (ቀኖና 10)
- ስለ በዓለ ዕርገት (ቀኖና 11)
- ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ (ቀኖና 11)
- ስለ ሰማዕታት መታሰቢያ (ቀኖና 21)
- ስለ ቅዱሳን ቁርባን (ቀኖና 30)

2. ስለ ክርስቲያን አገልግሎት ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች

- የቤተክርስቲያን አገልጋዬች መዓርጋት

3. ስለ ቤተክርስቲያን አባል ካህንም ሆነ ምዕመን ጠባይ ***(ቀኖና 14፣20፣23፣26፣29)***

ስለ መሪዎች ቦታ በቤተክርስቲያን ውስጥ (ቀኖና 27፥28)

<u>ዲድስቅልያ</u>

የሥርዓተ ቤተክርስቲያን ምንጮች ብለን ከምናቀርባቸው መካከል ዲድስቅልያ ዋና ተጠቃሽ ነው። ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሚቆጠሩት ሰማንያ አንዱ (፹ወ 1 ዱ) አሥራው ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ነው። ይህን መጽሐፍ ብዙዎቹ "ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት " ይሉታል።

መጽሐፉ ስለ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት አገልግሎት፣ በጋራ ስለሚፈጸሙ የአ hDhD ም ሥርዓትና ምግባር፣ የአምልኮ ሥርዓቶች፣ ስለ ጥምቀት ደግሞ በሰፊው ያትታል። ስለዚህ ዲድስቅልያ ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን ዋና ምንጭ ነው።

2. 34 <u>የቱ ጉባኤያት (የኒቅያ፣ የቁስጥንጥንያ፣ የኤፌሶን ውሳኔዎች)</u>

ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጭነት ከሚጠቀሱት የጉባኤያት ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ሦስት ቢሆኑም ሥርዓትን በተመለከተ ግን ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ የተደረጉ የአኅት አብያተ ክርስቲያናትን ብሔራዊ ጉባኤን ተቀብላ እንደተጠቀመችባቸው የፍትሐ ነገሥት አንድምታ ትርጓሜ መቅድም ያስረዳል።

ስለዚህ በፍትሐ ነገሥቱ ላይም ሆነ በሌሎች የሥርዓት መጻሕፍት ላይ የጉባኤያቱን አንቀጾች አስረጅ አንቀጽ ስንመለከት ከሦስቱ ጉባኤያት ውጭም ያሉ እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል።

2.4.1 <u>የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ</u>

የኒቅያ ጉባኤ በ 325 ዓ.ም አርዮስን ለማውገዝ 318 ሊቃውንት የተሰባሰቡበት ጉባኤ ነው። ለአውግዞተ አርዮስ የሚያሰኝውም ከዚህ ዓለም አቀፍ (Ecumenical) ጉባኤ በፊት ከግብጽና ከሊቢያ በተሰባሰቡ አንድ መቶ ጳጳሳት ተመክሮ ተዘክሮ አልመለስም በማለቱ ተወግዞ ስለነበረ ነው። የዚህም ጉባኤ መሠረታዊ አጀንዳ የአርዮስ ክህደት ቢሆንም በሁለተኛነት የፋሲካን በዓል አከባበር በተመለከተ ሰፊ ውይይት አድርጎ አንቀጸ ሃይማኖትን (ጸሎተ ሃይማኖትን) ያረቀቀና ያጸደቀ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ሥርዓትን በተመለከተ ባለ ፯ አንቀጽ ውሳኔ ወስኗል።

2.4.2 <u>የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ውሳኔ</u>

የቁስጥንጥንያ ጉባኤ የተሰበሰበው በ 381 ዓ.ም ይኸውም በትልቁ ቴዎዶስዮስ ዘመን ማለት ነው። ጉባኤው የተሰበሰባቸው ምክንያቶች የመቅዶንዮስ፣ የአቡሊናርዮስና የአውሳብዮስ ክህደቶች ናቸው።

2.4.**3** <u>የኤፌሶን ጉባኤ ውሳኔ</u>

የኤፌሶን ጉባኤ የተሰበሰበው በ 401 ዓ.ም በትንሹ ቴዎዶስዮስ ዘመን ነው የሰብሰባው ዋና ምክንያት የንስጥሮስ ክህደት እንጂ ስለ ቢላግዮስም ክህደት ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ተሰጥቶበታል። በጉባኤውም ላይ የተገኙት ሁለት መቶ ጳጳሳት ነበሩ። የጉባኤውም ሰብሳቢ ዐምደ ሃይማኖት የሚል ስም የተሰጠው የግብፅ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር። ይህም ጉባኤ ስምንት ቀኖናዎችን ደንግጓል።

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

3. <u>የሕንፃ ቤተክርስቲያን አተካከልና አሠራር</u>

ቤተክርስቲያን ስንተረጉም አንደኛው ትርጉም ሕንፃው እንደሆነ ተመልክተናል። በዚህ መሠረት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ስንል የሕንፃውንም ሥርዓት ይመለከታል።

እግዚአብሔር ከባሕርይ ምልዓቱ የተነሣ የሌለበት ቦታ ባይኖርም ውሱን ፍጥረታት እኛ ለሕሊናችን በሚስማማ ሁኔታ በውስን ቦታ እንድናመልከው አዝዞናል። ይህም ለእኛ መሰባሰቢያ ብቻ ሳይሆን እርሱም ከእኛ በረድኤትና በጸጋ ላለመለየቱ የቃል ኪዳን ቦታ በመሆኑ ነው። እስራኤልን "በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ" ያላቸው ለዚህ ነውና ዘጸ 25፥9። ሰዎችም ምሕረትና ይቅርታ፣ ረድኤትና በረከት ሲፈልጉ ወደዚሁ ቦታ ይወጡ ነበር። "እግዚአብሔርንም የፈለገ ሁሉ ከሠፈር ውጭ ወዳለው ወደ መገናኛው ድንኳን ይወጡ ነበር" እንዲል ዘጸ 33፥7 ከዚህ የተነሣ ቤቱ ቤተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ቤት) እየተባለ ተጠራ። 2 ኛ ዜና 36፥18

ይህ የእግዚአብሔር ቤት ደግሞ በአጋጣሚ የተፈጠረ ስላልሆነ፣ ሲያመች የሚኖር ሳያመችም የሚቀር ባለመሆኑ በሥርዓት ተጀምሯል። የመጀመሪያዋ ድንኳን ደብተራ ኦሪት ከመተከሏ በፊት በደብረ ሲና ሲገለጥ እንኳን የሕዝቡ፣ የአሮንና የሙሴ ቦታ መለያየቱ ልዩ ሥርዓት እንዳላት ያመለክታል ከዚህ ሥርዓት የተነሣ ቅዱስ ዳዊት ይህንን ተራራ ቤተመቅደስ ብሏታል። "ጌታ በመቅደሱ በሲና በመካከላቸው ነው"መዝ 77፥54። "ወደ መቅደሱም ተራራ አገባቸው ቀኙ ወደፈጠረችው ወደዚህች ተራራ"።መዝ 77፥54 በማለት የተናገረው ተራራው ተቦርብሮ እንደ ቤተ ተሠርቶ ሳይሆን ሕዝቡም ሆኑ ካህኑ አሮንና ነቢዩ ሙሴ አምልኮታቸውንና ትእዛዘ እግዚአብሔርን በሥርዓት በመፈጸማቸው ነው። በዚህ መሠረት የሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያንም ያለ ሥርዓት አትተከልም 2 ኛቆሮ 3፥7-11

3.1 <u>የቤተ ክርስቲያን ሥራ ፈቃድ</u>

ቤተ ክርስቲያን ለመትከልና ለመሥራት ሲፈለግ የክፍሉን ኤጲስ ቆጶስ ማስፈቀድ ይገባል። ያለ ኤጲስ ቆጶስ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያን አይተከልም አይሠራም (ፍት.መን አን 1 ቁ 3) ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናትና በግለሰብ ፈቃድና ስምምነት ብቻ አትተከልም። ራሱ ባለቤቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያሰሩና እንዲፈቱ ፈቃዱንም አውቀው እንዲፈጽሙ ሥልጣኑንም ጸጋውንም የሰጣቸው ጳጳሳት መፍቀድ አለባቸው። ይህም የእነርሱ ግለሰባዊ ፈቃድ ሳይሆን ፈቃደ እግዚአብሔር የሚታወቅበት በሥርዓት የመኖራችን መገለጫ ነው።

3.2 <u>የሕንፃ ቤተክርስቲያን ዐቅድ (ፕላን)</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሥዋዕት የምትሠዋው፣ ለምእመናን ሕገ እግዚአብሔርን የምታስተምረው፣ በአጠቃላይ ሰውን ለመንግሥተ እግዚአብሔር የምታዘጋጀው በቤተመቅደስ ነው። ይህ ቤተ መቅደስ ቅዱሳን መላእክት በሰማይ እንደሚያገለግሉበት ያለ በሰማያዊ ሥርዓት አምሳል የተበጀ የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ነው። ከቅዱሳን መላእክት የተወሰደ በሰማያዊው ሥርዓት አንጻር የታነፀ በመሆኑ ስንሠራው፣ ስናገለግልበት፣ ስንገለገልበት በሥርዓት ሲሆን ይገባል ለዚህ ነው ቤተክርስቲያን ሕንፃውን ስትሰራ ጥንቃቄ የምታደርገው። ሕንፃው ሲታነፅ ምሥጢር እንዳይፋለስ አሠራሩ ትርጉም አልባ እንዳይሆን አበው ይጠነቀቁበታል። ቤተ መቅደስ ሲሠራ ቅርጹ ከክርስቶስ የዓለም ቤዛነት ጉዞ፣ ከቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ከቅዱሳን ተጋድሎ ጋር የተያያዘ እንዲሆን ሆኖ ነው።

ቤተክርስቲያን ሲሠራ ሥርዓተ እንዳለው ለመረዳት በቤተክርስቲያን የሚታወቁ የአሠራር ዓይነቶች ቀጥለን እንመለከታለን።

3.2.1 <u>ክብ ቅርጽ</u>

በአገራችን በብዛት የምንገለገልበት ይህ የቤተ መቅደስ ዓይነት ነው። ክብ ቅርጽ ተብሎ የሚጠራው ዙሪያው ክብ የሆነና ውስጡ በሦስት የተለያዩ ክፍሎች የሚከፈል ስለሆነ ነው። ሦስት በሮችም ይኖሩታል። ክብ ቅርጽ ቤተ ንጉሥ ቅርጽ ይባላል። ባለ አንድ ጉልላት ሲሆን በጉልላቱ የቤተክርስቲያን ግርማ የሆነው መስቀል ይደረጋል። ቤቱ

ንጉሥ የሚባልበት ምክንያት የቀድሞ አንዳንድ ነገሥታት በራሳቸው ቤት በቤተ መንግሥታቸው አምሳል ስለ ሠሩት ነው ነገሥታቱም ይህንኑ ያደርጉ የነበረው እኛ ምድራዊ ነገሥታት ነን ሥልጣናችንም ኃላፊ ነው፤ አንተ ግን ዘላለማዊ ንጉሥ ስለ ሆንክ እንዲህ ያለ ያማረ ቅርጽ ያለው ቤት /ቤተ መቅደስ/ ይገባሃል በማለት ነበር።

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው በፊልጵስዩስ የተሠራቸው የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን እንዲህ ያለ ቅርጽ ነበራት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ክብ መሆኑ ፍጹምነትን እንደሚያመለክት ያስተምራሉ። ለምሳሌ ቅዱሳን ስዕላቸው ሲሳል ዐይናቸው፣ ገጻቸው ክብ ሆኖ የሚሣለው ሃይማኖትን ከምግባር አዋሕደው የተገኙና ከሕግ በላይ ሆኑ (የሕጉን ፈጽመው በትሩፋት የሚኖሩ) ቅዱሳን መሆናቸውን ለመግለጥ ነው። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ክብ የሆነችበትም ምክንያት ከዚህ የተያያዘ እንደ ሆነ መገንዘቡ አያዳግትም። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ልጆቿን ለፍጹምነት መዓረግ የምታበቃ ቅዱሳን የሆነ ቅዱሳንን በተጋድሎ ያጸናች በመሆኗ ሙሉ ክብ ሆና ተሠርታለች።

3.2.2 <u>ሰቀለማ ወይም ሞላለ ቅርጽ</u>

ይህ ቤተ መቅደስ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው፣ ሞላላ የሆነና ከፍ ብሎ የሚታነፅ ነው። አሠራሩም የተወሰደው ንጉሥ ሰሎሞን ካነፀው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ ይተረካል። በአገራችን የአክሱም ጽዮን የቀድሞ ቤተክርስቲያን፣ ደብረ ብርሃን ሥላሴ፣ ደብረ ዳሞ ለዚህ ቅርጽ ምሳሌ ሆነው ይጠቀሳሉ። ዐፄ ዮሐንስ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ያሠሩት የጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት የቀድሞ ቤተክርስቲያንም ዐሥራ ስምንት ጉልላት ያለውና ሰቀላማ ቅርጽ ያለው ነበር።

የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ሞላላ ቅርጽ ያለውን ይህንን ቤተ መቅደስ ጌታችን የፈጸመውን የድኅነት ሥራ እንድናስብበት፣ ከመስቀል ጋር የሚያያዙበት ወቅት አለ። ከመስቀል ጋር ሲያያዝ መሠረቱ የመስቀል ቅርጽ ይኖረውና ግድግዳውም በዚያም መልክ ወደ ላይ ይታነፃል ሞላልነቱም እንደተጠበቀ ነው። በአዲስ አበባ የሚገኙት የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን (ካቴድራል)፣ የምስካየ ኅዙናን መድኃኒዓለም ገዳም፣ እንዲሁም በደብረ ሊባኖስ ገዳም የአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ለዚህ ዓይነቱ ሕንፃ አሠራር ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው።

3.2.3 <u>ዋሻ ቅርጽ</u>

የጥንት ክርስቲያኖች በዘመነ ሰማዕታት ከዓለውያን ነገሥታት ሸሽተው በዋሻ ሲሸሸጉ የጀመሩት የቤተ መቅደስ ዓይነት ነው። በሩ አንድ ሲሆን በውስጥ ያሉት ክፍሎች ብዙ ጊዜ የሚለያዩት በመጋረጃ ነው። ጉልላት የለውም። ይህ ቤተ መቅደስ የሚታነፀው ተራራ በመፈልፈል በዋሻ ውስጥ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከተራራ ተነጥሎ ለብቻው የቆመ ድንጋይን /አለትን/ በመፈልፈል ሊሠራ ይችላል። ተራራ ተፈልፍሎ ከተሠሩ የዋሻ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አቡነ ሀብተ ማርያም ገዳም፣ አዳዲ ማርያም በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡ ከአለታቸው (ቋጥኛቸው) ተነጥለውና ተፈልፍለው ከተሠሩት መካከል ደግሞ የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ቤተ መድኃኒዓለም፣ ቤተ ጊዮርጊስ ተጠቃሽ ናቸው።

ከላይ ያየናቸው ሦስቱ የቤተ መቅደስ አሠራር ዓይነቶች ከሚሰጡት አገልግሎት፤ በውስጥ ካላቸው የክፍፍል ዓይነት አንድ የሚሆኑበት እንዲሁም የሚለያዩበት ነጥብ አለ ይህም ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ተገልጾል።

<u>አንድ የሚሆኑት</u>	<u>የሚለያዩበት</u>
❖ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት፣ መቅደስ አላቸው	❖ ሰቀላማና ክብ ቅርጽ አብያተ መቅደስ ጉልላት ሲኖራቸው ዋሻ ቅርጽ ቤተ መቅደስ ግን ጉልላት

የለውም።

- በውስጣቸው የሚፈጸመው የቅዳሴ፣ የማኅሌት፣ የሰዓታት የጸሎት ሥርዓት አንድ አይነት ነው።
- ስቀላማና ዋሻ ቅርጽ አብያተ መቅደስ የውስጥ ክፍሎቻቸው የሚከፋፈሉት በመጋረጃና ወለሉን ከፍ በማድረግ /በደረጃ ሲሆን ክብ ቅርጽ ግን በግድግዳ ይከፋፈላል።
- በሰቀላማና ዋሻ ቅርጽ አብያተ መቅደስ የሴቶችና የወንዶች መቋሚያ የሚለየው በመጋረጃ ሲሆን ክብ ቅርጽ ባሉበት ቤተ ክርስቲያን ግን በተለያዩ ቦታ ሆነው ያስቀድሳሉ።

3.3 <u>የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች</u>

ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ቢሠራም 3 ክፍል አለው፤ ይኸውም ሰሎሞን ቤተ መቅደስ አምሳል መሆኑ ነው፣ ምክንያቱም ለብዙው ክርስትና እምነት ሥርዓት መሠረቱና ምሳሌው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው። እንግዲህ ለቤተ ክርስቲያናችን 3 ክፍሎች አሉ ስንል የእያንዳንዱ ክፍል አቀማመጥና ጥቅም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ሀ. <u>ቅኔ ማኅሌት</u>

የመጀመሪያው ክፍል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ የሚገኘው ዙሪያው በመላ ቅኔ ማኅሌት ይባላል። ስያሜው ከግብሩ የተወረሰ ነው። ምክንያቱም ሥርዓተ ማኅሌት ይከናወንበታል። መዘምራን፣ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ማኅሌተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት መዝሙር የሚዘምሩበት ክፍል ነው። ቅኔ ይቀኙበታል፣ ዳዊት ያስተዛዝሉበታል።

በቅኔ ማኅሌቱ በመስዕ (ሰሜናዊ ምሥራቅ) በኩል ቀሳውስትና ዲያቆናት በመንፈቀ ሌሊት በነግህ ሰዓታት ይቆሙበታል፤ ኪዳን ያደርሱበታል፣ በጥንት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸው በዚሁ ክፍል ነበር፤ ለጥምቀተ ክርስትናና ለቁርባን ያልበቁ በትምህርት፣ በንሰሐ ገና የሚፈተኑ ሐዲስ አማንያንም (ንዑስ ክርስቲያን) ዲያቆኑ "ዓው ንዑስ ክርስቲያን" እስከሚል ድረስ በዚያ ይቆያሉ፣ ዲያቆኑ "የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ" ብሎ በደውል ሲያውጅ ወደ መካነ ቀኖናቸው ተመልሰው ይሄዳሉ። ወንዶች ምእመናንም ቆመው የሚያስቀድሱት በዚሁ ቦታ ነው።

መዘምራን በሚዘምሩበት በቅኔ ማኅሌት ቆመው የሚያስቀድሱ ንፋቅ ዲያቆናት፣ አናጉንስጢስ፣ መዘምራን ናቸው። (ፉት መን አንቀጽ 9) ቅኔ ማኅሌቱ በሌብ (ደቡባዊ ምሥራቅ) በኩል የሚገኘው ቦታ የሴቶች መቆሚያ ነው። በቤተክርስቲያን ሥርዓት ወንዶችና ሴቶች አብረው ቆመው ስለማይጸልዩ በመጋረጃ ይከፈላል። ክፍሉ በምሥራቅ የካህናት መግቢያና፣ በሰሜን የወንዶች መግቢያ፣ በደቡብ የሴቶች መግቢያ በር 3 አለው።

<u>ለ. ቅድስት</u>

ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው። የቤተ ክርስቲያኑ ማዕከላዊ ቦታ ነው። በዚህ ክፍል በስተምዕራብ በኩል ቆመው የሚያስቀድሱት ቆሞሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ናቸው፤ በስተሰሜን በኩል መነኮሳትና የሚቆርቡ ወንዶች ምዕመናን፣ በስተደቡብ በኩል ደናግል መነኮሳይያት፣ የካህናት፣ የዲያቆናት ሚስቶችና የሚቆርቡ ምዕመናት ቆመው ያስቀድሱበታል። በዚሁ ክፍል ቆመው ላስቀደሱ ምዕመናን ሥርዓት ቁርባን ይፈጸማል። ከሥርዓተ

ጥምቀትና ከሥርዓተ ንሰሐ በስተቀር የሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጸሎት የሚፈጸመውም በተክሊልና በቁርባን አንድ ለሚሆኑ ሙሽሮች ጸሎት የሚደርስበትና በካህናት እጅ የሚባረኩበት ክፍል ነው። የምሥጢረ ቀንዲል ጸሎትም በዚህ ክፍል ይፈጸማል። ቅድስቱ በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ አራት በሮች ሊኖሩት ይገባል። የማይቆርቡ ምእመናን በዚህ ክፍል ቆመው ማስቀደስ የለባቸውም።

ሐ. <u>መቅደስ</u>

በብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን በሚል ስያሜ ከሚታወቀው ውስጠኛው ክፍል ጋር የሚነጻጸር ነው። በዚህ ውስጥ ምሥጢረ ቁርባን፣ ሥርዓተ ቁርባን ይፈጸምበታል፣ መንበረ ታቦቱ፣ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ። በዚህ ክፍል ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ጀምሮ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያስቀድሳሉ። ወደዚህ ክፍል መግባት የሚችሉ ካህናትና ዲያቆናት ብቻ ናቸው። መቅደሱ 3 በር አለው። ይህም በር የምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ ነው። ለእያንዳንዱ በር መንጦላዕት (መጋረጃ) አለው። የዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ባለ አንድ ጉልላት ነው።

<u>ለምን ሦስት ሆኑ?</u>

ሀ. በሦስቱ ዓለማተ መላእክት (የመላእክት ከተሞች)

ምሳሌ፦ እነዚህ ሦስት የመላእክት ከተሞች

1. ኢዮር 2. ራማ 3. ኤረር በመባል ይታወቃሉ።

ለ. በሦስቱ መዓርጋተ ክህነት ምሳሌ

1. ዲቁና 2. ቅስና 3. ኤጲስ ቆጶስነት

ሐ. የሦስቱ ጥሃተ ገነት (የገነት በሮች) ምሳሌ

መ. በታቦተ አዳም፣ በታቦተ ሙሴና በታቦተ መላእክት አምሳል

3.4 <u>በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚሠሩ አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች</u>

ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ የሚሠራው አንድ ቤት ብቻ አይደለም። በቤተክርስቲያኑ ሊሠሩ የሚገባቸው ከቤተክርስቲያኑ ጋር አብረው አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች አሉ። በቤተክርስቲያኑ ምሥራቅ ዲያቆናቱ ለመስዋዕት የሚሆነው ጎብስትና ወይን የሚያዘጋጁበት ሁለተኛው ቤት ይሠራል። ይህም ቤት "ቤተልሔም" ይባላል። ስያሜው የተወሰደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተልሔም ዘይሁዳ ምሳሌ ነው። ምሥጢሩና ቁም ነገሩ ደግሞ ዲያቆናት ጎብስቱንና ወይኑን በቤተልሔም አዘጋጅተው ወደ ቤተክርስቲያን ለመሥዋዕት ማምጣታቸው በቤተልሔም የተወሰደው፣ በቀራንዮ ለመሥዋዕት የቀረበው ክርስቶስ ይህ ነው ለማለት ነው። መቅደስ የቀራንዮ ምሳሌ ነው። ለመሥዋዕት የሚቀርበው (መገበሪያ) የሚሰየምበት፣ በቤተክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ የሚሠራ ሦስተኛ ቤት አለ። ይህም "የግብር ቤት" ይባላል። ስንዴው መገበሪያ ተብሎአልና። መገበሪያውን አሰናድቶ ማቅረቡ ደግሞ መሰይም ይባላል። ይህም የመሥዋዕቱ አቀራረብ ቋንቋ ነው።

የቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት የሚቀመጡበት አራተኛ ቤትም ይሠራል። ይህም ዕቃ ቤት ይባላል። የቤተክርስቲያኑ መገልገያ የሆኑት አልባሳትም፣ መጻሕፍትም የሚጠበቁት በዚሁ ቦታ ነው። (ሕዝ 44፥19፣ ፍት መን 12) ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸምበት የማጥመቂያ ቤትም አለ። ከዚህም ሌላ በገጠር ባሉ አብያተ ክርስቲያናትም የሙታን በድን የሚያርፉበትና ጸሎተ ፍትሐት የሚፈጸምበት <u>ደጀ ሰላም</u> ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ተያይዞ ይሠራል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት 5 ቤቶች በግድ ከቤተክርስቲያኑ ሳይለዩ አብረው የሚሠሩ አስፈላጊዎች ቤቶች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እንደ ምዕመናን ዐቅም ሊሠሩ የሚገባቸው ቤቶች አሉ። እነዚህም፡-

ሀ. የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት

ለ. የሰንበት ት/ቤት ክፍሎች

ሐ. የስብከተ ወንጌል አዳራሽ

መ. የእንግዶችና የካህናት ማረፊያ ቤቶች

ሠ. የመንፈሳዊ ት/ቤትና የተግባረ እድ መማርያ ክፍሎች

ረ. ቤተ መጻሕፍት ሰ. የንዋየ ቅድሳትና ጧፍ ዕጣን መሸጫ ክፍሎች ናቸው።

ምዕራፍ አራት

4. ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሔድ የሚደረግ ዝግጅት /ጥንቃቄ

ጠቢቡ ሰሎሞን "ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ" /መክ 5፥1/ እንዲል ወደ ቤተ መቅደስ ለመሄድ የሚነሣ ሰው እግሩን መጠበቅ ማለትም እግረ ሥጋውን ከማይገባ ቦታ እግረ ጎሊናውን ከኃጢአት ከበደል መጠበቅ ይገባዋል። መቼ፣ እንዴት ሆኖ ወደ ቤተ መቅደስ /ቅድመ እግዚአብሔር/ መግባት እንዳለበት ማወቅና አስቀድሞ መዘጋጀት ይኖርበታል። ወደ ቤተ መቅደስ ከመግባት አስቀድሞ ሊደረጉ የሚገባቸውን ዝግጅቶች በቅደም ተከተል እንመለከታቸዋለን።

4.1 የልቡና ዝግጅት

ወደ ቤተ መቅደስ ለመሄድ የሚነሣ ሰው ከሁሉ አስቀድሞ የልቡና ዝግጅት ያስፈልገዋል። ይኸውም ልቡናውን ከቂም ከበቀል፣ ከክፋት ከተንኮል፣ ከዝሙት ንጹሕ ማድረጉንና አለማድረጉን መመርመር አለበት። ምክንያቱም እርሱ አስቀድሞ ራሱን ካልመረመረ ልቡናንና ኩላሊትን የሚመረምር እግዚአብሔር ሊመረምረው ሊንቀውም ይቻላልና ነው። /መዝ 7፥9/

እግዚአብሔር በሊቀ ነቢያት ሙሴ አማካይነት ሕዝበ እስራኤልን ካዘዛቸው ትእዛዝ አንዱ የልቡና ግርዛት ነው። ወደ እርሱ ሲመጡ በድንኳኑ ፊት ሲሰግዱ ከነበደላቸው እንዳይቀርቡ "የልቦናችሁን ሸለፈት ተገዘሩ" ብሏቸዋል። "እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶች ጌታ ታላቅ አምላክ፣ ኃያልም የሚያስፈራም፣ በፍርድ የሚያዳላ፣ መማለጃም የማይቀበል ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፤ ከእንግዲህ ወዲህም አንገተ ደንዳና አትሁኑ" ዘዳ 10፥16 የልቡናን ሸለፈት መገዘር ማለት የልቡናን መሰበር፣ ከቂም ከበቀል ነጻ መሆን፣ ከአምልኮ ጣዖት መራቅ፣ በአጠቃላይ እግዚአብሔር ከማይወደው ነገር ሁሉ መለየትና መራቅ ነው።

ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙሩ "መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር መንፈስ የዋህ ልበ ትሑተ ወየዋህ ኢይሜንን እግዚአብሔር የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፤ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም"። /መዝ 50፥17/ ይለናል። ክቡር ዳዊት በእጃችን ከምንይዘው ጧፍና ሻማ፣ ለቤተ መቅደስ ከምናቀርበው መባዕና ስእለት በፊት እግዚአብሔር የእኛን ስጋ እንደሚሻ ነግሮናል። ይህም ለእግዚአብሔር ልባዊ ስጦታ ማቅረብ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው። ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ "ኢታፍቅርዋ ዓለም፤ ወሐድሱ ልበክሙ፤ ወኢመክሩ ዘይፈቅድ እግዚአብሔር ዘሠናይ ወዘ ጽድቅ ወዘፈጽም - የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ

የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነ ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ“ /ሮሜ 12፥2/ ብሎናል። ጌታችንም በወንጌል “ብፁዓን ንጹሐነ ልብ እስመ እሙንቱ ይሬእይዋ ለእግዚአብሔር ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ እግዚአብሔርን ያዩታልና“ /ማቴ 5፥8/ ስለዚህ የሰው ልጅ ልቡናውን አንጽቶ ከቀረበ እግዚአብሔርን በቸርነቱ ማየት ይችላል።

ልቡናችንን በንሰሐ መርምረን ከኃጢአት ተለይተን ከቀረብን እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይቀበላል፣ በምናቀርበው መባዕ ይደሰታል እግዚአብሔር ከመባችን ከመሰዋዕታችን በፊትና በላይ ውስጣችንን የልባችንን ቀናነት ይመለከታል። “እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ“ /ዘፍ 4፥4/ የተባለው የአቤል የልቡ ቅንነትና የመሥዋዕቱ ደግነት ነው። እግዚአብሔር ከመሥዋዕቱ በፊት የተመለከተው አቤልን ነበር። በእኛም ሕይወት ከኃጢአታችን ጋር ወደ ቤተ መቅደሱ ከመቅረባችን በፊት እኛን እንደሚመለከት ሳንዘነጋ ራሳችንን በንሰሐ እናዘጋጅ ዘንድ ይገባል።

4.2 <u>ንጹሕ ልብስ መልበስ</u>

ቤተ መቅደስ መልካም መዓዛ ያለው እጣን ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት፣ ምእመናን የልባቸው መሻት የከንፈራቸው ፍሬ የሆነውን ጸሎታቸውን የሚያቀርቡበት፣ የሐዲስ ኪዳኑ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሠዋበት ንጹሕ የሰርግ ቤት ነው። በዚህ ፊት በሰዉ ልጆች ነፍስና ስጋ ላይ የሚፈርደው የጌቶች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር አለ። በዚህ ቤት በሥጋም በነፍስም ንጽሕት የሆነች እመቤታችንና ቅዱሳን አሉ።

ከዚህ አንግር ለቅዳሴ፣ ለኪዳን፣ ለሰዓታት፣ ጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄድ ሰው ይኸንን ማሰብ አለበት፤ ለሰማያዊ ሰርግ እንደተጠራ፣ በንጉሥ ፊት እንደሚቆም፣ ከቅዱሳን ጋር እንደሚታደም አስቦ ልብሱን ንጹሕ ማድረግና መዘጋጀት ይገባዋል። አንዳንድ ሰው ጎረቤቱ ሰርግ ሲጠራው ምን እንደሚለብስ በማሰብ የሚጨነቅ ሲሆን ወደ ትልቁ ሰርግ ወደ ቅዳሴው ሲቀርብ ግን ለዐይን ደስ በማያሰኝና ባገኘው ልብስ የሚሄድ አለ። በምድራዊ ባለሥልጣን ፊት ሲቀርብ ልብሱን አጥቦ አንጽቶ የሚቀርብ በንጉሠ ሰማይ ወምድር በእግዚአብሔር ቤት ሲቆም ግን ግድ የሌለው ነው። ይኸ ግን ስህተት ነው።

አባታችን ያዕቆብ በአንቱ በላባ ቤት ለአሥራ አራት መቶ ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ተመልሶ መሥዋዕት እንዲሠዋ ሲያዘው ቤተሰቦቹን ልብሳቸውን እንዲለውጡ አዝዟቸው ነበር። “እንግዶቹን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ፣ ንጹሐንም ሁኑ፣ ልብሳችሁንም ልበሱ፤ ተነሥተንም ወደ ቤቴል እንውጣ፤ በዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ በሄድሁባትም መንገድ ከእኔ ጋር ለነበረው ለእግዚአብሔር መውጪያን አደርጋለሁ።“ ብሏቸዋል። /ዘፍ 35፥2/

ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን በምንሄድበት ቀን ወደ ሥራ ገበታችንና ወደ ሰርግ ስንሄድ ከምንዘጋጀው በላይ ተዘጋጅተን ጸዐዳ ለብሰን ሰውነታችንን ንጹሕ አድርገን መሄድ ይኖርብናል።

4.3 ***ልብስን ማደግደግ ወይም በትምህርተ መስቀል መልበስ***

ወደ ቤተ መቅደስ ስንሔድ ነጭ መልበሳችን የተገባ ነው። ነጭ ነጠላ፣ ጋቢ አደግድገን ወይም የተገባ ነው። በትእምርተ መስቀል በዚሁ መልኩ ለብሰን በቤተ መቅደስ ደርሰን ስንቆም የምማስባቸው ምሥጢራት አሉ።

4.3.1 ለምን በትእምርተ መስቀል እንለብሳለን?

የክርስቶስን መከራ ለማሰብ፣ ነጠላው ወደ ግራና ቀኝ በትምእርተ መስቀል አምሳል ይጣፋል። በዚህ ጊዜ ጌታችን በዕለተ አርብ የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራ እንዲሁም በቀራንዮ በመልዕልተ መስቀል መስቀሉን ያስታውሰናል። ይኸንን የተመሳቀለ ነጠላ የሚመለከትም ሁሉ የጌታችንን መከራ መስቀል መቀበል ያስባል።

4.3.2 ለምን ነጭ እንለብሳለን?

ሀ. የሚጠብቀንን ሰማያዊ ክብር ለማሰብ

በምድር ላይ በብዙ መከራ ተፈትነው ያለፉና ለክብር የበቁ ቅዱሳን በሰማይ የክብርና የቅድስና ምስክር (መግለጫ) ነጭ ልብስ ይሰጣቸዋል ማለትም ብርሃን ይለብሳሉ በአንድነትም ይዘምራሉ። ራእ 6-9-11

“ከዚህ በኋላ አየሁ እነሆም፥- አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤“ በማለት በሰማይ በክብር የሚኖሩ ቅዱሳን ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጎናጽፈው እንደተመለከተ ቅዱስ ዮሐንስ ገልጾልናል። ራእ 7፥9 እኛም በሃይማኖት በምግባር ጸንተን ካለፍን በሰማይ ይኸ ክብር ይጠብቀናል ያንን ለማሰብ ነጭ ልብስ እንለብሳለን።

ከዚህም በተጨማሪ ነጭ ስንለብስ ብርሃን የለበሱ ቅዱሳን ከእኛ ጋር እንዳሉና በዙሪያችን ሆነው ስለ እኛ እንደሚያማልዱ እናስባለን። ዕብ 12፥1

ለ. ቅዱሳን መላእክት ከእኛ ጋር መሆናቸውን ለማሰብ

ጌታችን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ ሥጋውን ሽቱ ሊቀቡት ወደ መቃብሩ ለወረዱ ሴቶች ቅዱሳን መላእክት ከበረዶ ይልቅ የነጣ ነጭ ልብስ ለብሰው ተገልጠውላቸዋል። “ወማርያምስ ቆመት ኀበ መቃብር አፍአ ወትበኪ፤ ወእንዘ ትበኪ ሐወይት ውስተ መቃብር። ወርእየት ክልኤተ መላእክተ በጸዓድው አልባስ፤ ወይነብሩ አሐዱ ትርአስ ወአሐዱ ትርጋዕ ኀበ ነበረ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በስተውጭ ቆማ ነበረ። ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች፤ ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የጌታ ኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ አንዱ በራስጌ ሌላው በግርጌ ተቀምጠው አየች።“ ዮሐ 20፥11-16 ነጭ ለብሰን ስናስቀድስ ቅዱሳን መላእክት በጥበቃቸውና በተራዳኢነታቸው ከእኛ እንደማይርቁ ሁልጊዜ ከጎናችን እንደሚሆኑ እናስባለን።

ሐ. <u>ከጌታችን ጋር እንዳለን እንድናስብ</u>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር ሲገልጥ ልብሱ እንደ በረዶ ነጭ ሆኗል። "ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ለብቻቸው አወጣቸው። በፊታቸውም መልኩ ተለወጠ፤ ፊቱን እንደ ፀሐይ አበራ፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ሆነ።" ማቴ 17፥1-2

በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ምሥጢረ መንግሥቱን የገለጠ፣ በአዕማደ ሐዋርያት ፊት ገጹ ሲለወጥ ደቀ መዛሙርቱ እንዲመለከቱት የፈቀደ አምላክ ከእኛም ጋር እንዳለ ለማሰብ በቤተ ክርስቲያን ነጭ ለብሰን እንቆማለን እንመላለሳለን። እንዲሁም ምሥጢረ ሥላሴ ምሥጢረ ሥጋዌ የሚታመንባት፣ የሚነበብባት፣ የሚተረጎምባት አማናዊት ደብረ ታቦር ቤተ ክርስቲያን እንደ ሆነች ለማሰብ ነጭ እንለብሳለን።

4.4 <u>መባዕ (ስጦታ) ይዞ መቅረብ</u>

ወደ ቤተ መቅደስ ስንሄድ ባዶ እጃችንን ሳይሆን መባዕ ይዘን መሄድ ያስፈልጋል። መባዕ (ስጦታ) ይዞ መቅረብ እንደሚገባ የሚያዝዘውን ሕግ የሠራው እግዚአብሔር ነው። በብሉይ ኪዳን እስራኤላዊያን ወደ ቤተ መቅደስ ሲቀርቡ መባዕ ወይም ስጦታ እንዲይዙ ታዝዘው ነበር፤ ዘጸ 25፥1

በሐዲስ ኪዳንም መባዕ ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ እንደሚገባ በዚህ መልኩ ተናግሯል። "እንግዲህ መባዕን በመሠውያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፣ በዚያ በመሠውያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፣ አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ፣ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ" ማቴ 5፥23-24 በዚህ ምዕራፍ ጌታችን ያስተማረው ስለ እርቅ ቢሆንም በውስጡ ግን መባዕ በማቅረብ፣ ሻማ፣ ጧፍ፣ ዕጣን፣ ዘቢብ፣ መጋረጃ፣ ጥላ ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ ማቅረብ እንዳለ ገልጾልናል።

ከዚህ አንባር መንፈሳዊ ሰው ወደ ቤተ መቅደስ ሲሄድ "ኢትቁም ዕራቀከ ቅድመ እግዚአብሔር - በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጅህን አትቁም" እንደተባለ አስቦ ወቅሙ የሚፈቅድለትን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይኖርበታል። ቅዱስ ዳዊት "ከእጅህ የወሰድነውን መልሰን ሰጠንህ" እንዳለ ሰው ከእግዚአብሔር ያገኘውን መልሶ ለእግዚአብሔር መባዕ አድረጎ በማቅረብ በረከት ማግኘት ይገባዋል።

አባታችን አብርሃም በመልከ ጼዴቅ ፊት በቀረበ ጊዜ መልከጼዴቅ የጌታችን ሥጋና ደም ምሳሌ የሆነውን ኅብስትና ወይን አቀበለው። አብርሃም ደግሞ ዓሥራትን ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው። ዘፍ 14፥17 ዛሬም ካህናት እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሲያቀብሉን ምእመኑ ደግሞ እንደ አብርሃም ዓሥራቱን በኩራቱን ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት ያቀርባሉ። ከአበው የወረደ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነውና፤ ስለዚህ ያስታወሰ ስለት፣ በአጋጣሚ ድንገት፣ ሰው ሲያደርግ ስላየ ሳይሆን ትእዛዝ መሆኑን አስቦ ወደ ቤተ መቅደስ የሚቀርብ ሰው የቻለውንና ተገቢ የሆነውን መባዕ ሳይዝ መሄድ የለበትም።

4.5 በትምህርተ መስቀል አማትቦ ደጃፉን (ደጀ ሰላሙን) መሳለም

4.5.1 ማማተብ

ደጃፉን ለመሳለም ስንቀርብ አስቀድመን በመስቀል አምሳል እናማትባለን። ይኸም መንፈሳዊ ትርጉም አለው።

4.5.1.1 የማማተብ መንፈሳዊ ትርጉም

ጣቶታችንን በትእምርተ መስቀል ካመሳቀልን በኋላ ከላይ ወደ ታች (ከግንባራችን ወደ ደረት) እንወረዳለን። ይኸም እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ለማመልከት ነው። በመቀጠል ጣቶቻችንን ወደ ግራ ተከሻችን እንወስድና መልሰን ወደ ቀኝ ተከሻችን እናመጣቸዋለን። ከሰማየ ሰማያት በተለየ አካሉ በተወላዲነት የወረደው ቃለ እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግራ (ወደ ሲኦል) በአካለ ነፍስ እንደ ወረደና ነፍሳትን ወደ ቀኝ (ወደ ገነት) እንዳሸጋገረ ለማመልከት ነው። በአጠቃላይ በምሥጢረ ሥጋዌ የተፈጸመልንን የድኅነት ሥራ እንመሰክራለን።

4.5.1.2 ስናማትብ የምናስባቸው ምሥጢራት

ጣቶቻችንን በትእምርተ መስቀል አመሳቅለን ስናማትብ ኅሊናችን የሚያወጣቸውና የሚያወርዳቸው ልቦናችን የሚያስባቸው የተለያዩ ምሥጢራት ይኖራሉ የተወሰኑትን እንመልከት

4.5.1.2.1 ስናማትብ ጌታችን ስለ መዳናችን በመስቀል ላይ እንደሞተልን እንመሰክራለን

ክርስቲያን ጌታችን ዳግመኛ እስኪመጣ ሞቱን ሕማሙን በየጊዜው በየሰዓቱ ማሰብ መመስከር ይገባዋል። ሞቱን የምንናገረው ደግሞ በጊዜ ቁርባን ብቻ አይደለም ሥጋውን ደሙን ስንቀበል የምናማትበው በቤተ መቅደሱ መሥዋዕት ፊት ነው። ከዚያ ውጭም በጉዞ፣ በምግብ፣ በሥራ ወዘተ በተለያዩ ጊዜያት ማማተብ ይገባል። ይኸም ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ በቀራንዮ (ጎልጎታ) እንደሞተልን ለመመስከር ነው።

4.5.1.2.2 ስናማትብ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እናስባለን

ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" (ዮሐ 15፥13) በማለት ሰውነቱን ለሌላው ቤዛ አድርጎ ለሕማም ለሞት አሳልፎ ከመስጠት በላይ ፍቅር እንደሌለ ተናግሯል። እውነተኛ ፍቅር፣ ፍጹም ፍቅር እስከ ሞት ያደርሳል፤ ተላልፎ እስከ መስጠት ያደርሳል። ይኸን ፍጹም የሆነ ፍቅር ያየነው በወልደ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነው። እርሱ ስለ እኛ በመስቀል ተሰቅሎ ሞቶልናልና። ዮሐ 3፥16 ስናማትብ የምናስበው ይኸንን የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ እግዚአብሔር እስከ መስቀል ሞት ደርሶ ምን ያህል እንደወደደን።

4.5.1.2.3 ስናማትብ የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንደሆነ እናስባለን

መድኃኔዓለም ክርስቶስ ስለ እኛ ከመስቀሉ በፊት የሰው ልጆች በበደላችን ሙታን ነበርን። ሞት ጥላውን አጥልቶብን ውጦን ይኖር ነበር። ጌታችን በመስቀል ላይ የተሰቀለው ሞታችንን በሞቱ ሊያጠፋ፣ እርሱ ስለ እኛ ቤዛ ሆኖ ሊሞት ነው። ኤፌ 2፥5። ስለዚህ ስናማትብ የምናስበው በክፉ ምኞት የሚጸነሰው የኃጢአት ደመወዙ ሞት መሆኑን ነው። መድኃኒዓለም ክርስቶስ እኛ በበደላችን ሞት ስለ ተፈረደብን የእኛን ሞት እርሱ ሞተ በመስቀል ተሰቀለ።

4.5.1.2.4 <u>ስናማትብ መስቀል ኃይላችን እንደሆነ እናስባለን</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። የክርስቶስ በመስቀል መከራ የመቀበሉ ነገር ባላመኑ ሰዎች ዘንድ ስንፍና ነውና። በእኛ ዘንድ ግን ኃይለ እግዚአብሔር ነው" ያለው ቅዱስ ሥጋውን የደረሰበት ክቡር ደሙን ያፈሰሰበት ቅድስት ነፍሱን የሰጠበት ዕፀ መስቀሉ ኃይሉ ስለተገለጠበት ነው። (1 ቆሮ 1፥18) ሐዋርያው አትናቴዎስም "ኃጢአትን በምድር ላይ አሳረፈ ሞትንም በሲኦል መርገምንም በመስቀል ላይ ሻረ።" ብሏል መስቀል ሞት የተሻረበት ስለሆነ ስናማትብ በመስቀሉ ጸጋን መስጠቱን፣ ሞትን ድል መንሳቱን እናስታውሳለን። ዛሬም በመስቀሉ ኃይል ፈተናን ድል እንደምናደርግ እናስባለን በመስቀሉ በረከትንና ኃይልን እንሞላለን

4.5.1.2.5 <u>ስናማትብ ጠላታችንን ዲያብሎስን እናሳፍራለን</u>

"ጥልን በመስቀሉ ገድሎ /ዲያብሎስን በመስቀሉ ድል ነስቶ/ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀቻቸው። ሁለታቸውን ከተሰፋው ርቀው የነበሩትንና ወደ ተሰፋው ቀርበን የነበርነውን አንድ አደረገን።" ይላል ኤፌ 2፥16።

ዲያብሎስን "ጥል" ያለው በግብሩ ሲጠራው ነው፤ ዲያብሎስ ድል የተነሳው በመስቀል ነው። ጌታችን በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ ዲያብሎን በነፋስ አውታር በእሳት ዛንጀር ሰቅሎታል። ስለዚህ ቅዱስ መስቀልን ሲመለከት ዲያብሎስ መሸነፉን መዋረዱን ያስባል። በመስቀል አምሳል ስናማትብ የድል ምልክት ነውና አፍሮ ፈርቶ ይርቀናል።

4.5.1.2.6 <u>ስናማትብ ስለ እኛ የተሰቀለው የመድኃኒዓለም ክርስቶስ ተከታዮች መሆናችንን እንመሰክራለን።</u>

በመስቀል አምሳል ስናማትብ፣ መስቀሉን በአንገታችን አስረን በልብሳችን ጠልፈንና ለብሰን ስንታይ ክርስቶስን ማመናችንን እንመሰክራለን። "በሰው ፊት ለመሰከረልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ"(ማቴ 10፥32)

4.5.2 <u>ደጃፉን መሳለም</u>

ደጃፉን የምንሳለምበት ምክንያት

ሀ. ቤተ መቅደሱን እንዲሁም በውስጡና በዙሪያው ያለውን የነካ ስለሚቀደስበት ዘጸ **40፥9**

ሕንፃ ቤተክርስቲያኑ ደጃፍ በቅብዐ ሜሮን የከበረ የተቀደሰ ስለሆነ የሚሳለመው፣ የሚስመው የሚደባበሰው ሁሉ ይቀደስበታል።

ለ. ቤተ መቅደስ የክርስቶስ ማደሪያ ስለሆነ

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል፣ ዘርፍ፣ ልብሱ መቅደሱ ናት። ኤፌ 5፥23። አካል ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ያለውን ሁሉ እንደሚይዝ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት ሲባል የቤተክርስቲኑን አካል ሁሉ ያጠቃልላል። ስለዚህ አካሉ የሆነችውን ይህችን ቤተክርስቲያን መሳለም የጌታችንን የልብሱን ዘርፍ በመንካቷ እንደ ተፈወሰችው ሴት የእምነት ጥንካሬ ምልክት ነው። በእምነት ለሚሳለም በእምነት ለሚኖር ሰው የቤተክርስቲያን ደጃፎቿ፣ ዐጸድዋ፣ በቅጽረ ቤተክርስቲያን ያለው ጠበል፣ አጥሩ ቅጥሩ ውስጡ ውጭው ሁሉ ፈውስና መድኃኒት ይሆንዋል።

ሐ. ቤተ መቅደሱ የመለኮት ማደሪያ ስለሆነ

ቤተክርስቲያን (ቤተ መቅደስ) የመለኮት ማደሪያ ናት። በሰማይ በክብር የሚኖር እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱ በረድኤት ያድራል ቤተ መቅደሱን የክብሩ መግለጫ አድርጎታልና "አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁምና፤ ዐይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ" (2 ዜና 7፥16)፤ "ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን" (መዝ 131፥7) እንዲል ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነም ደጃፍ አጥሩ ቅጥሩ ሁሉ የተቀደሰ በበረከት የተሞላ ነው። ስለዚህ ወደ ቤተ መቅደሱ የሚቀርብ ሰው ይኸን እያሰበ ይሳለመዋል።

ስለዚህም ሰው ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን ደጀ ሰላሟን (ደጃፏን) "ሰላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም ቅድስት፤ ቅድስት የምትሆን የሰማያዊት ኢየሩሳሌም አምሳል የሆንሽ ቤተክርስቲያን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል" እያለ ሊሳለም ይገባዋል።

4.6 <u>በቤተ መቅደሱ (በሕንፃው) ፊት መሰገድ</u>

ወደ ቤተ መቅደስ ለጸሎት የሚገባ ሰው ደጃፉን ከተሳለመ በኋላ በቤተ መቅደስ ለእግዚአብሔር የአምልኮት (የባሕርይ) ስግደት ሊሰግድ ይገባዋል።

4.6.1 <u>ለቤተ መቅደስ ስግደት እንዲገባ</u>

እሥራኤል ዘሥጋ ከመሪያቸው ከሊቀ ነቢያት ሙሴ ጋር የአምልኮ ሥርዓታቸውን በሚፈጽሙበት በደብተራ ኦሪት ፊት ለፊት ተንበርክከው ይሰግዱ ነበር። ምክንያቱም የደመናው ዓምድ እግዚአብሔር የመገለጡ ምልክት ድንኳኑም የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ማደሪያ ነውና። ዘጸ 33፥7

ንጉሡ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ ታቦቱን ከድንኳን አውጥቶ ወደ መቅደስ ባስገባ ጊዜ ቤተ መቅደሱ በእግዚአብሔር ብርሃን ተሞላ ሕዝቡም ሁሉ በቤተ መቅደሱ ፊት ሰግደዋል። "የእስራኤልም ልጆች ሁሉ እሳቱ ሲወርድ የእግዚአብሔርም ብርሃን በቤቱ ላይ ሲሆን ያዩ ነበር፤ በወለሉም ላይ በግምባራቸው ወደ ምድር ተደፍተው ሰገዱ" 2 ኛ ዜና 7፥3

2 ሳሙ 12፥ 20 "ዳዊትም ከምድር ተነሥቶ ታጠበ፣ ተቀባም ልብሱንም ለወጠ፤ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ገብቶ ሰገደ።" ተብሎ እንደተጻፈ ቅዱስ ዳዊት ቤተ እግዚአብሔር አምላክ በክብር በረድኤት የሚገለጥበት ልዩ ስፍራ መሆኑን ዐውቆ ግንባሩንና ጉልበቱን መሬት አስነክቶ ሰግዷል።

"እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትን እገባለሁ፤ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ" መዝ 5፥7 "ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን።" መዝ 131፥7 "በመላእክት ፊት እዘምርልሃለሁ። ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ" መዝ 137፥2

ምዕራፍ አምስት

5. በቤተ ክርስቲያን የተከለከሉ ነገሮች

5.1 ጫማ አድርጎ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ክልክል ነው

ቅዱሳት መጻሕፍት በተቀደሰ ቦታ ስንቆም ጫማችንን ማውለቅ እንዳለብን ይነግሩናል ዘጸ 3፥5፣ የሐዋ 7፥39 ፍትሐ ነገ ፍት መን አንቀጽ 12፥12 ሙሴ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን ትቶ ከግብፅ ተነሥቶ ወደ ምድያም አገር ሔደ፤ በዚያም ኖረ። እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን ሊጠብቅ እንዳለው ሊያስተምረው የበጎች እረኛ አደረገው። በደብረ ሲና ሐመልማልና ነበልባል በተዐቅቦ ተዋሕደው ተመለከተ። በዚያም ሥፍራ ከነጫማው እንዳይቆም "አንተ የቆምክበት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ" አለው። ዘጸ 3፥5። በዚህም ከእግረ ሥጋው ላይ ጠፍሩን እንዲፈታ፣ ከእግረ ልቡናውም የዮቶርን ምሥጢር (ልማድ፣ ጥንቆላ) እንዲያጠፋ ተናገረው እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ሊልከው ሽቶ ነው። ነቢዩ በዚህ ቃል የታዘዘውን ለመፈጸም በአፍአ የሚታየውን በእግሩ የተጫማውን ጫማ አወለቀ። እንዲሁም በልቦናው ነግሦ የነበረውን ልማደ ዮቶርንና ተጥባበ ግብፅን አስወገደ።

ሙሴ ሐመልማሉ ከነበልባሉ ተዋሕዶ ሲነድ ያየበት ደብረ ኮሬብ የተቀደሰ ስፍራ እንደሆነ ሁሉ የእግዚአብሄር ቤት የሚታነፅበት ቦታ ሁሉም ቅዱስ ነው። "አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁም" እንዲል 2 ዜና 7፥04

ስለዚህ መሥዋዕት ወደሚሠዋበት፣ ቃለ እግዚአብሔር ወደሚነገርበት፣ ታቦተ ሕጉ ወዳለበት፣ ቅዱሳን መላእክት ወደሚዘምሩበት ቅዱስ ሥፍራ ስንቀርብ በውስጡ የታጠቢአትን ጫማ በአፍዓም የእግራችንን ጫማ ማውለቅ ይገባናል።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ በውስጥ በልቦናችን ክፋትና ቂም በቀል ካለን ያንን አርቀን በተጨማሪም በውጭ በእግራችን ተጫምተነው የሚታየውን ጫማም አውልቀን መቅረብ ይኖርብናል።

5.2 ለሃጩን የማዘረብረብ ነውር (ልጋግ) ያለበት ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም

5.3 በቤተ ክርስቲያን ዐጸድ ሥጋዊ ግብዣ ማድረግ አይገባም

መሥዋዕት በሚሠዋበት የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት አካባቢ በቤተ መቅደሱ አቅራቢያ ግብዣ አድርጎ እየበሉና እየጠጡ መገኘት ሥርዓትን ማፍረስ ነው። ፍት ነገ ፍት መን አን 1

5.4 የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ንዋያተ ቅዱሳትን ለግል አገልግሎት ማዋል አይገባም

ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸው እያንዳንዳቸው ንዋያት የተለዩና የተቀደሱ ናቸው። ዘጸ 40፥9 እነዚህ የተቀደሱ ንዋያት ቅዱስ ለሆነ እግዚአብሔር ለአገልግሎት ማቅረቢያነት በቤተ መቅደስ ይቀመጣሉ። አስፈላጊ በሆነ ሰዓትና ወቅት ካህናት ያገለግሉባቸዋል። ከዚህ ውጪ ግን ንዋያቱን ከቤተ መቅደስ አውጥቶ ለግል አገልግሎት ማዋል፣ በቤታችን፣ በሰርግ ቤቶችና በሌሎች የድግስ ቦታዎች መጠቀም የተከለከለ ነው። ከበሮው፣ ጸናጽሉ፣ መቋሚያው፣

ሌሎችንም የቤተ መቅደስ ንዋያት ሁሉ ለአገልግሎት ካልሆነ በቀር (ለጥምቀት፣ ለፍትሐት ወዘተ) ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ማውጣት አይገባም።

ለቤተ ክርስቲያን መባዕ ሆኖ የተሰጠ ሁሉ ለግለሰብ መጠቀሚያ (መነገጃ) መሆን የለበትም፣ በአራጣ ማበደር፣ በወርቁ መጠቀም በንዋያቱ ፈትፍቶ መብላትና መጠጣት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው። ዳን 5፥25-31

ፍትሐ ነገሥትም በፍትሕ መንፈሳዊ ክፍሉ "ከቤተ ክርስቲያን ከተባረከ ዕቃ ወገን የሆነውን ሁሉ የወርቅና የብር ዕቃም ውጪ ሰው በቤቱ ውስጥ ሊሠራባቸው አይገባውም። ይህ ሕግን ማፍረስ ነውና። ይህንን ያደረገ እንደሆነም ከተፈረደበት በኋላ ከቤተክርስቲያን ይለይ።" ይለናል ፍትሐ ነገ አንቀጽ 1 ለስጣ 28

5.5 <u>በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ገበያ መገበያየት አይገባም</u>

ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በረከት የሚሸምቱባት ጸልየው፣ ሰግደው፣ መጽውተው ከፈጣሪያቸው ዋጋ የሚቀበሉባት የምሕረት አደባባይ ናት። በዚህች ቅድስት አደባባይ መጸለይ፣ መቁረብ፣ ቃለ እግዚአብሔርን መስማት፣ መዘመር እንጂ ሥጋዊ ንግድ መነገድ አይፈቀድም። "ለሻጮችና ለለዋጮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገበያየት አይገባቸውም" (ፍት. መን. አን 1)

5.6 <u>በቤተ መቅደስ በማኅበር ጸሎት ወቅት የግል ጸሎት ማድረስ ክልክል ነው</u>

5.7 <u>በቤተ መቅደስ በቅዳሴ ሰርዓት አቋርጦ መውጣት ክልክል ነው</u>

5.8 <u>ሴት ልጅ በወር አበባ ወቅት ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት አይፈቀድላትም</u>

ሴት ልጅ በወር አበባ ወቅት ወደ ቤተ መቅደስ አትገባም። ይህ የሆነው እንደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት የወር አበባን እንደ መርገም ቆጥሮ የተረገመች የረከሰች ናት በማለት አይደለም። የሐዲስ ኪዳን ሴቶች ከድንግል ማርያም በተወለደው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቀድሰዋል በዚህ የተነሣ የወር አበባ የዘር፣ ፍሬ የማፍራት ምልክት እንጂ የመርገም ምልክት አይደለም። ፍትሐ ነገ አን 14፥563 ከዚህ ውጭ ግን በዚህ ወቅት እንዳትገባ የተከለከሉባቸው ምክንያቶ አሉ።

ሀ. <u>በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት</u>፡- በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በወር አበባ ወቅት ሴት ልጅ ወደ ቤተ መቅደስ እንድትገባ አይፈቀድላትም (ዘሌ 12፥15-28)

ለ. <u>ሥጋ ወደሙን መቀበል ስለማትችል</u>፡- በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወደ ቤተ መቅደስ የሚገባ ምእመን የሚገባበት አንዱ ምክንያት ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን ለመቀበል ነው። ለመቁረብ ወይም በሌላ መልኩ በረከት ለመሳተፍ ደግሞ ከፈሳሽ ነጻ መሆን ያስፈልጋል። በማንኛውም ምክንያት ከሰውነቱ ፈሳሽ የሚፈሰው ሰው ለመቁረብ አይፈቀድለትም። ይህም ስለ ሥጋውና ደሙ ክቡር ነው። ስለዚህ ሴት ልጅ በወር አበባዋ ወቅት በሚፈሳት ፈሳሽ ምክንያት መቁረብ ስለማትችል ወደ ቤተ ክርስቲያን አትገባም።

እውነታው ይህ ሆኖ እያለ "በወር አበባ ወቅት የጸሎት መጻሕፍት ይዛ በቤቷ መጸለይ፣ በሥዕላት ፊት ቆማ ጸሎት ማድረስ፣ ከካህናት ዘንድ ቀርባ መስቀል መሳለም አይፈቀድላትም" የሚል አመለካከት ያላቸው አሉ። ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው በዚህ ወቅት ቤተ መቅደስ አትገባም እንጂ በቤቷ ወይም በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ዙሪያ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዛ መጸለይ፣ ማስቀደስ፣ መስቀል መሳለም አትከለከልም።

5.9 <u>የሌሊት ልብስ ወይም የአረማውያን ልብስ ለብሶ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት የተከለከለ ነው።</u>

የሌሊት ልብስ በተለያየ ሁኔታ ሊቆሽሽ ይችላል። ይህን ልብስ ለብሶ ለቅዳሴ ወይም ለጸሎት ቤተ መቅደስ መግባት አይገባም። በሌሊት ልብስ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ለቤተ ክርስቲያን የምንሰጠው ክብር አነስተኛ አድርጎ የሚያሳይብንም ነው። ቤተክርስቲያን የንጉሥ እግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነች ወደ እርሷ ስንመጣ በውስጥም በውጭም ተዘጋጅተን የሚገባንን ልብስ ለብሰን መገኘት ይገባናል እንጂ ባልተገባ አለባበስ መቅረብ የለብንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ሰውነትን መታጠብ፣ ንጽሕናን መጠበቅ ይገባል። የተቀደደና ያደፈ ልብስ ለብሶ መሄድ ክልክል ነው በችግር ምክንያት ካልሆነ በቀር ረዘም ያለና ንጹሕ ልብስ ለብሶ መሄድ ያስፈልጋል። ዘፍ 9፥21-27 ዘሌ 19፣10-11፥ 1 ቆሮ 11፥5-14 የአረማውያንን ልብስ ለብሶ ማስቀደስም ከሥርዓት ውጭ መሆን ነው። አረማውያን የሚለብሱት ልብስ ራሱን የቻለ ባሕልና ትርጉም ያለው በመሆኑ ይህንን ልብስ ለብሰን ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት አይገባንም።

5.10 <u>ወንድ ልጅ ሕልመ ሌሊት (ዝንየት) ከመታው በዕለቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገባም</u>

ወንድ ልጅ በመኝታው ሰዓት ሕልመ ሌሊት (ዝንየት) ካገኘው ማለትም ከሰውነቱ ዘር ከፈሰሰ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገባም። (ዘሌ 15፥2-18) በተለያየ ምክንያት ዘር በፈሰሰው ዕለት በአፍዓ (በውጭ) ካልሆነ ገብቶ እንዲያስቀድስ አይፈቀድለትም። በማግሥቱ ግን ገላውን ታጥቦ ይገባል።

5.11 <u>ባልና ሚስት ከተራክቦ በኋላ ዕለቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት አይፈቀድላቸውም</u>

“ጋብቻ ቅዱስ መኝታውም ንጹሕ“ ቢሆንም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ከተራክቦ በኋላ ዕለቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት አይፈቀድም። ቅዱስ ጳውሎስ “ለጸሎት በመፈቃቀድ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት አይከላከሉ“ እንዳለ ባልና ሚስት ከተራክቦ የሚርቁት በበዓላት፣ በአጽዋማት፣ ለጸሎትና ለቅዳሴ በሚዘጋጁባቸው ዕለታት ነው። 1 ቆሮ 7፥5፤ ኩፋ 34፥12፤ ዘጸ 19፥15 ከተራክቦ በኋላ ግን ቤተ ክርስቲያን መግባት አይፈቀድላቸውም።

5.12 <u>በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሳቅ፣ መሳለቅ፣ ዋዛ ፈዛዛ ነገር መነጋገር ክልክል ነው</u>

ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት የሚገባ ሰው ከገባ በኋላ በዝምታ፣ በጸጥታ፣ በፍርሃት ሆኖ የእግዚአብሔርን ምሕረት መሻት ይገባዋል። ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን መላእክት ዝማሬ የሚቀርብበት፣ ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት፣ የነቢያት ትንቢት የሐዋርያት ስብከት የሚሰማበት በመሆኑ በዚህ ቦታ ሐሜት፣ ጮሆ መነጋገር፣ መሳቅ መሳለቅ አይገባም። ሊቃውንት ስለዚህ ነገር ብዙ ብለዋል። “በምድራዊ ንጉሥ ፊት በቆምህ ጊዜ በምንም ምክንያት ቢሆን ለመሳቅ አትደፋፈርም። ታዲያ በሰማያዊ ንጉሥ ነገሥት ፊት ትስቃለህን“ ብሏል። ዮሐ.አፈ.አን 6

በቀኖና መጻሕፍትም “በቅዳሴ ጊዜ የሚስቅ ዓለማዊ ቢሆን ወደ ውጭ ያውጡት ከቅዱስ ምሥጢር (ከቁርባኑ) አያቀብሉት ተብሏል።“ (ቀኖና ባስ አን 79)

5.13 <u>አብዝቶ ጠጥቶና ሰክሮ መግባት ክልክል ነው</u>

“እንዳትሞቱ ወደ መገናኛው ድንኳን ስትገቡ አንተና ልጆችህ የወይን ጠጅና የሚያሰክርን ነገር ሁሉ አትጠጡ“ ዘሌ 10፥8-10 የእግዚአብሔር ቤት የመንፈሳዊ መብልና መጠጥ መገኛ ነው። ወደዚህ ቤት የሚገባ ካህንም ሆነ ምእመን ሰውነቱን በንጽሕና ሊጠብቅ ይገባዋል። መጠጥ አብዝቶ ጠጥቶ በስካር መንፈስ መቅረብ የለበትም ይህን ካደረገ አብረውት የታደሙ ምእመናንና ካህናትን በማይሆን ጠረን ይረብሻል። ጎሊናቸውን ሰብስበው እንዳይጸልዩ ያደርጋል። ከሁሉም በላይ በቤተክርስቲያን አድሮ የሚመሰገን እግዚአብሔርን ያሳዝናል።

ስካር ሰዎች ወደ ሕይወታቸው ወደው ከሚጋብዟቸው የፈቃድ እብደቶች አንዱ ነው። ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁንና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከስካር እንድንጠበቅ አስተምሮናል። ሉቃ 21፥34

5.10.4 <u>በቂም በቀል ሆኖ ሰውን አስቀይሞ የሰውን ገንዘብ በማጭበርበር ወስዶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ መጸለይ ክልክል ነው።</u>

በቤተ ክርስቲያን በቅድመ እግዚአብሔር ለጸሎት ስንቆምና ለአገልግሎት ስንተጋ ፍቅረ እግዚአብሔርንና ፍቅረ ቢጽን በመፈጸም ሊሆን ይገባል። ሰውን ማስቀየም፣ የሰውን ገንዘብ ማጭበርበር፣ ቂመኛነትና በቀለኛነት ደግሞ “ባልንጀራን እንደ ራስ አለመውደድ“ ነው ማቴ 5፥23-24፣ ማር 11፥25፣ ሉቃ 18፥9-14 በመሆኑም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎትም ይሁን ለአገልግሎት ከመግባታችን በፊት ከተጣላነው መታረቅ፣ የቀማነውን መመለስ፣ የበደልነውን መካስ ይኖርብናል።

<u>ምዕራፍ ስድስት</u>

6. <u>የንዋያተ ቅድሳት ምሥጢራዊ ትርጉም የአቀማመጥና የአጠቃቀም ሥርዓት (በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአገልግሎት የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት)</u>

ንዋያተ ቅድሳት፡- ከሁለት የግእዝ ቃላት የተገኘ ነው። ንዋይ ዕቃ ማለት ሲሆን፤ ቅዱስ ማለት ደግሞ ልዩ፣ ክቡር፣ ምርጥ ማለት ነው። ንዋያተ ቅድሳት ማለትም በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮትን ሥርዓት ለመፈጸም የሚያገለግሉ "የተቀደሱ የቤተ እግዚአብሔር ዕቃዎች፣ ንዋያተ ቤተ እግዚአብሔር" ናቸው። እነዚህም ከሌሎች ዕቃዎች የተለዩ፣ የተመረጡ፣ ወይም የከበሩ ዕቃዎች ናቸው። 1ኛ ዜና 24፥19፣ 28፥12 በቤተ ክርስቲያን በሚፈጸሙት ጸሎታት ላይ ለአገልግሎት የሚውሉት ንዋያተ ቅድሳት የየራሳቸው የሆነ ስምና የአገልግሎት ድርሻ አላቸው ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን።

6.1 ቃጭል፡-

ከብረት፣ ከብር፣ ከመዳብ፣ ከነሐስ ከሌሎችም ማዕድን ነክ ነገሮች የሚሠራ ከደወል ያነሰ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካህናት ለአገልግሎት የሚጠቀሙበት ነው። በቅዳሴ ጊዜ የሚቃጨልና ድምፅ የሚሰጥ ንዋይ ነው። ድምፁ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ /ማቴ 3፥12/ የሚለው የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ስብከትና በዕለተ ዓርብ በእግረ መስቀሉ ስር ሆኖ ያለቀሰው ወንጌላዊው ዮሐንስ ለቅሶ ምሳሌ እንደሆነ ሊቃውንት ያስተምራሉ።

6.1.1 ቃጭል የሚመታባቸው ጊዜያትና የሚመታበት ምክንያት

ሀ. ቀዳስያን ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ

መጀመሪያ ላይ ዲያቆናቱ መሥዋዕቱን አክብረው ንፍቀ ቄስ ጽናሐ ይዞ እያዜሙ ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ሲጓዙ ቃጭል ይመታል። በዚህ ጊዜ የሚመታው አንድም ቅዳሴ መግባታቸውን ለማሳወቅ ዳግመኛም "ሰው አምላክ ሆነ፤ አምላክ ሰው ሆነ የሚለውን የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት ለማሰብ ነው" ዮሐ 1፥14 "ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን" ማለት "የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ" ማለት ነው። ወንጌል ከተነበበና የዕለቱ ስብከት ከተሰበከ በኋላ ዲያቆኑ ቃጭል እየመታ "ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን" ብሎ ያውጃል።

ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት "ደሙን ለመቀበል ያልበቃችሁ ወደ ክርስትና ለመመለስ (ለመጠመቅ) አስባችሁ ትምህርቱን ያላጠናቀቃችሁ ውጡ" ሲል ነው። የሚቀጥል ነው እንጂ ካደጉ በኋላ ክርስቲያን ለመሆን የሚመጡ ምእመናን እስኪጠመቁ ድረስ ሁለትና ሦስት ዓመት እየተማሩ ሊቆዩ ስለሚችሉ በዚህ ጊዜያችው ያልተጠመቁ፣ ምሥጢረ ቁርባንን ያልተረዱ በመሆናቸው "ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን" እስኪባል ድረስ አስቀድሰው ትምህርቱን ሰምተው "ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን" ከተባለ በኃላ ይወጣሉ።

ሐ. በእግዚአታ ጊዜ

ሠራኢ ካህኑ እየመራ ሕዝቡ እየተቀበለ እግዚአታ በሚደርስበት የቅዳሴ ሰዓት ንፍቅ ዲያቆን ከመጋረጃ ውጭ ሆኖ ቃጭል ይመታል። በዚህ ጊዜ የሚሰማው የቃጭል ድምፅ የሐዋርያት ለቅሶ ምሳሌ ነው። አባቶቻችን ሐዋርያት ጌታ ተሰቅሎ ባዩት ጊዜ "በደል ሳይኖርብህ ለሰው ብለህ በሥራ ሥስቱን ሕማማተ መስቀል ተቀበልህ፤ ለእኛ ስትል ሞትህ" እያሉ አልቅሰዋል።

6.2 ሰን /መቁረርት /ኩስኩስት/

ቁረ፡- ቀዘቀዘ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ቆሪሪ፣ በራድ ማለት ይሆንና መቁረርት፣ ማቁረሪያ፣ ማብረጃ፣ ማቀዝቀዣ የሚል ትርጉም ይሰጠናል። ይኸውም መለኮት የተዋሐደውን ነፍስ የተለየውን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ገብቷቸውና ተገብቷቸው የተቀበሉ ምዕመናን በጥርሳቸው በትናጋቸው እንዳይቀርና እንዳይነጥብ ከአፋቸው ለቅልቀው ጠርገው የሚያወርዱበት ቅዳሴ ጠበል ስለሚሰጥበት ነው። ሰን ካህኑ በቅዳሴ ጊዜ እኔ

በሃጢያታችሁ ንፁህ ነኝ በማለት እጁን ሲታጠብ የሚጠቀምበት ማንቆርቆሪያ ነው። በብሉይ ኪዳን አሮንና ልጆቹ ወደ መገናኛው ድንኳን ሲገቡ የሚታጠቡት መቁረርት ከነሐስ እንዲሠራ ሙሴ ታዝዞ ነበር ሙሴም በታዘዘው መሠረት በነሐስ አሠርቶ ዘይት ቀብቶ ይጠቀሙበት ነበር። ዘጸ 30፣17

በሐዲስ ኪዳን መቁራሪት በቅዳሴ ጊዜ ለተለያዩ አገልግሎት ይውላል። በቅዳሴ ጊዜ ካህኑ ሲናጸ እጁን ይታጠብበታል። ይኸም "እኔ ከደሙ ንጹሕ ነኝ" ብሎ ጲላጦስ የታጠበበት ምሳሌ ነው። ማቴ 27፣17 ጲላጦስ ራሱን ንጹሕ እንዳደረገ ካህኑም ንሰሐ ሳትገቡ፣ የበደላችሁትን ሳትክሱ የቀማችሁትን ሳትመልሱ ወደዚህ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ብትቀርቡ ሳይገባችሁ ተቀብላችሁ በሚኖርባችሁ ፍርድ በሚመጣባችሁ ዕዳ፣ በደል ንጹሕ ነኝ ለማለት ይታጠባል በሌላ በኩል ሰን /መቁረሪት/ ኩስኩስት/ በስሙነ ሕማማት ባለው በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ባለው አገልግሎት ጌታችን የሐዋርያት እግር ያጠበበት የጥምቀት ምሳሌ ይሆናል። ዮሐ 13፣5

6.3 ብርት

ከነሐስ ወይም ከሌሎች ብረቶች የሚሠራ የእጅ መታጠቢያ የሚሆን ሳህን ነው። በብሉይ ኪዳን ከላይ ካየነው ከመቁረርት ጋር በአንድነት ሆኖ ለማስታጠቢያነት ያገለግል ነበር በሐዲስ ኪዳንም በቅዳሴ ጊዜ ካህኑ ወደ አገልግሎት ወይም ወደ ቅዳሴ ሲገባ እጁን ሲታጠብ ይታጠብበታል። በሰሙነ ሕማማት በጸሎተ ሐሙስ ከቅዳሴው ቀደም ብሎ ካህኑ የምእመናንን እግር የሚያጥበው በዚህ በብርት ነው።

6.4 ጽንሐሕ - የዕጣን ማጠኛ ማለት ነው

እግዚአብሔር ሙሴን ቁመቱን ሁለት ክንድ፣ ስፋቱን አንድ ክንድ ከስንዝር ቅርጽ አድርገህ እንደ ሙቀጫ ፈልፍለው የምትፈለፍለው እንጨት ሽሞሽር ሽጢን የሚባል የማይነቅዝ እንጨት ነው። ከዚያም በውስጥና በውጭ በወርቅ ለብጠው፣ አራት ቀለበት ሁለት መሎጊያም አብጀለት። በግራና በቀኝ ሁለት አቅርንት /መሎጊያ/ አውጣለት። ስንደርስ የሚባል ነጭ ዕጣን ፈጭተህ አኑር አግብተህ ዕጣኑን አድርገህ በወርቅ ዘንግ አዋሕደው የጢሱ ቅታሬ አምሮ እንዲወጣ ወርቁን እንዳይሰማው ፈጥነህ ብረት ድፋው ብሎት ነበር ዘጸ 30፥6-10፤ 37፥25-29

ይኸም ምሳሌ ነው፤ ማዕጠንት የእመቤታችን፣ የተለበጠው ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ ዕጣኑ የትሰብእት /የሥጋ/፣ ፍሕም የመለኮት፤ የወርቅ ዘንግ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፤ የከፈለ፣ የፈጠረ፣ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና። አቅርንት የሥልጣነ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።

በሐዲስ ኪዳንም ጽንሐሕ የዕጣን መሥዋዕት ይቀርብበታል። ካህኑ እጀታውን ይዞ መንበረ ታቦቱን፣ ቅድሳት ሥዕላቱን የቤተ መቅደሱን ዙሪያ፣ መሥዋዕቱን ወዘተ ያጥንበታል።

6.4.1 የጽንሐሕ የተለያዩ ክፍሎችና ምሳሌያዊ ትርጉማቸው

ጽንሐውን ስንመለከት የምናያቸው እያንዳንዳቸው ክፍሎች ራሱን የቻለ መሥጢራዊ ትርጉም አላቸው።

1. ሙዳይ የሚመስለው የጽንሐሕው ክፍል

ይኸ ዕጣንና እሳቱ የሚዋሐዱበት ሙዳይ የመሰለ ክፍል ነው። ከላይ ክዳን አለው እርሱም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ምሳሌ ነው። እሳቱ በዚህ ክፍል ተቀምጦ ጽንሐውን እንደማያቃጥለው እመቤታችንም እሳተ መለኮትን በማኅፀኗ ተሸክማው አላቃጠላትም።

2. <u>የሙዳዩ መክደኛ</u>

ይኸ ክዳን በላዩ ላይ መስቀል አለበት ይህም ከመስቀሉ ጋር በአንድነት የቀራንዮ ምሳሌ ነው። በቀራንዮ ኮረብታ የተተከለውን መስቀል በኅሊናችን እንድንሥል ያደርገናል። ገላ 3፥1

3. <u>በመካከል የሚገኝ አንድ ዘንግ</u>

በሦስቱ ዘንጎች መካከል የሚገኝና ከታች በክዳኑ ላይ ከሚገኘው መስቀል ጋር የሚገናኝ ዘንግ ነው። ይኸ ዘንግ የቅድስት ሥላሴ የአንድነታቸው ምሳሌ ነው፤ ዘንጉ ከላይ ወደ ታች መውረዱ ቃለ እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር በተለየ አካሉ በተወላዲነት ግብሩ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ የመወለዱ የመሰቀሉ የመሞቱ ምሳሌ ሲሆን ከታች ወደ ላይ መውጣቱ ደግሞ ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ የመነሣቱና የማረጉ ምሳሌ ነው። በመቀጠል ከላይ ወደ ታች መውረዱ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሳው ሥጋ ዳግመኛ ለፍርድ ሊመጣ እንዳለው ያመለክተናል። በአጠቃላይ ይኸ ዘንግ የቅድስት ሥላሴን አንድነት፣ የእግዚአብሔር ወልድን ከልዕልና ወደ ትሕትና መውረድና ዘሮ ማስተማር፣ መሰቀሉን፣ ከሙታን ተለይቶ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱንና ማረጉን የሚያዘክር ነው።

4. <u>ሻኩራዎችን የያዙ ሦስት ዘንጎች</u>

በመካከል ያለውን ዘንግ ከብበው ያሉና በላያቸው ሻኩራዎችን የያዙ ሦስት ዘንጎች ናቸው። እነዚህ ሦስት ዘንጎች እግዚአብሔር በመለኮት፣ በሕልውና አንድ ቢሆንም በስም፣ በግብር፣ በአካል ሦስት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። መካከለኛውን ዘንግ አይተን አንድነቱን ስናስብ በዚያው ያሉትን ሦስቱን አይተን ደግሞ ሦስትነቱን እናስባለን።

5. <u>በሦስቱ ዘንጎች ላይ የሚገኙ ሻኩራዎች</u>

እነዚህ ሻኩራዎች በቁጥር ዐሥራ ሁለት ወይም ሃያ አራት መሆን አለባቸው። ዐሥራ ሁለት ሲሆኑ የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ሃያ አራት ሲሆኑ ደግሞ የሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌ ናቸው። ጽንሐው ሲወዛወዝ ሻኩራዎቹ ድምፅ ይሰጣሉ። ይኸ ድምፅ ደግሞ ሻኩራዎቹ ዐሥራ ሁለት ከሆኑ “ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ“ /መዝ 18፥1-4/ ተብሎ የተነገረላቸውን የቅዱሳን ሐዋርያት ስብከት ያስታውሰናል።

ሻኩራዎቹ ሃያ አራት ከሆኑ ደግሞ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በሰማይ የሚያሰሙት የምስጋና ድምፅ “ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ“ እያሉ የሚያመሰግኑት ምስጋና ምሳሌ ነው። ራእ 4፥7

6. <u>ድምፅ የሚያሰሙ ሽቦዎች</u>

በተራ ቁጥር (1) እንዳየነው ሙዳዩ የእመቤታችን ማኅፀን ምሳሌ ሲሆን ከሙዳይ ውስጥ የሚገኘው ፍሕም ደግሞ በማኅፀኗ ያደረው የእሳተ መለኮት ምሳሌ ይሆናል።

6.5 <u>ሙዳይ</u> - በቁሙ መኖሪያ፣ መጨመሪያ፣ መክተቻ ሲሆነ የዕጣን ማስቀመጫ /ማቅረቢያ/ ነው። ምሳሌነቱ የእመቤታችን ሲሆን በውስጡ ያለው ዕጣን ደግሞ የጌታ ምሳሌ ነው ካህኑ ቅዳሴ ጊዜ ፍሬ ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት አምስት የዕጣን እራፊ /ቆቀሮችን/ መርጦ ያስቀምጣል። እነዚህ አምስት ዕጣኖች የአምስቱ ኪዳናት ምሳሌ ናቸው።

እነዚህም ኪዳናት ቁርባን አቤል፣ መሥዋዕተ ኖኅ፣ ኂሩተ አብርሃም፣ መብዐ ይስሐቅ፣ ተልእኮ ሙሴ ወአሮን ናቸው። (መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው)

6.**6** <u>መሶበ ወርቅ</u> - መሥዋዕቱ ከቤተልሔም ወደ መቅደሱ የሚወጣበት ነው። መሶበ ወርቅ ከስንደዶ፣ ከአክርማና ከአለላ፣ ከወርቅ ከብር ከሌሎችም ማዕድናት የሚሠራ ነው። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

6.7 <u>ጻሕል</u> - ከወርቅ፣ ከብረትና ከብር የሚሠራ የጌታችን ሥጋ የሚሠዋበት በታቦቱ ላይ የሚቀመጥ የተቀደሰ ንዋይ ነው። ጌታችን የተወለደበት የከብቶች በረት አንድም የእመቤታችን የማኅፀኗ ምሳሌ ነው።

6.8 <u>ጽዋዕ</u> - ዲያቆኑ የጌታችንን ክቡር ደሙን የሚያቀብልበት ንዋይ ነው። ጽዋዕ የጌታችን ገቦ (ጎን) ምሳሌ ሲሆን ጌታችንን ጎኑን በወጉት ጊዜ ደሙ እንደ ፈሰሰ ዲያቆን የጦር ምሳሌ በሆነ ዕርፊ መስቀል ወደ ጽዋው በጠለቀ ጊዜ ክቡር ደሙን ይዞ ይወጣል። አንድም የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ከጽዋው የጌታን ደም እንደሚቀዳ ከእመቤታችን ነስቶ ገንዘብ በአደረገው በውኃዛ ደሙ ዓለሙን ያዳነው ጌታችን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ተገኝቷል። አንድም በዕለተ ዓርብ ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት በብርሃን ጽዋዕ ደሙን ተቀብለውታል።

ጽዋው የሚሸፈንበት ልብስ አይሁድ ጌታችንን በኩርኩምና በጥፊ ሲመቱት ዐይኑን የሸፈኑበት (ያሰሩበት) ጨርቅ ምሳሌ ነው።

6.9 <u>ዕርፊ መስቀል</u> - ዕርፍ፣ ጨለፈ፣ ቀዳ፣ ጠለቀ ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው። ጌታችን በመልዕልተ መስቀል ያፈሰሰው ክቡር ደም ከጽዋው እየተቀዳ ለምእመናን ስለሚሰጥበት ይኸ ስም ተሰጥቶታል። ማንኪያ ዓይነት የሆነ የክርስቶስን ደም ለማቀበል የሚያገለግል ንዋይ ቅዱስ ነው። ዲያቆኑ ደሙን በሚጠልቅበት በጽዋው በኩል ጉድጉድ ያለ ሲሆን ከላይ እጀታው ደግሞ በመስቀል ቅርጽ የሚሠራ ነው።

በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ የተገለጸው መልአኩ ይዞት የታየው ጉጠት የዕርፊ መስቀል ምሳሌ ነው። በዚህ ምዕራፍ መልአከ እግዚአብሔር ከመሠዊያው ላይ ፍሕም በጉጠት ይዞ የኢሳይያስን ከንፈር እንደ ዳሰሰና ከለምጹ እንዳነጻው ተጽፏል። ኢሳ 6፥6-8 ዕርፊ መስቀል ሌንጊኖስ የጌታችንን ጎን የወጋበት ጦር ምሳሌ ነው።

6.10 <u>ዐውድ</u> - ቀጥተኛ ትርጉሙ አደባባይ ማለት ነው። ከብረት ከነሐስ የሚሰራና በድርገት ጊዜ ጻሕሉ የሚቀመጥበት ሰፋ ያለ ሳህን ነው። ሥጋው እንዳይነጥብ (እንዳይወድቅ) መጠበቂያና ሰፋ ጎላም ከበርም ብሎ እንዲታይ ለማለት የተደረገ ነው። ይኸ ቅዱስ ንዋይ አይሁድ ጌታችንን ለመያዝና ለመስቀል ሸንጎ ያደረጉበት አደባባይ ምሳሌ ነው።

6.11 <u>አጎበር</u> - ከብረት ወይም ከእንጨት የሚሠራና በድርገት ጊዜ በዐውዱ ላይ የሚደፋ አራት ማዕዘን የሆኑ ሦስት እግሮች ያሉት ንዋይ ነው። የማኅተመ መቃብር /የመቃብር መክደኛ/ ምሳሌ ነው። እግሮቹ ሦስት መሆናቸው የቅድስት ሥላሴ የሦስትነታቸው ምሳሌ ነው።

6.12 <u>አትሮንስ</u> - ከእንጨትና ከብረት የሚሠራ፣ መጻሕፍት ሲነበቡ የሚዘረጉበት ንዋይ ነው። ልዑካን በቅዳሴ ሰዓት ቅድሳት መጻሕፍትን ሲያነቡ ይጠቀሙበታል። መዘምራንም በቅኔ ማኅሌት በአገልግሎት ጊዜ የሚያስፈልጉ መጻሕፍትን በማስቀመጥ የሚባለውን ያዜማሉ የሚነበበውን ያነቡበታል። በብሉይ ኪዳን በደብተራ ኦሪትና በታላቁ ቤተ መቅደስ ለቅዱሳት መጻሕፍት ማንበቢያነት ያገለግል ነበር። በሐዲስ ኪዳንም የቤተ ክርስቲን መጻሕፍት በላዩ ይዘረጉና ያነቡበታል።

አትሮንስ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን በላዩ የሚነበቡ መጽሐፍ ደግሞ የጌታችን ምሳሌ ነው።

6.13 <u>ማኅፈዳት</u> - በቁሙ መጠቅለያ ማለት ነው። ማኅፈዳት የሚባሉት ለመጠቅለያነት የሚውሉና አምስት የሚሆኑ መጠቅለያ ልብሶች ናቸው። ብዙ ጊዜ በጥቁር ጨርቅ ይሠራሉ።

አንደኛው ማኅፈድ በጻሕሉ ሥር ይነጠፋል። ሁለተኛው ከጻሕሉ ላይ ይነጠፋል ሦስቱ ማኅፈድ ደግሞ ሦስት ጾታ (ወገን) ያለው አንበር አለ። በዚያ ላይ ይነጠፋል።

ይኸም ምሳሌ ነው ዐውዱ የእመቤታችን የሰውነቷ። ከዐወዱ ላይ የሚነጠፈው ማኅፈድ የድንግልናዋ ምሳሌ ነው። ዐውዱ ማኅፈድ እንደለበሰ እመቤታችንም ድንግልናን እንደ ልብስ ተጎናጽፋለች። በሦስቱ ጾታ አንበር የሚያጠፋበት ሦስቱ ማኅፈዳት ደግሞ የቅድስት ሥላሴ የሦስትነታቸው ምሳሌ ናቸው። ሦስቱ ማኅፈዳት እመቤታችን ጌታን በጸነሰች ጊዜ አብ ለማጽናት፣ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን ለመዋሐድ፣ መንፈስ ቅዱስ ለማንጻት (ኃጢአት ኑሮባት ሳይሆን ድንግልናን ከማጣት ዘርን ከመቀበል ሊጠብቃት እንዳልተለያት ያመለክተናል።

ዐውዱ የቤተልሔም፡- በዐውዱ ላይ የሚነጠፍ ማኅፈድ እመቤታችን ጌታችን በቤተልሔም በወለደች ጊዜ የሸፈነችበት ቆጽለ በለስ ምሳሌ፣ ጻሕል የጎል (የከብቶች በረት) በጻሕሉ ላይ የሚነጠፈው የመጠቅለያው ጨርቅ ምሳሌዎች ናቸው።

ዐውድ የጎለጎታ፣ ጻሕል የመቃብረ ክርስቶስ የታችኛው ማኅፈድ የመገነዝ፣ የላይኛው ማኅፈድ የሰበን፣ አንበር የማኅተመ መቃብር ምሳሌዎች ናቸው።

6.14 <u>ጃንጥላ</u> - ከነጭ ወይም ወርቃማ ቀለም ካለው ጨርቅ ወይም ሐር ይሠራል፡- ዘንጉ ከብረት፣ ከብር ... ሊሠራ ይችላል። ታቦቱ ወደ ዐውደ ምህረት ሲወጣ፣ ካህናቱ መሥዋዕቱን ለማክበር ወደ ቤተልሔም ሲወርዱና መሥዋዕቱን አክብረው ከቤተልሔም ቤተ መቅደስ ሲወጡ ጃንጥላ ይዘረጋል።

በቅዳሴ ጊዜ ካህናቱ ጽንሐሕ ይዘው ለማዕጠንት ሲወጡ፣ ወንጌል ሲነበብ ጃንጥላ ይዘረጋል። ይኸም የሚሆነው ለታቦቱ ለመሥዋዕቱ፣ ለወንጌሉ ክብር ነው።

ጃንጥላ የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ሕዝበ እስራኤል በሲና በረሃ ፵ ዓመት ሙሉ ሲጓዙ የፀሐዩ ግለት እንዳያቃጥላቸው የእግዚአብሔርመልአክ ደመና ይጋርድላቸው ነበር። ዛሬም ክርስቲያኖች ልምላሜ ገነትን ዕረፍተ መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት በምናደርገው ጉዞ የእግዚአብሔር ረድኤት እንደ ደመና እንደሚጋርደን ለማመልከት ጃንጥላ ይዘረጋል። አንድም ጃንጥላ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ጽላቱን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊቀበል ወደ ሲና ተራራ በወጣ ጊዜ የጋረደው ደመና ምሳሌ ነው።

6.15 <u>ተቅዋም /መቅረዝ/፡-</u> የመብራት ዕቃ፣ የቀንዲል፣ የሻማ መኖሪያ፣ የሚቆም ወይም የሚንጠለጠል ባለ ብዙ አዕቅ ማለት ነው። ት. ዘካ 4፥2 በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሙሴን ተቅዋም ዘወርቁን እንዲሠራ አዝዘታል ዘጸ 25፥31-40፤ 37፥24፥ ዘዳ 8፥4

ቅዱስ ኤፍሬም ተቅዋም የእመቤታችን ምሳሌ መሆኑን በድርሰቱ ገልጻ D ል /ውዳሴ <u>ማርያም ዘእሑድ</u>፡- ተቅዋም ዘወርቅ/ በሐዲስ ኪዳን ተቅዋም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይውላል። አዘውትሮ የሚበራበት ሻማ ነው ጧፎች ወይም ሻማዎቹ የቅዱሳን መላእክት ምሳሌዎች ናቸው።

6.06 ድባብ፦ እንጨት እንደ ምሰሶ ቆመው በላዩ ጨርቅ በመስፋት የሚሠራ ትልቅ ጥላ የሚመስል ንዋይ ነው። ላዩ በነሐስ፣ በብር በመሳሰሉት እንዲያብረቀርቅ ሆኖ ይለበጣል። በክብረ በዓላት ታቦተ ሕጉ ሲወጣ ተዘርግቶ ከፊት ለፊት ይሔዳል ይኸውም በደብተራ ኦሪት እግዚአብሔር ለእነ ሙሴ ይገለጥ የነበረበት ዓምደ ደመና ምሳሌ ነው። በደመናው መካከል ክብና ልዩ ብርሃን /ሽኺናህ/ ወጥታ በታቦቱ ላይ ታረብ ነበር። ድባብ የዚህች ብርሃን ምሳሌ ነው። ያን ጊዜ በታቦቱ ላይ ይገለጥ የነበረ ብርሃን ዛሬም እንዳልተለየን ያመለክታል። 1 ነገ 8፥3፣ ዘጸ 33፥10፣ 24፥3-6፣ ዘጸ 19፥9

6.07 መነሳንስ (ጭራ)

ከጻሕልና ከጽዋው ውስጥ ተሐዋስያን እንዳይገቡ ለመከላከያነት ያገለግላል።

6.08 ታቦት እና ጽላት

ጽላቱ የሚያድርበትና የጽላቱ መኖሪያ የሆነው ታቦት የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ የክብሩም ዙፋን ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ታቦት እንደሆነ በዘጸዓት 25፥1-22 ተገልጻ D ል።

እግዚአብሔር በታቦቱ ላይ ሆኖ ሊቀ ነቢያት ሙሴን ያናግረው ነበር። በታቦቱ ውስጥ ዐሥርቱ ቃላት የተጻፈባቸው ሁለት ጽላት ነበሩ። እግዚአብሔር በታቦቱ የተለያዩ ተአምራትን አድርጓል። ታቦት ከብሉይ ኪዳንና ከእስራኤል የነፃነት ሕይወት ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው። በአሁኑም ጊዜ የጻሕሉና የጽዋው ማስቀመጫ፣ የመሥዋዕቱ ማክበሪያ ታቦት ይባላል።ኢትዮጵያ ከብሉይ ኪዳን ከወሰደቻቸው አንዱ ጽላተ ኪዳን (ታቦተ ሕግ) ነው። በኦሪት ታቦት የሚባለው ጽላቱ የሚቀመጥበት ማኅደሩ ነው። (ዘጸ 40፥21፤ ዘጸ 25፥20-22፤ መዝ 131፥8፤ 2 ቆሮ 6፥16፤ ዕብ 9፥4፤ ራእ 11፥19) የታቦት ትርጓሜው ማደሪያ መሠወሪያ ማለት ብቻ ሳይሆን መታያ፣ መገለጫም ነው። ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ ነውና (ዘጸ 13፥21-22)

ጽላት የሚባለው እግዚአብሔር ሙሴ አስቀድሞ አሠርቱ ቃላትን በእጁ ጽፎ የሰጠው ቃሉ ተጽፎ የሚገኝበት ነው (ዘጸ 4፥13፣ ዘጸ 5፥1-22፣ ዘጸ 31፥18፣ ዘጸ 24፥16፣ ዘጸ 10፥1-6፣ ዘጸ 34፥1-29)

በጽላቱ ላይ የእግዚአብሔር ስም ይቀረፅበታል፤ ከላይ ሥዕለ ሥላሴ፣ ቀጥሎ ምስለ ፍቁር ወልዳ፣ ዮሐንስ ፍቁር እግዚእ እንዲሁም መቅደሱ የተሠራበት ዓድቅም ሆነ ሰማዕት፣ መልአክም ሆነ ሐዋርያ፣ ሥዕሉ ይቀረጻል፤ ስሙ ይጻፋል፤ ይህ ከተጻፈበት በኋላ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሠየማል።

ጽላተ ኪዳኑም ማኅደረ እግዚአብሔር ነው፤ ያለ ታቦትም መሥዋዕት አይሠዋም። በቅዳሴ ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቁሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት፣ ወይኑን ደሞ መለኮት ወደ መሆን የሚለውጠው በዚህ በታቦቱ ላይ ነው። ይህም የአሁኑ ታቦት በክብር የላቀ መሆኑን ያስረዳናል የቀደመው ታቦት የበግና ፍየል ደሞ የሚረጭበት ነበርና። የአሁኑ ግን የክቡር የክርስቶስ ሥጋና ደም ይቀርብበታል። ለዚያኛው ይህ የሚያስፈልገው ከሆነ ለዚህ ለፍጹሙ መሥዋዕትማ ይልቁን እንዴት አብልጦ አያስፈልገው።

6.09 መስቀል - ለክርስቲያኖች የሕይወትና የድኅነት ምልክት ነው። መስቀል ድኅነት የሆነው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ ለመሆን ከተሰቀለበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ የታወቀ ነው። ነገር ግን ከዚያ በፊት መስቀል የእርግማን ምልክት የሆነ የወንጀለኞች መቅጫ ነበር። (ዘጸ 21፥23) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ዓለሙን ከኃጢአትና ከሞት ለማዳን በቀራንዩ የተሰቀለበትን የተመሳቀለ ዕፀ መስቀል ከሌላው መስቀል የሚለየው ቅዱስ በመሆኑ ነው። ይህም መስቀል ቅዱስ መስቀል ይባላል። በመስቀል ድኅነትን አግኝተናል። (1 ጴጥ 2፥24-25)

ሕግን በመተላለፋችን የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን ነበር፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ አልቻልንም ነበር፤ ነገር ግን ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል /በመስቀሉ/ እኛን አስታረቀን፤ በመስቀሉም ኃጢአትን ቀጣው፣ ቸነከረው፣ ሰቀለውም (ኤፌ 2፥15-16)

በእንጨት (በዕፅ) ምክንያት የመጣውን በደል ክርስቶስ በእንጨት (በዕፀ መስቀል) ላይ ተሰቅሎ አጠፋው። ወልድ ከሰማየ ሰማያት መውረዱ፣ ከሰው ወገን መወለዱ፣ ራሱን በፈቃዱ ዝቅ ማድረጉ ሲሆን ከዚህ የበለጠ ደግሞ ሞቱን በመስቀል ያደረገው።

መስቀል በጥንተ ግብሩ የርግማንና የኃጢአት ምልክት ሆኖ መቆየቱ ቢታወቅም አሁን የርግማን ምልክት የነበረው ተሽሮ የድኅነት ምልክት፣ የሕይወት ዓርማ ሆነዋል። ቆላ 1፥19-20፣ ገላ 6፥14 ለክርስቶስ መስቀል የተለየ ክብር የምንሰጥበት የተለያ ምክንያቶች አሉ። እነሱም፥-

1. ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ ራሱን የሠዋበት እውነተኛ መንበር በመሆኑ
2. የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት፣ እኛ የዳንበት የነፃነት አርማችን፣ የእኛ የክርስቲያኖች አንድነት የተመሠረተበት የድኅነት አርማችን ነው።
3. መስቀል መለኮታዊ ፍቅር የተገለጠበት መሣሪያ ነው፣ ማለት የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ክርስቶስ ስለ እኛ መከራ መስቀልን ተቀብሎ በእርሱ ውርደት እኛ ከብረናል፣ ይህን የመጨረሻ ፍቅሩን የገለጠበት መስቀል ስለሆነ እናከብረዋለን።
4. መስቀል ለአመንበት ኃይላችን ነው። ይህ መስቀል አማናዊና ምሥጢራዊ ኃይል ቅዱስ ጳውሎስ እንደ አለው ለአመኑ ነው እንጂ ላላመኑ ሞኝነት ነው። 1 ቆሮ 1፥18 እንዲያውም መስቀልን "ኃይለ እግዚአብሔር" ነው ማለቱ ዋዛ ይመስላቸዋል። መስቀልን በመቅጫነቱ የሚመለከቱት ብዙ ናቸው። ርግጥ መስቀሉ ለሞት፣ ለአጋንንት መቅጫ ሆኗል።

መስቀል በብሉይ ኪዳን ብዙ ምሳሌ አለው፤ የኖኅ መርከብ የተሠራችበት እንጨት፤ ሙሴ የፈርኦንን ጠንቋዮች ድል ያደረገበት በትር የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው። ምእመናን በክርስቶስ አምነው በመስቀል አማትበው ከኃጢአት ከአምልኮ ጣዖት ድነዋል። በመስቀል አጋንንትን፣ መናፍቃንን፣ ፍትወታት እኩያትን ድል ሲያደርጉ ይኖራሉና።

መስቀልን ሁልጊዜ አርማችንን አድርገን በፊታችን እናማትባለን። ይህንንም ዓርማ በተመለከትን ጊዜ ትዝ ሊሉን የሚገቡ ነገሮች፥-

ሀ. መስቀል የውርደት፣ የርግማን ምልክት የነበረ ሲሆን ክርስቶስ ስለ እኛ መሥዋዕት በመሆን ለበረከት እንዳደረገው እንገነዘባለን።

ለ. መስቀል ታላቅ የፍቅር ምልክት ሁኖ ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ከሞተ እኛም ይህንኑ መስቀል የፍቅር ምልክት አድርገን እንድንሸከመው፣ የክርስቶስንም ፍጹም ፍቅር እንድንረዳውና ለፍቅሩ ተገቢ የሆነ ሕይወት እንዲኖረን እንዲሁም እኛም እርስ በእርሳችን በፍጹም ፍቅር መዋደድ እንደሚገባን ያሳስበናል።

"መስቀሉን ተሸክሞ በኃላዬ ያልተከተለኝ እኔን ለማገልገል አይገባውም" ሲል ክርስቶስ የሰጠው ለክርስትና ሕይወት ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ አለብን (ማቴ 18)። ስለዚህ መስቀሉን በተመለከትን ቁጥር በመስቀል የተሰቀለውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናስታውሳለን።

መስቀል እግዚአብሔርና ሰው የታረቁበት ታላቅ አደባባይ ነው፤ ክርስቶስ መስቀልን ለአዳም እውነተኛ ፍቅርን ያደረገበት አደባባይ ስለሆነ እንከብረበታለን እንመካበታለን እንጂ አናፍርበትም። ከዚህ የተነሣ የቤተክርስቲያን ምሥጢራትን ለመፈጸም መስቀል ከፍተኛውን ቦታ ይዞ እንመለከተዋለን። የመጀመሪያውና ዋናው ቡራኬ የሚከናወነው በመስቀል ነው። ይህ ሥርዓት ቤተክርስቲያን ነው።

ስለዚህ በቅዳሴ ጊዜም ሆነ በሌሎች የማኅበር ጸሎት ጊዜያት ያለ መስቀል ቡራኬ አይከናወንም። ካህናቱም ሙሴና አሮን ሕዝቡን በባረኩበት በረከት የሚባርኩት በእጅ መስቀል ነው። እናም ሁልጊዜ ገጻችንን ባማተብን ጊዜ (የመስቀል ምልክት ባደረግን ጊዜ) እግዚአብሔር ወልድ በአባቱና በእኛ መካከል እርቅ የተፈጸመበት መሣሪያ እንደሆነ ይሰማናል፤ ስለዚህ መስቀል የክብራችን ምልክት ነው፤ መስቀል ጌጣችን ነው።

<u>ለቅዱስ መስቀል ክብር ይገባል፦</u> ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ "እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን።" (መዝ 131፥7) እንዳለ፤ መስቀል በዘባነ ኪሩብ ላይ የቆሙት እግሮቹ የሰውን ልጅ ለማዳን ተቸንክረው የዋሉበት የመድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ዙፋኑ ነውና የአክብሮት ስግደትን እንሰግድለታለን። እናከብረዋለን። መስቀልን በብዙ ምክንያት እናከብረዋለን። በአጠቃላይ መስቀል

- የእግዚአብሔርን ፍቅር የምናስብበት ነው 1 ዮሐ 3፥16
- ዲያብሎስ ያፈረበት፣ ሞተ ነፍስ ድል የተነሳበት ነው። ሮሜ 5፥12-14፣ ቆላ 2፥14፣ 1 ቆሮ 15፥54
- ክቡር ደሙ ቅዱስ ሥጋው የተፈተተበት ነው። ሉቃ 22፥16-19
- የመድኃኒታችን ውለታ የእመቤታችን እናትነት የምናስብበት ነው ዮሐ 19፥25
- የተዘጋው የገነት ደጅ የተከፈተበት ነው ሉቃ 23፥43
- መንፈሳዊ ኃይል የምናገኝበት ነው 1 ቆሮ 1፥18
- የሰው ልጅ ከሲኦል ነጻ የወጣበት ነው ኤፌ 2፥14-16
- ቅዱስ መስቀል መመኪያችን ነው ገላ 6፥14
- ሥራችንን ሁሉ የምንባረክበት ነው።

<u>የመስቀል ዓይነቶች</u>

ሀ. <u>የመጸር መስቀል፦</u> በቅዳሴ ጊዜ፣ በማዕጠንት ጊዜ ስራዒ ዲያቆን የሚይዘው ነው።

ለ. <u>የእጅ መስቀል</u>፦ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳትና ካህናት የሚይዙት ምእመናንን የሚባርኩበት ነው።

ሐ. <u>የአንገት መስቀል</u>፦ ምእመናን በማዕተባቸው አስረው በአንገታቸው በማድረግ ለጌታችን ያላቸውን ፍቅር የሚገልጡበት ነው።

መ. <u>እርፈ መስቀል</u>፦ ነቢዩ ኢሳይያስ ከለምጹ የነጻበት ፍሕም መያዣ ጉጠት ምሳሌ፦ ጌታ በዕለተ አርብ ጎኑን የተወጋበት ጦር ምሳሌ ሲሆን በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደሙ ይሰጥበታል፤ እርፈ መስቀል ጽዋዕ ከሚሠራበት ቁስ

እንደ ማንኪያ ሆኖ የሚሠራ ሲሆን በክቡር ደሙ ማቀበያ በኩል ጎድጎድ ያለ ልዩ ቅርጽ ያለበትና በእጀታው በኩል መስቀል ያለበት ነው።

እነዚህ ከላይ የተገለጡት የመስቀል ዓይነቶች በቅርጻቸው የተለያዩ ምሥጢር ሲኖራቸው የተለያየ ስያሜም አላቸው። ለምሳሌ፡-

1. ቀርነ በግዕ መስቀል
2. አርዌ ብርት መስቀል
3. ቀራንዮ ሐዋርያት መስቀል
4. ልሳነ ከለባት መስቀል
5. ትእምርተ ንትፈት መስቀል
6. ዕፀ ሥርዳይ መስቀል
7. ሐረገ ወይን መስቀል
8. ዕፀ ሳቤቅ መስቀል
9. ጽጌ ደንጉላ መስቀል
10. ዓምደ ዓለም መስቀል
11. ትእምርተ ከዋክብት መስቀል
12. እሳተ ገብኤ መስቀል
13. ለንጊኖስ መስቀል

6.20 <u>አልባሳት</u>

ቀዳስያን ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት በቅዳሴ ጊዜ የሚለብሱት አልባሳት፣ የልዑካን ልብስ /ልብስ ተክህኖ/ ይባላል። በቅዳሴ ጊዜ ሊለበስ የሚገባውን የልብስ ተክህኖ ዓይነት በቤተ ክርስቲያን ሕግ ማለትም በፍትሕ ነገሥት ተወስኗል። በፍት.ነገ.ፍት.መን 12፥479 ላይ እንደተገለጸው የቀዳስያን ልብስ ነጭ እንዲሆን ታዝዟል። በዚሁ አንቀጽ መሠረት አንድ ቀዳሽ ለመቀደስ የተሰየመበትን ልብሰ ተክህኖ ቅዳሴ ሳይጠናቀቅ ማውለቅ አይገባም። የመቀደሻ አልባሳትም በቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት በንጽሕና ይቀመጣሉ። "ወደ ውጭም ወደ አደባባይ ወደ ሕዝቡ በሚወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፤ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩት፣ ሕዝቡንም በልብሳቸው እንዳይቀድሱ ሌላውን ልብስ ይልበሱ" (ሕዝ 44፥19) እንደተባለ ከንዋያት ቅድሳት ውስጥ አንዱ የሆነው ልብስ ተክህኖ በንጹሕ ዕቃ ቤት ይቀመጣል።

አልባሳት የተለያዩ ሲሆኑ በሚለብሷቸው ልዑካን የክህነት ደረጃ ይወሰናሉ።

6.20.1 <u>ቀሚስ</u> - ከሁሉም አልባሳት በፊት የሚለበስ ልብስ ነው። እርሱም በመጀመሪያ የሚለበስ ልብስ ነው። ቀሚስ በልክ እንዲሆንም ታዝዟል፤ ከዚህ በተጨማሪ ረዥም እንዲሆን ማሳጠሪያ፣ ልክ እንዲሆን ሰውነትን

ማጠንከሪያ የሚሆን መታጠቂያ (ዝናር) አለው። ከዚህም በላይ ካባ ይደርቡበታል ፍት.ነገ.ፍ.መን.አን 12 ለሙሴ የተሰጠው ትዕዛዝ ቢጨመር እንዴት አድርጎ መስራት እንዳለበት

6.20.2 <u>ካባ ላንቃ</u> - የቀሚሱ መደረቢያ ልብስ ካባ ላንቃ ይባላል ከካባው ጋር ለምድ አብሮ ተሰፍቶ ስለሚገኝ ነው ካባ ላንቃ የተባለው። የለምዱ እግር (ዘርፍ) በየቦታው እንደ ላንቃ እየሆነ ስለሚወርድ ካባ ላንቃ ተብሎአል የሚሰራውም ልዩ ልዩ ቀለማት ካላቸው ሐር ጋር ሆኖ ወርቀ ዘቦ ነው። ወርቅና ሐሩ አብሮ ተፈትሎ ከተሠራ ጨርቅ ሊሰፋ ይችላል ወይም ልሙጡ ማንኛውም ጨርቅ ይሆናል። ካህናቱ የሚለብሱት ካባ ላንቃ አምስት መንዲል (መርገፍ) አለው። ይኸውም በካባው ላይ የሚደረበው ለምድ ላይ የሚገኙት አምስቱ መንዲል አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌዎች ናቸው።

6.20.3 <u>ሞጣሕት</u> - በአንገት ተጠልቆ ፊት ለፊት የሚወርድ የደረት ልብስ ነው። ወይም በኦሪቱ ኤፋድ የሚባለው የአሮን ልብስ አምሳል ነው። የዚህም ጨርቅ ከላይ ከተጠቀሰው ዓይነት የሚሠራ ልብስ ነው።

6.20.4 <u>አክሊል</u> - የራስ ልብስ፣ ቀጸላ፣ መሸፈኛ፣ ጌጥነት ያለው አክሊል ይባላል። ዘሌ 8፥9፣ ማር 15፥1፣ ዘካ 6፥11 አክሊል ካህናት እና ዲያቆናት በቅዳሴ ጊዜ ደፍተው ይቀድሳሉ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው አክሊል ሃይማኖቱን ለጠበቀ፣ መልካሙን ገድል ለተጋደለ፣ መልካሙን ሩጫ ለሮጠ፣ ክርስቲያኖች በተጋድሏቸው መጨረሻ የሚቀዳጁት የድል ምልክት፣ የመንፈሳዊ ተጋድሎ ውጤት ነው። ይህንንም ለማሳየት ከላዩ ላይ መስቀል አለው። (2 ጢሞ 4፥7-8)

6.20.5 <u>መጎናጸፊያ</u> - ትልቅ እና አራት ማዕዘን ያለው ባለ ገበር፣ ከወርቅ ዘቦና ከመሳሰሉት የሚሠራ፣ ታቦተ ሕጉ የሚለብሰው ለአክብሮተ ሥጋ ወደሙም ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት መጎናጸፊያ ይባላል።

6.20.6 <u>መጋረጃ</u> - ግርዶሽ፣ ጥላ፣ ከለላ፣ ልብስ ኪዳን፣ ልባጥ ሽፋን ማለት ነው ዘዳ 26፥31,37፤ ዕብ 6፥19 የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ክፍሎች የሆኑት ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት፣ መቅደስ የሚከፋፈሉት በመጋረጃ ነው። የመቅደስም በሮች መጋረጃ አላቸው።

6.20.7 <u>ምንጣፍ</u> - በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነጠፍ ነው። ይኸውም ምንጣፍ እንዲለሰልስ፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እሾህ እንዳይወጋቸው፣ እንቅፋት እንዳይመታቸው በብርሃን ዓምድ መምራቱን የማስታወስ ምሥጢር ነው። በቤተ ክርስቲያን የሚነጠፉ ምንጣፎች ስለሚረገጡ ቅዱሳት ሥዕላትና እነዚህን የመሰሉ ነገሮች የሌሉባቸው መሆን አለባቸው።

6.20.8 <u>ማኅፈዳት</u> - አምስት መጠቅለያዎች (መሸፈኛዎች) ናቸው። ብዙውን ጊዜ ከጥቁር ጨርቅ የሚሠሩ ናቸው። አንደኛው በጸሕሉ ሥር በታቦቱ ላይ ይነጠፋል፤ ሁለተኛው በጸሕሉ ላይ ይነጠፋል፤ መስዋዕቱ የሚጠቀለልበት ነው። ሦስተኛው የመሥዋዕቱ ልብስ ነው፤ ቁመቱ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ሆኖ ይለብሳል፤ አራተኛው ከሰሜን ወደ ደቡብ ሆኖ ይለብሳል፤ አምስተኛው ከመስዕ (ሰሜናዊ ምሥራቅ) ወደ ዐዜብ (ደቡባዊ ምዕራብ) ሆኖ ይለብሳል።

ክርስቶስ በበረት ሲወለድ በጨርቁ መጠቅለሉንና በበለስ ቅጠል መሸፈኑን የሚያስታውስ፣ በተለይም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ የገነዙትን የሚያመለክት ነው።

6.20.9 <u>መንጦላዕት</u> - በ 3 ቱም የመቅደስ በር፣ የሚጋረዱ መጋረጃዎች ናቸው። እነርሱም ለመቅደሱ ክብርን የሚሰጡ ናቸው። መጋረጃዎቹ የሚከፈቱበትና የሚዘጉበት ጊዜ አለ። በመጀመሪያ ቅዳሴ ማለትም “ኦ እጐዬ“

ከሚለው ምዕዳን ጀምሮ እስከ “ሚመጠን“ ድረስ ይዘጋል፤ ስግዱ ተብሎ ከታወጀና ፍትሐት ዘወልድና በእንተ ቅዱሳት ሲጸልይ ከተከፈተ ጀምሮ እስከ ፍሬ ቅዳሴ ድረስ ይከፈታል። ከፍሬ ቅዳሴ እስከ ሦስተኛው ጸሎተ ፈትቶ ማለትም “አርኅው ሖኅተ መኳንንት“ ብሎ ንፍቁ ዲያቆን ማኅሰቢያ እስከሚሰጥ ድረስ ይዘጋል። “አርኅው ሖኃተ“ ሲል ይከፈታል፤ በቁርባን ጊዜ ይዘጋል።

ምዕራፍ ሰባት

7. በቅኔ ማሕሌት የምንገለገልባቸው የመዝሙር መሣሪያዎች ምሳሌያዊ ትርጉም

7.1 ከበሮ

ከበሮ በቁሙ ንዋየ ማኅሌት፣ አታሞ፣ ነጋሪት፣ ስለ ክብረ በዓል የሚመታ፣ ጫሂ፣ ተሰሚ ማለት ነው። ”ሰብሕዎ በከበሮ” “ንሥኢ ከበሮ” “መሰንቆ ወከበሮ” ይላል። (መዝ 150፣ ኤር 38፥4፣ ዳን 3፥10፣ ኢሳ 5፥12) ከበሮ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊትና ምሳሌነት አለው።

ከበሮ ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር እየተመሰገነበት በመዝሙር ንዋይነት ሲያገለግል ኖሯል። እሥራኤል ባሕረ ኤርትራን ከተሻገሩ በኋላ የሙሴና የአሮን እኅት ማርያም ከበሮ እየመታች ዘምራለች (ዘጸ 15፥20)

ነቢዩ ዳዊትም “እግዚአብሔርን በከበሮ በማኅሌት አመስግኑት“ ብሎአል (መዝ 150፥4) በሌላም ቦታ “ለያዕቆብ አምላክ እልል በሉ፣ ዝማሬውን አንሡ ከበሮንም ስጡ“ ይላል (መዝ 80፥2) በተጨማሪም “ስሙን በማኅሌት ያመሰግኑ ፣ በከበሮና በመሰንቆም ይዘምሩለት“ ብሎ ተናግሮአል (መዝ 149፥3) ዳዊትና ሠራዊቱም ታቦተ ጽዮንን ከአሚናዳብ ቤት በአመጡ ጊዜ ዳዊትና የእግዚአብሔር ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና በመሰንቆና በከበሮ

በነጋሪትና በጸናጸል በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ በሙሉ ታይላቸው ይዘምሩ ነበር (2 ሳሙ 6፥5) ‹‹ዮዲትም ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን ከበሮ እየመታችሁ አመስግኑት›› ብላለች (ዮዲት 17፥2)

7.1.1 <u>የከበሮ አሠራርና ምሳሌያዊ ትርጉም</u>

ከበሮ መሀሉ ተፈልፍሎ ከእንጨት ወይም መሀሉን ክፍት በማድረግ ዙሪያው ከበሮ፣ ከወርቅ፣ ከነሐስ ይሠራል። የላይኛውና የታችኛው አፉ ክፍት ይደረግና ክፍት የሆነው አፍ በተወጠረ ቆዳ ይሸፈናል። እዚህ ላይ አንደኛው የከበሮ አፍ ጠባብ ሌላኛው ሰፊ እንዲሆንም ይደረጋል። ሁሉቱ አፎች እኩል ሆነው መሠራት የለባቸውም። ምክንያቱም ምሥጢር ያፋልሳሉና ነው። የከበሮው ጎን ዙሪያውን በቀይ በጨርቅ ይሸፈናል። ከጨርቁም ላይ ጠፍር ይለጠፋል (ይታሰራል) ከዚያም ለማንጠልጠል እንዲመች ማንገቻ ይደረግለታል።

ከበሮ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ግራና ቀኝ ሲመታ ስንመለከት ጌታችን በአይሁድ እጅ በጥፊ መመታቱን ያስታውሰናል።

ሀ. <u>ሰፊው የከበሮ አፍ</u> - የመለኮት ምሳሌ ነው።

ይኸ የከበሮ አፍ የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት፣ ምሉዕ በኩለሄ መሆኑን፣ ለሥልጣኑ ወሰን ድንበር እንደ ሌለው የሚያስታውሰን ነው። የአፉን መስፋት ስንመለከት በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በህልውና በመለኮት ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተስተካከለ ሁሉን የያዘ ሁሉን የሚገዛ መሆኑን እናስባለን።

ለ. <u>ጠባቡ የከበሮ አፍ፡-</u> የትሰብእት ምሳሌ ነው።

በመዝሙር ጊዜ እየተቆረቆረ ድምፅ የሚሰጠው ጠባቡ የከበሮ አፍ የወልደ እግዚአብሔርን በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ መገለጥ የሚያመለክተን ነው። ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ እርሱ በሥልጣኑ ሽረት በመለኮቱ ጎልፈት የሌለበት ቢሆንም ሥጋን ተዋሕዶ ተገልጧል። ይኸንን ጠባብ የከበሮ አፍ ስንመለከት ሁሉን የሚገዛ እርሱ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑን እናስባለን።

ሐ. <u>ከበሮው የሚለብሰው ጨርቅ</u>

ከበሮው የጌታችን ምሳሌ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። ከዚህ አንጻር የለበሰው ጨርቅ ደግሞ በዕለተ ዓርብ አይሁድ ጌታችንን ያለበት ጨርቅ (ቀይ ከለሜዳ) ምሳሌ ነው፡ ማቴ 27፥28

መ. <u>በከበሮው ላይ የተጠላለፈው ጠፍር</u>

በጌታችን ጀርባ ላይ የታየው የግርፋት ሰንበር ምሳሌ ነው። ጌታችን አይሁድ እየተፈራረቁ በገረፉት ጊዜ የጅራፍ ምልክት (ሰንበር) በጀርባው ላይ ታይቷል። ጠፍር የሰንበሩ ምሳሌ ነው። ጠፈሩን በከበሮው ላይ ስንመለከት በጌታችን ጀርባ ላይ የታየውን ሰንበር እናስተውሳለን። መዝ 21፥16

ሠ. <u>የከበሮው ማንገቻ</u> ከበሮውን ለመምታት ስናስብ በአንገታችን የምናስገባው ማንገቻ ጌታችንን አስረው የንተቱበት ገመድ ምሳሌ ነው። አይሁድ ጌታችንን ወደ ቀራንዮ ሲወስዱት የእጁ መጋፊያና መጋፊያ እስኪገዋም ድረስ በገመድ የእንግርግሪት አስረው ጎትተውበታል። ማንገቻውን በከበሮው ላይ ስናይ ይኸንን ጌታችን የታሰረበትን ገመድ እናስታውሳለን። አንድም የተገረፈበት ጅራፍ ምሳሌ ነው።

7.1.2 <u>የከበሮ አመታት</u>

ከበሮ ሲመታ ራሱን የቻለ አካሄድ አለው ከበሮ እንደ ተገኘ አይመታም ምሳሌያዊ ትርጉሙን ቀጥለን እንመልከት።

ሀ. <u>ከበሮውን ግራና ቀኝ መምታት</u>

ከበሮ ሲመታ አንድ ጊዜ ግራውን ሌላ ጊዜ ቀኝ ጎኑን ነው። ይኸም አይሁድ የጌታችንን የግራና የቀን ጉንጮች በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው ማቴ 27፥31

ለ. <u>እየተንቀሳቀሱ /እያሸበሸቡ/ መምታት</u>

መዘምራን ከበሮውን ግራና ቀኝ ሲመቱ እያሸበሸቡ ግራና ቀኝ እየተንቀሳቀሱ ነው። ይኸም ማሸብሸባቸው ወደ ግራና ቀኝ መንቀሳቀሳቸው አይሁድ ጌታችንን እያንገላቱ ወደ ቀራንዩ የመውሰዳቸው ምሳሌ ነው።

ሐ. <u>ከርጋታ ወደ ፍጥነት እየተሸጋገሩ መምታት</u>

ከበሮ ሲመታ በመጀመሪያ በርጋታ እየተቆረቆረ ይቆይና በኋላ በፍጥነት ይመታል። ይኸም ጌታችንን አይሁድ እንደያዙት መጀመሪያ በቀስታ እየዘበቱ፣ ይመቱት እንደነበርና ኋላ ላይ ግን ጲላጦስ ተመራምሮ እንዳያድነው፣ እያሉ የሰንበትም ቀን ሳይገባባቸው ያሰቡትን ለመፈጸም እየገፉ እያንገላቱ እየመቱትም ወደ ቀራንዮ (ጎልጎታ) የመውሰዳቸው ምሳሌ ነው።

መ. <u>መሬት አስቀምጦ መምታት</u>

በማሕሌት ከበሮ የሚመታው ቆሞ በአንገት አንጠልጥሎ ብቻ አይደለም። መዘምራኑ ወረብ እስኪወርቡ ድረስ ከበሮውን መሬት አስምጠው ይቆረቁሩታል። ይኸም ጌታችንን አይሁድ ወደፊት እየገፉ ወደ ኋላ እየጎተቱ ወደ ምድር መጣላቸው ምሳሌ ነው። ከበሮ መሬት ተቀምጦ ሲቆረቆር ስናይ ጌታችን መሬት ላይ ወድቆ መንገላታቱን እናስባለን።

7.2 <u>ጸናጽል</u>

ጸንጸለ መታ ካለው ግሥ የተገኘ ነው፤ ጸናጽላት በሚልበት ጊዜ ብዛትን፣ ጸናጽል ሲል ደግሞ ነጠላን የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙም ሻኩራ፣ ቃጭል እንደማለት ነው። ጸናጽል ከናስ ወይም ከብርና ከሌላም ማዕድን ሊሠራ የሚችል የዜማ መሣሪያ ነው። ጸናጽል ያማረ ድምፅ ያለው ሆኖ መልክና ልዩ ጌጥ አለው መዝ 150፥5 “ዳዊትና እስራኤል ሁሉ በቅኔና በበገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣ በጸናጽልና በመለከት በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ነበር።“ 1 ዜና 13፥8፤ መዝ 15፥5 “ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት“ “በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጸናጽል ሆኜአለሁ“ 1 ቆሮ 13፥1

7.2.1 <u>የጸናጽል አሠራርና ምሳሌያዊ ትርጉሙ</u>

ጸናጽል የ“ሀ“ ቅርጽ ኖሮት ከብር፣ ከናስ፣ ከወርቅ ይሠራል። በ“ሀ“ ቅርጽ መሀል ለመሀል ሁለት ዘንጎች አግድም እንዲኖሩ ይደረጋል። በዘንጎቹ ላይ ቅጠሎች /ሻኩራዎች/ ይንጠለጠላሉ። እነዚህ ሻኩራዎች ቁጥራቸው የታወቀና የተወሰነ ነው። ከላይ ቀስት የሚመስል ደጋን ይሠራል። “ሀ“ ቅርጽ ያለው ብር፣ ናስ መያዣ እንዲሆን ከታች እጀታ ይደረግለታል።

7.2.1.1 <u>ዓምዶቹ /ሁለቱ ዓምዶች/፦</u> የሁለቱ ኪዳናት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ናቸው ጸናጽሉን የሚያቆሙትና የሚያጸኑት ሁለቱ ዓምዶቹ እንደሆኑ ሃይማኖትም የሚጸናው በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ነው።

7.2.1.2 <u>ሁለቱ ጋድሞች፦</u> በሁለቱ ዓምዶች መካከል የሚዘረጉ፣ ሻኩራዎቹን የሚይዙ ሁለት ጋድሞች አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ተኝቶ ሳለ በሕልሙ ባየው መላእክቱ ሲወጡበት ሲወርዱበት የነበረው የብርሃን መሰላል ምሳሌ ነው። (ዘፍ 28፥12-13) እነዚህ ጋድሞች ሁለት የሆኑበት ምሳሌያዊ፣ ትርጉም የሚከተለውን ይመስላል።

ሀ. <u>የፍቅረ ቢጽና የፍቅረ እግዚአብሔር ምሳሌዎች ናቸው</u>

ቅዱሳን መላእክት ጋድሞቹን እየረገጡ ወደ ሰማይ ሲወጡ ወደ ምድር ሲወርዱ እንደ ነበር አባታችን ያዕቆብ አይቷል። ሰውም ፍቅረ እግዚአብሔርንና ፍቅረ ቢጽን ገንዘብ አድርጎ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲገባ ለማጠየቅ ጋድሞቹ ሁለት ሆነዋል።

ለ. <u>የደቂቀ አዳምና የደቂቀ መላእክት ምሳሌዎች ናቸው</u>

በጋድሞቹ ላይ እየወጡና እየወረዱ የታዩ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ይዘምሩ ነበር። በሐዲስ ኪዳን ከቅዱሳን መላእክት ጋር ደቂቀ አዳምም በአንድነት ሆነው እንዲያመሰግኑ ለማጠየቅ የመሰላሉ ጋድሞች ሁለት ሆነዋል። ሁለቱን ጋድሞች ስናይ ደቂቀ አዳም ከቅዱሳን መላእክት ጋር እንደሚያመሰግኑ እናስባለን።

ሐ. <u>የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ናቸው</u>

ሁለቱ ጋድሞች ወደ ሰማይ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ መሸጋገሪያ ድልድዮች ናቸው። የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም የመንግስተ ሰማያት መውረጃ ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ ስለሆኑ ጋድሞቹ በእነርሱ ተመስለዋል።

7.2.1.3 <u>ቅጠሎቹ ወይም እንክብሎቹ</u>

የቅዱሳን መላእክት ምሳሌ ናቸው። ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ባየው የብርሃን መሰላል ላይ ሲወጡና ሲወርዱ የነበሩ ቅዱሳን መላእክትን እንድናስብ በጋድሞቹ ላይ ቅጠሎች ይደረጋሉ። ጸናጽሉ ሲወዛወዝና ቅጠሎቹ የሚሰጡትን ድምፅ ስንሰማ ቅዱሳን መላእክቱን በመሰላሉ በመውጣትና በመውረድ ማመስገናቸውን እናስባለን።

<u>የቅጠሎቹ ቁጥር፦</u> በጋድሞቹ ላይ የሚደረጉት ቅጠሎች አምስት ከሆኑ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌዎች ናቸው። ስድስት ከሆኑ የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌዎች ይሆናሉ። ሰባት ሲሆኑ የሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ይሆናሉ።

<u>ቀስተ ደመና</u> - በጸናጽሉ ላይ የምናገኘው ቀስተ ደመና የሚመስለው ክፍል የኖኅ ቃል ኪዳን ምሳሌ ነው። ዘፍ 9፥12 ጸናጽል በማኅሌት አገልግሎት በኩል በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው ከከበሮ ጋር ነው እንጂ ብቻውን ሊሆን ወይም ሊያገለግል አይችልም።

7.3 <u>መቋሚያ</u>

መጨበጫው ከእንጨት፣ መደገፊያው ከነሐስ፣ ከብርና ከወርቅ የተሠራ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ለአዳም ተስፋ አድርጎ የሰጠው የመስቀል ምሳሌ በመሆኑ ቅዱስ ያሬድና አባ እንጦንስ በማኅሌትና በጸሎት ወይም በሰዓታት ጊዜ መቋሚያ እንዲያዝ ወይም በመቋሚያ አገልግሎት እንዲፈጸም አድርገዋል። በመሆኑም ቅዱስ እንጦንስ በጸሎት ጊዜ ቅዱስ ያሬድ በማኅሌት ጊዜ መቋሚያን ተጠቅመዋል። ሙሴ ባሕረ ኤርትራን የከፈለበትን በተሻገረ ጊዜም ተአምራት ያደረገበትን ትእምርተ መስቀል ያለበት መቋሚያውን በትከሻው ይዞ በእሥራኤል መካከል ወዲያና ወዲህ

በማለት "ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ" እያለ ያመሰገነውን ምስጋና የሚያሳስብ እንደሆነ ሊቃውንቱ ይናገራሉ።

የመቋሚያ ምሳሌያዊ ትርጉም

- መቋሚያ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።
- መቋሚያ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምሳሌ ነው።

<u>መዘምራንና መቋሚያ</u>

መዘምራን በወረብ ጊዜ መቋሚያውን በተከሻ ቸው ተሸክመው ያሸበሸባሉ ይኸም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወደኝ ቢኖር መስቀሌን ተሸክሞ ይከተለኝ ያለውን ቃል ለማሰብ ነው።

መዘምራን መቋሚያውን በእጃቸው ይዘው አንድ ጊዜ ወደ ግራ ሌላ ጊዜ ወደ ቀኝ ይዘመበታል። ይኸም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ እጅ ተይዞ መስቀሉን ተሸክሞ የመንገላታቱ ምሳሌ ነው።

መዘምራን በቅኔ ማሕሌት መቋሚያውን ወደ ላይ ያነሡና መልሰው ወደ መሬት በማውረድ ከመሬቱ ላይ ይደሰቁታል። ይኸም አይሁድ ጌታችን በገመድ አስረው እንደጎተቱት ወደ መሬትም እንደጣሉት ለማሰብ ነው። በመረግድም ጊዜ ተሸክመው ክብ ሠርተው መዞራቸው የክርስቶስን መስቀል ተሸክሞ የቀራንዮን ተራራ መውጣቱን ያስታውሰናል።

<u>ምዕራፍ ስምንት</u>

<u>8. ሥርዓተ ቅዳሴ</u>

8.1 <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት</u>

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ርትዕት፣ ሐዋርያዊትና ጥንታዊት በመሆንዋ በእግዚአብሔር ቸርነት በትሁታን ልጆቿ ጥረት ያገኘቻቸው የሃይማኖት፣ የታሪክ የፍልስፍናና የጥበብ መጻሕፍት አሏት ከእነዚህ የመንፈሳዊ ሥነ ጽሑፍ ሥራዎቿ መካከል ቅዳሴያት ጉልህ የሆኑበት ቦታ ይይዛሉ። ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት፣ ትምህርተ ሃይማኖት የሚነገርበት፣ ቅዳሴ ጠበል የሚታደልበት በመሆኑ ከሌሎች ጸሎት ሁሉ ይለያሉ። ቅዳሴ የክህነት ሥልጣን ባላቸው ብቻ የሚደረስ፣ አምስት ልዑካን በየተልዕኳቸው የሚሳተፉበት በመሆኑ የጸሎት ቁንጮ ነው።

የቅዳሴ መሠረታዊ መገኛው ቅዳሴ መላእክት ነው። ትጉኃን መላእክት ከተፈጠሩበት ዕለት ጀምረው ባለማሠለስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እያሉ ያመሰግናሉ በቅዳሴ ሥርዓታቸውም አንዱ ሲያመሰግን ሌላው ተሰጥዖ ይቀበላል። /ኢሳ 6፡3/

በቤተክርስቲያን ታሪክ ሐዋርያት ቅዳሴ እየቀደሱ ሥጋው ደሙን ይፈትቱ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ ተጽፏል። በግብጽ ቤተክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያውን ቅዳሴ የደረሰው ቅዱስ ማርቆስ መሆኑንና ይኸው ቅዳሴ ማርቆስ እንደሚባል ይገልጣሉ።

ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በ 34 ዓ.ም ቢሆንም ምሥጢራት መፈጸም የተጀመረው የመጀመሪያው ጳጳስ ፍሬምናጦስን ካገኘች በኋላ በ 4 ኛው መ/ክ/ዘመን ነው። በመሆኑም ቅዳሴያት ለቤተክርስቲያናችን አገልግሎት መዋል የጀመሩት ከዚህ ዘመን ጀምሮ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

<u>የቅዳሴዎቻችን ብዛት ስንት ነው?</u>

በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴያት ብዛት "14" ናቸው። ዛሬ በየመጻሕፍቱ በግእዝና በአማርና የተጻፈው፣ ማርች 23/1954 ማርቆስ ዳውድ በአረብኛና በእንግሊዘኛ የተረጎሙት መጽሐፈ ቅዳሴ ያጠቃለለው በአብዛኛው ሁሉም ካህናት የሚያውቁት በቅዳሴ ት/ቤቶች የሚሰጡት አሥራ አራቱ ቅዳሴያት ናቸው።

ነገር ግን በልዩ ልዩ ዘመናት ተዘርፈውና ተሸጠው ሄደው በአውሮፓ ሙዝየም የሚገኙት፣ በጥንታዊያን ገዳማትና አድባራት መጻሕፍት ቤት በተቀመጡት፣ በኢትዮጵያ የማይክሮ ፊልም ቤተመጻሕፍት በማይክሮ ፊልም ተነስተው ከተቀመጡት የብራና መጻሕፍት እንደምናገኛው ከሆነ ግን የኢትዮጵያ ቅዳሴያት ዝቅተኛው ቁጥር 20 ነው። እነዚህም፡-

1. ቅዳሴ ሐዋርያት
2. ቅዳሴ እግዚእ
3. ቅዳሴ ማርያም ዘሕርያቆስ
4. ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ
5. ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ
6. ቅዳሴ ዮሐንስ ወንጌላዊ
7. ቅዳሴ ያዕቆብ እኁ ለእግዚእነ
8. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ /ዘሀሳዕና/
9. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ /ዘልደት/
10. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘድንግል ማርያም /ዘኡሲስ
11. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ
12. ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት
13. ቅዳሴ ባስልዮስ ዘዐቢይ
14. ቅዳሴ አትናቴዎስ
15. ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ
16. ቅዳሴ ቄርሎስ /ረዥሙ/
17. ቅዳሴ ቄርሎስ /አጭሩ/
18. ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ
19. ቅዳሴ ማርቆስ
20. ቅዳሴ ጊዮርጊስ /መዓዛ ቅዳሴ/

በቤተክርስቲያን በብዛት የታወቁት ቅዳሴያት ግን የሚከተሉት ናቸው።

1. ቅዳሴ ሐዋርያት
2. ቅዳሴ እግዚእ
3. ቅዳሴ ማርያም /ዘሕርያቆስ/
4. ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ
5. ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ
6. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ /ዘሀሳዕና/
7. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ /ዘልደት/
8. ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት
9. ቅዳሴ ባስልዮስ ዘዐቢይ
10. ቅዳሴ አትናቴዎስ
11. ቅዳሴ ኤጲፋንስ
12. ቅዳሴ ዮሐንስ ወንጌላዊ
13. ቅዳሴ ቄርሎስ /ረዥሙ/
14. ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ

8.2 <u>ሥርዓተ ቅዳሴ</u>

ሥርዓተ ቅዳሴ የምንለው ከግብዓተ መንጦላዕት አንስቶ "ዕትው በሰላም" እስከሚለው ያለው ነው። ይህም ሥርዓት "በቤተክርስቲያን፡- ጉባኤ /የምእመናን አንድነት/ ናት" የሚለውን የሚመለከት ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ነው።

ሥርዓተ ቅዳሴ በአንድነት የሚፈጸም እንደመሆኑ መጠን ራሱን የቻለ አጠቃላይ ሥርዓት አለው ይኸውም በመጀመሪያ በእኛ ሀገር ከበዓለ ጥምቀት በቀር ከቤተ መቅደስ ውጭ የማይፈጸም፣ በቤተ መቅደስም ያለ ታቦት (ያለ ምሥዋዕ) የማይፈጸም ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ጸሎቱ፣ ካህኑ፣ ዲያቆኑም ሆኑ ሕዝቡ ለየራሳቸው ይበል ካህን፣ ይበል ዲያቆን፣ ይበሉ ሕዝብ በሚል የታዘዘላቸውን ብቻ በመፈጸም በጎብረት የሚጸልዩት መሆኑ ነው።

ይህም ማለት በዚህ የጎብረት ጊዜ ምንም ዓይነት የግል ጸሎት አይፈቀድም ማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ አስቀዳሾቹ ሁሉ ራሱን የቻለ የአቋቋም ሥርዓት እንዳላቸው ሁሉ ልዑካኑንም (ቀዳሾቹ) ራሱን የቻለ የአቋቋም ሥርዓት አላቸው በዚህ መሠረት ሠራኢው ካህን ከመንበሩ በስተምዕራብ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አዙሮ፣ ንፍቁ ካህን ከመንበሩ በስተደቡብ ፊቱን ወደ ሰሜን አዙሮ፣ ሠራኢ ዲያቆን በስተምሥራቅ ፊቱን ወደ ምዕራብ አዙሮ፣ ንፍቁ ዲያቆን በሰሜን ፊቱን ወደ ደቡብ አዙሮ በመቆም መንበሩን ይከብቡታል። አምስተኛው ልዑክም ከሠራኢው ካህን በስተግራ ቆሞ ለካህኑ መብራት ያበራለታል፣ መጽሐፍ ይገልጽለታል። ይህ መደበኛ አቋቋማቸው ይሁን እንጂ እንደሚጸልዩት ጸሎት በየጊዜው ይንቀሳቀሳሉ እንጂ አንድ ቦታ ላይ ብቻ ቆመው አይቀሩም።

8.2.1 <u>የዝግጅት ቅዳሴ</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ጸሎተ ቅዳሴው 3 ታላላቅ ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ግብዓተ መንጦላዕት ወይም የዝግጅት ቅዳሴ ሲባል፤ 2 ኛው የንባብ ወይንም የትምህርት ቅዳሴ ይባላል፤ 3 ኛው ደግሞ ፍሬ ቅዳሴ የሚባለው ነው።

ግብዓተ መንጦላዕት እየተባለ የሚጠራው ይህ ጸሎት ካህኑ ከመቅደስ በአፋአ ከሚጸልየው ጸሎት ጀምሮ "ሚ መጠን ግርሞት" እስከሚለው ድረስ ያለው ነው።

ሀ. <u>የካህኑ ዝግጅት</u>

ካህኑ ዝግጅቱን የሚጀምረው ወደ መቅደስ ገብቶ በመስገድ ነው። የዕለቱ ቀዳሽ ካህን መቅደስ ውስጥ እንደገባ ከመጋረጃው አፍአ (ውጭ) አንድ ጊዜ፣ መጋረጃውን አልፎ በታቦቱ ፊት ሦስት ጊዜ ይሰግዳል። ከዚህ በመቀጠልም ካህናቱንና ዲያቆናቱን እጅ ነስቶ ተረኛነቱን በመግለጥ በጸሎት እንዲያስቡት ይነግራል።

ካህኑ ከዚህ በመቀጠል የሚያደርገው ልብሰ ተክህኖውን መልበስ ነውና ልብሰ ተክህኖውን ከእርሱ የሚበልጥ ካህን (ጳጳስ፣) ካለ አስባርኮ ከሌለ ደግሞ ራሱ ባርኮ ይለብሳል። በዘወትር ቀን ከሆነ ግን ራሱ ብቻም ባርኮ ሊለብስ ይችላል።

ለ. <u>ጸሎተ ቀዳማዊ</u>

ካህኑ ልብሰ ተክህኖውን ከለበሰ በኋላ ቀጥታ የሚያመራው ወደ ጸሎት ነው። ጸሎት ቀዳማዊ እና ጸሎት ካልዓይ ተብለው በሁለት ይከፈላል።

በዚህ ጸሎት ውስጥ የሚከተሉት ይጠቃለላሉ።

ሀ. ካህኑ በሕዝቡ ፊት ሁኖ ለራሱም ለሕዝቡም የሚሆን ጸሎት ቅዳሴውን በጥንቃቄ መከተል እንደሚገባው ሞዕዳኑን "ኦ እጐየ ሁሉ በዝንቱ ልቡና" ሲል ይጀምራል።

ለ. ካህኑ በመላ ቀዳሾቹን ካህናት ይዞ በሕዝቡ ፊት ቁሞ የንሰሐ ጸሎትን ይጸልያል፤ ይኸም ዝግጅትና ጸሎት ለቅዳሴ ተገቢ አገልግሎታቸውን ለመስጠት ንጹሐን ሁኖ መቅረባቸውን የሚያመለክት ነው።

ሐ. የተለያዩ መዝሙራት ዳዊት ይጸልያል እነርሱም፡-

መዝ 24፣ 68፣ 101፣ 102፣ 129፣ 130

መ. ከዚህ በኋላ ካህኑ "እግዚአብሔር አምላክነ አንተ ውእቱ ባሕቲትከ ቅዱስ" ከሚለው ጀምሮ ይጸልያል፣

ሠ. በድጋሚ ካህኑ "እግዚአብሔር አምላክነ ዘተአምር ኩሎ ሕሊና ሰብእ" የሚለውን ይጸልያል፤ ይኸው ጸሎት የቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ ነው።

ረ. ካህኑ "እግዚአብሔር አምላክነ ወፈጣሪነ" የሚለውን ይጸልያል።

ሰ. "ኦ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአንሣእከነ እምድር..." የሚለውን ጸሎት ይጸልያል።

ሸ. "እግዚአብሔር አምላክነ ዘይነብር መልዕልተ" የሚለውን ጸሎት ከመጀመሩ በፊት 3 ጊዜ ይሰግዳል። ይኸንም ይጸልያል፤ ይህም ጸሎት የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው።

ሐ. <u>ጸሎተ ካልዓይ (በንዋያተ ቅድሳት ላይ የሚጸለይ ጸሎት)</u>

ከላይ የተገለጹትን ጸሎቶች ከፈጸመ በኋላ ንዋያቱን በጸሎትና በቡራኬ ያከብራቸዋል። ካህኑ እያንዳንዱን ንዋያተ ቅድሳት የየራሳቸውን ጸሎት እየጸለየ ካከበረ በኋላ ሲያስተናብር "እግዚአብሔር ማዕምረ ልብ..." የሚለውን ይጸልያል፤ ሲፈጽም ደግሞ "ሃሌሉያ ወአንሰ በብዝኃ ምሕረትከ እበዉእ ቤተከ" የሚለውን ይጸልያል በዚህ መንገድ ግብዓተ መንጦላዕት ይፈጽማል ከዚህ በኋላ ሀለተኛው ክፍል (ጸኡ ንዑሰ ክርስቲያን እስከሚለው ድረስ ያለው) ይቀጥላል።

8.2.3 <u>የንዑሰ ክርስቲያን የንባብ ወይም የትምህርት ቅዳሴ</u>

ይህ ሁለተኛው ክፍል ሁሉንም ሕዝብ የሚያሳትፈው ጸሎት የሚያከናውነው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው። ርእሱን የንዑሰ ክርስቲያን ቅዳሴ ያልነው ከዚህ በመነሣት ሲሆን በዚሁ ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት የሚቀርቡበትና ትምህርተ ወንጌልም የሚሰጥበት ስለሆነ ትምህርት ቅዳሴም ብለነዋል።

1. ጎብስቱን በመሶብ ወርቅ ወይኑን በጽዋዕ ዲያቆኑ ተሸክሞ ከቤተልሔም ወደ ቤተ ክርስቲያን በማዕጠንት እየታጀበ፤ ቃጭል እየተመታ ሲገባ፤ መረዋው ይደወላል፤ አስቀዳሹ ሕዝብ በበኩሉ ቦታውን ይዞ ቀጥ ብሎ ይቆማል። በዚህ ጊዜ ገባሬ ሠናይ ካህን "ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት" የሚለውን አዋጅ ፊቱን ወደ ምዕራብ አዙሮ ያውጃል። ሕዝቡም ዕለታቱ ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ሐሙስ ከሆኑ "እምነ በሀ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርጉት አረፋተሃ ወሥእልት በዕንቁ ጳዝዮን እመነ በሀ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን" የሚለው፤ ረቡዕ፣ ዓርብና ቀዳሚት ከሆነ ደግሞ "መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ" የሚለውን፣ በእሑድ ሰንበት "ኩሉ ዘገብራ ለጽድቅ ጽድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ፤ ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ይፈልጠኒኑ እም ሕዝቡ" የሚለውን እስመ ለዓለም ይዘምራል። በትንሣኤና በበዓለ

ሃምሣ "ሃሌ ሉያ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገንዝዎ ለኢየሱስ በስንዱነት ለዘተንሥአ እሙታን በመንክር ኪን" የሚለውን አቡን ይዘምራል። ከዚህ በማስከተልም "እመቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን..." የሚለውን የሐዋርያት ሲኖዶስ ያውጃል።

2. ዲያቆናት ቀዳስያኑ በጎበረት 1 ጊዜ መንበሩን ይዞራሉ፤ ካህኑም "ተዘከር እግዚኦ እለ አቅረቡ ለከ" የሚለውን እየጸለየ አብሮ ይዞራል።
3. ሕዝቡ "አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ" የሚለውን እየዘመረ ካህኑ "እግዚአብሔር አምላክነ ዘተወከፍከ ቁርባነ አቤል በውስተ በጽው..." የሚለውን እየጸለየ አንድ ጊዜ መንበሩን ይዞራል።
4. ከዚህ በኋላ ካህኑ "ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን ዘሐርከ ውስተ ከብካብ" የሚለውን ጸልዩ ቡራኬ ይጀምራል ከዚህ በኋላ ካህኑ ስለ ራሱ እና ስለ መስዋዕቱ ሁሉም እንዲጸልዩለት ልመና ያቀርባል እንደገናም ወደ ረዳቱ ካህን ፊቱን መልሶ "ወንድሜ ካህን ሆይ በጸሎትህ አስበኝ" ሲል ይለምነዋል። እርሱም በጸሎቱ በስሜቱ በአገልግሎቱም ፍጹም ተባባሪነቱን በመግለጽ "እግዚአብሔር ክህነትህን ይጠብቅ መሥዋዕትህንም ቁርባንህንም በብሩህ ገጽ ይቀበልህ" ሲል ይጸልይለታል።

ሀ. <u>የሃይማኖት ምስክርነት</u>

ይ.ካ "አሐዱ አብ ቅዱስ፤ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፤ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ካህኑ ይኽን ቃል ጮኾ አሰምቶ፣ እጁንም ዘርግቶ አንገቱን አቅንቶ በታላቅ ዜማ ይቀድሳል። በዚህ ቃል አንድነትንና ሦስትነትን በመመስከር የሥላሴን ስራ እና ቅዱስነት በመግለጽ የእምነት ምስክርነትን በመስጠት ቅዳሴው ይጀመራል።

ይ.ሕ "በአማን አብ ቅዱስ፣ በአማን ወልድ ቅዱስ፣ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን የቄሱን ቃል በጸጥታ ከሰማ በኋላ የጋለ ምስክርነት በመስጠት ያረጋግጣል።

በመዝ 116 ላይ የተገለጸውን የዳዊት መዝሙር ካህኑና ሕዝቡ በመቀባበል ይሉታል።

ለ. <u>ጸሎተ አኮቴት (የምስጋና ጸሎት)</u>

ጸሎተ አኮቴት ማለት የምስጋና ጸሎት ማለት ነው።

ጸሎተ አኮቴት የሚባለው ጸሎት "ነአኩቶ ለገባሬ ሠናያት" ከሚለው ጀምሮ እስከ ፍሬ ቅዳሴ የሚጸለየው ጸሎት ነው። ዲያቆኑ "ተንሥኡ ለጸሎት" ሲል ሕዝቡ "እግዚኦ ተሣሀለነ" ይላል ካህኑ "ሰላም ለኩልክሙ" ሲል ሕዝቡ "ምስለ መንፈስከ" ይላል።

በመቀጠል ካህኑ "ነአኩቶ ለገባሬ ሠናያት ላዕሌነ" የሚለውን የቅዱስ ባስልዮስ ጸሎት ይጸልያል።

ዲያቆኑ ደግሞ በምዕራብ በር እንደ ቆመ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ "ጸልዩ" ይላል ሕዝቡም "ኪራላይሶን" (አቤቱ ይቅር በለን) ይላል።

ሐ. <u>ጸሎተ መባዕ</u>

ጸሎተ መባዕ ማለት ጧፍ፣ ሻማ፣ ዘይት፣ ዕጣን፣ ዘቢብ፣ መገበሪያ፣ አልባሳት፣ መጻሕፍት፣ ንዋያተ ቅድሳት ይዘው መጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚያገቡ ሰዎች የሚጸለይ ጸሎት ነው። ይህም ጸሎት የሚጸለየው በሁለተኛው ክፍለ ቅዳሴ በጸሎተ አኮቴት መካከል ነው።

ይ.ዲ - "ተንሥኡ ለጸሎት" - ንፍቅ ዲያቆን

ይ.ሕ - "እግዚኦ ተሣሃለነ"

ይ.ካ - "ሰላም ለኩልክሙ" - ንፋቅ ካህን

ይ.ሕ - "ምስለ መንፈስከ"

ይ.ካ -"ወካዕበ ናስተበቁዕ ዘኩሎ ይእኅዝ እግዚአብሄር አብ" የሚለው የሐዋርያት የመባዕ ጸሎት ካህኑ ይጸልያል።

ይ.ዲ - "ጸልዩ በእንተ እለ ያበውዑ መባዐ"

"መባ ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ"

ይ.ሕ - "ተወክፍ መባዖሙ ለአኅው..."

ይ.ዲ - "ተንሥኡ ለጸሎት" (በለሆሳስ)

ይ.ሕ - "እግዚኦ ተሣሃለነ"

ይ.ካ - "ሰላም ለኩልክሙ"

ይ.ሕ - "ምስለ መንፈስከ"

መ. ጸሎት እንፎራ (አናፎራ)

ስለ ኅብስቱና ስለወይኑ ክብር በተለይ የሚጸለይ ጸሎት፣ ቡራኬም የሚተላለፍበት፣ እማሬ ምልከታ የሚደረግበት ጸሎት ነው።

ይካ "ኦ ሊቅየ ኢየሱስ ክርስቶስ..." የሚለውን ጸሎት ካህኑ ይጸልያል፤ በዚህም ጊዜ ካህኑ ሊጠነቀቅባቸው፣ ሊጠብቃቸውም የሚገቡ ክፍሎች አሉ። እነርሱም፡-

1. እማሬ፡- ይኸ ቃል በሚኝበት ላይ ካህኑ በእጁ እያመለከተ በዐይኑም እየተመለከተ በኅብስቱና በወይኑ ላይ አፋን ከልቡ፣ ልቡን ከአፋ ጋር አድርጎ መጸለይና ማመልከት አለበት፤ ይኸንም የመሰለ ቃል በፍሬ ቅዳሴ በየቦታው አለ፤ እማሬያት 11 ናቸው። በጸሎተ እንፎራ 2 "ይረስዮ" ሲል 2፤ በሥጋና፣ በደሙ ላይ 7፣ ሲደመር 11 ነው።

2. ቡራኬ፡- ይኸም ቃል በሚገኝበት ቦታ ላይ 1 ጊዜ ወይም 3 ጊዜም እንደሆነ እንደትእዛዙ በኅብስቱም በወይኑም ላይ መባረክ አለበት የቅዳሴ ቡራኬያት 42 ናቸው። እነዚህም 21 የአፍአ፣ 21 የውስጥ ቡራኬያት ናቸው። የአፍአ ቡራኬ ለሕዝብ፣ የውስጥ ቡራኬ ለቁርባን ነው።

ሠ. ጸሎተ መግንዝ

ጸሎተ መግንዝ ማለት የመገንዣ ጸሎት ማለት ነው፤ ካህኑ ይህንን የሚጸልየው በማኅፈድ ኅብስተ ቁርባኑንና ጽዋውን ሲሸፍን ነው። ኅብስቱንና ወይኑን መሸፈኑ የጌታ የመገነዙ ምሳሌ ነው።

ረ. ጸሎተ ፍትሐት ዘወልድ

ይ.ካ - "ፍትሐት ዘወልድ ይጸልያል፤ ሕዝቡ ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረት እየለመነ በመሬት ላይ ወድቆ ይህን የንሰሐ ጸሎት በማድመጥ "አሜን" ይላል።

በዚህ ጸሎት ሕያዋንን በአጠቃላይ እያመለከተ ሥርየተ ኃጢአት እንዲያገኙ ይጸልይላቸዋል፤ ስለ አዲሶች ሙታን ማለት 40 ቀን ስላልሞላቸው ዕረፍተ ነፍስ እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ይለምናል።

ይ.ዲ. "በእንተ ቅድሳት" ጸሎቱ ከኪዳን የተወሰደ አንድ ክፍል ሲሆን የሚጸልየውም ካህን ወይም ዲያቆን ነው ስለማንኛውም ወገን ምልጃ ያለበት ጸሎት ስለሆነ አሁንም ሕዝቡ ሰግዶ (ወድቆ) "አሜን ኪርያላይሶን" ወይም "አሜን እግዚኦ ተሣሃለነ" እያለ እግዚአብሔርን ይለምናል።

ሰ. <u>ጸሎተ ዕጣን</u>

ጸሎተ ዕጣን ማለት ዕጣንን ለመባረክና ለማክበር በዕጣን ላይ ካህኑ የሚጸልየው ጸሎት ነው፤ አምስት ቆቀር ዕጣን ተመርጦ ይቀርብና ካህኑ በዕጣኑ ላይ ጸሎቱን አድርጎ ይባርከዋል፤ ሦስቱን ቆቀር ዕጣን ወዲያው እንደ ባረከው በማዕጠንቱ ውስጥ ይጨምረዋል። አንዱን በጸሎተ ወንጌል ጊዜ፣ አንዱን ደግሞ "ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ" ሲባል ይጨምረዋል።

ከዚህ በኋላ ንፋቁ ዲያቆን፣ ሠራኢው ካህንና ሠራኢው ዲያቆን በአንድነት ሆነው በመንበሩ ዙሪያ 3 ጊዜ ዑደት ያደርጋሉ። ይኸም ንፋቅ ዲያቆን መብራት ይዞ ይቀድማል፣ ካህኑ ማዕጠንቱን ይዞ እያጠነ ይሄዳል ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን መጽሐፈ ጳውሎስን ይዞ ይዞራል። ንፋቁ ዲያቆን መብራት ይዞ መቅደሙ የመጥምቁ ዮሐንስ፣ ሠራኢ ካህን መከተሉ የክርስቶስ፣ ሠራኢው ዲያቆን ከካህኑ በኋላ ሆኖ መስቀል ይዞ መዞሩ የእስጢፋኖስ ምሳሌዎች ሆነው ነው።

ይ.ዲ. "ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተክርስቲያን"

ሸ. <u>የሐዲስ ኪዳን ምንባባት</u>

ከሐዲስ ኪዳን የሚነበቡት በሠራኢው ዲያቆን መልእክተ ጳውሎስ፣ በንፋቁ ዲያቆን፣ መልእክተ ሐዋርያት፣ በንፍቁ ካህን የሐዋርያት ሥራ፣ በሠራኢው ካህን ወንጌል ሲሆን የሚነበቡትም በሁለተኛው ክፍል ቅዳሴ ነው። ለዚህም ነው የንባብ ወይም የትምህርት ቅዳሴ የተባለው።

ቀ. <u>ጸሎተ ኪዳን</u>

ጸሎተ ኪዳን ማለት ከመጽሐፈ ኪዳን በተለይም ለጸሎት ጌታ ከተናገረው ኪዳን ተወስዶ የሚጸለይ ነው፤ ለጸሎት የተለዩ ሰባት ኪዳናት አሉ ከእነሱ አንዱ ይህ ጸሎት ነው። ጸሎቱ በሌሊት፣ በነግህ፣ በሠርክ እንዲጸለይ ተደርጎ በ 3 ተከፍሎ የሚጸለይ ነው። በቅዳሴ ጊዜ የሚጸለየው የነገው በነግህ የሠርኩ በሠርክ ቅዳሴ ነው።

በ. <u>ጸሎተ ወንጌል</u>

ጸሎተ ወንጌል ማለት ምእመናን የወንጌልን ቃል በንቃት አድምጠውና ተገንዝበው ለመፈጸምና ቃሉን በተግባር ለማድመጥ እንዲችሉ ወንጌል ከመነበቡ በፊት ሊነበብ ሲል ቀደም ብሎ የሚጸለይ ጸሎት ነው።

ይ.ዲ - "ተንሥኡ ለጸሎት"

ይ.ሕ - "እግዚኦ ተሣሃለነ"

ይ.ካ - "ሰላም ለኩልክሙ"

ይ.ሕ - "ምስለ መንፈስከ"

ይ.ካ - "እግዚአብሔር እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነ" የሚለውን ካህኑ ይጸልያል

ይ.ዲ - "ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ" ዲያቆኑ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ በቅድስት ላይ ቆሞ ወደ ምዕራብ ስለ ቅዱስ ወንጌል ጸልዩ ብሎ ሕዝቡን ያዝዛል

ይ.ሕ - "ረስየነ ድልዋን ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱስ"

“ወንጌልን ለማዳመጥ ለመረዳት የተገባን የተዘጋጀንም አድርገን“ ሲል ሕዝቡ በአንድ ድምፅ ይጸልያል።

ይ.ካ - “ተዘከር ካዕበ እግዚኦ እለ አወሥዑኒ ... “ የሚለውን ፊቱን ወደ መሠዊያው አድርጎ ይጸልያል

ይ.ዲ - ምስባክ ከዳዊት መዝሙር ለየዕለቱ የተወሰነው 3 ስንኝ ሁልጊዜ ይዘመራል በዚህ ጊዜ ካህኑ 4 ቱን መዓዘን ይባርካል። እንዲህ ሲል “እግዚአብሔር ልዑል ይባርክ ላዕለ ኩልነ ወይቀድስነ በኩሉ በረከት“ ይኸን ከፈጸመ በኋላ የሚቀጥለውን ጸሎት ይጸልያል። “እግዚአብሔር አምላክነ ወመድኃኒነ ወመፍቀሬ ሰብእ“ ይኸንም ከፈጸመ በኋላ በጽንሐው ዕጣን ጨምሮ አንድ ጊዜ በመንበሩ ዙሪያ እያጠነ ዑደት ያደርጋል። በዚህም ጊዜ መብራት የያዘው ዲያቆን በፊቱ ይሆናል ቀጥሎ ረዳቱ ካህን ወንጌሉን ይዞ በፊቱ ይሔዳል ሠራኢው ዲያቆን መስቀል ይዞ ሠራኢውን ካህን ይከተላል፤ ጥላ የያዘ 3ኛ ዲያቆን የነቢያት፣ ንፍቅ ካህን የመጥምቁ ዮሐንስ፣ ሠራኢ ካህን የጌታ፣ ሠራኢ ዲያቆን የእስጢፋኖስ ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው።

ይ.ካ - በማዕጠንቱ “ቡሩክ እግዚአብሔር አኀዜ ኩሉ“ ተራዳኢው ካህን “አዕኩትዎ ለአብ“

ይ.ካ - “ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ“

ይካ - ንፋቅ “አዕኩትዎ ለወልድ“

ይ.ካ - “ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ“

ይ.ካ - ንፋቅ “አዕኩትዎ ለመንፈስ ቅዱስ“ እያሉ በማዕጠንት ወንጌልን ያከብራሉ።

ይ.ዲ - “ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምኡ ወንጌል ቅዱስ ዜናሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ“ በማለት በምዕራብ በር ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ ያውጀል።

የንጉሥን አዋጅ ወንጌል መንግሥትን ቅዳሴ አዳምጦ እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጠቅላላ የምሥራች ሥራን የሚናገር የሚያበስር ነው። ማለት ነው።

ይካ - እግዚአብሔር ምስለ ኩልክሙ ካህኑ ወንጌሉን ከንፍቁ ካህን ተቀብሎ ለሕዝቡ እያሳየ እግዚአብሔር አይለያችሁ ከእናንተ ጋር ይሁንላችሁ ሲል የዕለቱን ዜና በሚስመበት ጊዜ ጸጋ እግዚአብሔር እንዳይለያቸው ይመርቃቸዋል።

ይ.ካ በታላቅ ድምፅ “ወንጌል ቅዱስ“ ዘዘኄወ፣ ዘሰበከ እያለ እንደ ወንጌሉ ምንባብ ያዜማል። በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ፣ በ3ቱ ወንጌላት “ዘዘኄወ“ ይላል ምክንያቱም 3ቱም ወንጌላት የጌታን ዜና የሕይወት ታሪክ የሚናገሩ ስለሆነ ነው በዮሐንስ በ4ኛው ወንጌል ግን “ዘሰበከ“ ይላል። ምክንያቱም ባሕርዩ ወደ አምላክነቱ ሄዶ “ቀዳማዊ ቃል“ እንደ አለው ሁሉ ይበልጡ የወንጌል ክፍል መለኮታዊ ሥራውን መለኮታዊ ባሕርዮን ስለሚናገር ምሥጢር ሥላሴን አጉልቶ ስለሚያስረዳ ዜና ሳይሆን ስብከት ትምህርትም ነው በተለይም ነገረ መለኮት ነውና “ዘሰበከ“ ይላል። ስለዚህም ራሱ ወንጌላዊው ገባሬ መለኮት ተብሎ ተሰይሚል ዮሐንስ ታዎንሎስ የሚለው ነባቤ መለኮት የሚለውን ትርጉም ተከትሎ ነው።

ይሕ - “ስብሐት ለከ ክርስቶስ እግዚእየ ወአምላክየ ኩሉ ጊዜ“ የምሥራች የምታሰማኝ ጌታዬና አምላኬ ክርስቶስ ሆይ ሁልጊዜም ለአንተ ምስጋና ይገባል“ ሲል እያንዳንዱ ምእመን የጌታን ባለውለታነቱን አውቆና አምኖ ያመሰግናል “ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ...“ የሚለውን ይዘምራሉ በአስተምሕሮ፣ በክረምትና በጾም ወራት በተፈሥሑ ፈንታ “በወንጌል መራሕነነ“ የሚለው ይዘመራል።

የሰላም ወንጌል ስለሆነች ሰላምን የምትሰብክ ወንጌል እንደመሆኗ ከንባቡ በኋላ ሕዝቡም ሁሉ ይሳለማት ዘንድ ይገባል።

በመጀመሪያ ገባሬ ሠናዬ ካህን ለረዳቱ "ነዋ ወንጌል መንግሥት" ሲል ይሰጠዋል እርሱም ሲቀበል "መንግሥቶ ወጽድቆ ዘአወፈየኒ አወፈይኩከ" እያለ ለዲያቆኑ ይሰጣል ዲያቆሙን በበኩሉ "ነስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት"ሲል ለካህኑ አመቻችቶ ወንጌሉን ይይዝለታል።

ካህኑም "ባርክ እግዚኦ ነገር ዘእምወንጌለ ዕገሌ ረድኢ ወሐዋርያሁ..." ሲል ይጀምራል ይኸም በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ የሆነ እንደሆነ የወንጌላዊያኑን ስማቸው እየጠራ ያናገረው በዮሐንስ የሆነ እንደሆነ ግን "ዝ ቃል ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ" በማለት አሳውቆ ንባቡን ይጀምራል።

ካህኑም ወንጌሉን አንብቦ ሲፈጽም በማቴዎስ "ሰማይ የምድር የነልፍ ወቃልየስ ኢየኀልፍ" በማርቆስ "ዘቦ ዕዝን ሰሚዐ ለይሰማዕ" በሉቃስ "ይቀልል ኅልፈተ ሰማይ ወምድር እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእም ነቢያት ይቤ እግዚእ ለአርዳኢሁ" በዮሐንስ ዘየአምን በወልድ በሕይወት ዘለዓለም ይላል።

እንዲሁም ከምንባብ በኋላ የሚዘመሩት መርገፎች የሚከተሉት ናቸው። በማቴዎስ "ነአምን አበ ዘበአማን..." ይላል በማርቆስ "እሉ ኪሩቤል ወሱራፌል..." ይላል በሉቃስ "መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚኦ..." ይላል በዮሐንስ "ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ቃለ እግዚአብሔር..." ይላል።

ይ.ካ፡- ንፋቅ ካህን በለሆነሳስ "ርኁቀ መዓት ውብዙኃ ምህረት ወጻድቅ" የሚለውን ይጸልያል እንዲህ ስለጠቅላላ ጸሎት ቅዳሴ በላይ ስለ ክብረ ወንጌል ከጥንት ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የሚመጣው ምሳሌ በአማርኛ እንደሚከተለው ይሆናል።

በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃላት ሲነበቡ የሰማያዊውን ንጉሥ የተከበረ የወንጌሉን ቃል ለመስማት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ከማመስገንና ከመቀደስ በቀር ማድነቅና ጸጥታ ሊሆን ይገባል።

የምድራዊ ንጉሥ ደብዳቤ ሲነበብ አንድ ሰው እንኳን ለመናገር ለማይደፈር ከሆነ ቢናገርም ግርፋትና ቅጣት የሚያገኘው ከሆነ የሰማያዊ ንጉሥ ደብዳቤ የምትሆን ወንጌል ስትነበብማ ቢናገር እንደምን እንደርሱ ያለ ያገኘው ይሆን (ከዚህ በኋላ ካህኑ የተነበቡትን መጻሕፍተ ሐዲሳትና ምስባኩን በማብራራት ለሕዝቡ ስብከት ያደርጋል)።

ከጸሎተ ዕጣን ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ ባለው ጸሎት ንዑስ ክርስቲያን ሁሉ ይካፈሉት ነበር፤ ምንአልባት ስብከት የሚገኙበት፤ ትምህርት የሚሰጥበት ክፍል ነውና ንዑስ ክርስቲያን የተባሉት በእውቀት እንዲታነጹ፣ በእምነት እንዲጸኑ በማለት እስከዚህ ሰዓት የጸሎቱ ተካፋዮች ሆነው ይቆያሉ፤ ከዚህ በኋላ ግን ፍሬ ቅዳሴ ሊጀመር ስለሆነ እነርሱ እንዲወጡ ዲያቆኑ እንዲህ ሲል ያውጃል።

ይ.ዲ፡- ዓው ንዑስ ክርቲያን

ይ.ዲ፡- ተንሥኡ ለጸሎት

ይ.ሕ፡- እግዚኦ ተሣሃለን

ይ.ካ፡- ሰላም ለኩልክሙ

ይ.ሕ፡- ምስለ መንፈስከ

ተ. ጸዋትው

ማኅበረ ምእመናን የሚጸለይ ጸሎት ነው። ጸዋትዉ ማለት የምእመናን ወገኖች ማለት ነው፤ ስለ ጾታ ምእመናን ስለሚጸለይ ጸዋትው ተብሎአል።

ይ.ካ፡- ወካዕበ ናስተብቁዕ በማለት ካህኑ ስለአንዲቱ ቅድስት ቤተክርስቲያን ከዓለም ዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ስለምትገኝ የሐዋርያትም ጉባኤ ስለምትሆን ቤተ ክርስቲያን ፍጹም ሰላምና አንድነት ይጸልያል።

ይ.ዲ፡- "ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን..." ሲል ፊቱን ወደ ምዕራብ ወደ ሕዝቡ አድርጎ ትእዛዝ ያስተላልፋል። ካህኑም "ኩሎ ሕዝበ ወኩሎ መራእየ ባርኮሙ" ሲል ሕዝቡን በመስቀል ይባርካል፤ ሕዝቡም "ኪራይላይሶን (አቤቱ ይቅር በለን)" ሲል ስለቤተ ክርስቲያን ያለውን ስሜት ጸሎቱን ልመናውን ያቀርባል።

ይ.ዲ፡- ንፍቅ ዲያቆን ተንሥኡ ለጸሎት

ይ.ሕ፡- እግዚኦ ተሣሃለነ

ይ.ካ፡- ንፍቅ ካህን ሰላም ለኩልክሙ

ይ.ሕ፡- ምስለ መንፈስከ

ይ.ካ፡- ንፍቅ፤ ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ይጸልያል ማለት ረጅም ወራት፣ ሰፊ ዘመናት ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እግዚአብሔር ይሰጠው ዘንድ፤ እንዲሁም እግዚአብሔር የጠባቂነት ጊዜ የተሰጠውን በትክክል ለመፈጸም እንዲቻል እንዲያደርገው፤

ይ.ዲ፡- ንፋቅ" ጸልዩ በእንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት..." ብሎ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ በምዕራብ በር ቆሞ ያዝዛል በዚህ ጊዜ ሕዝቡ "አቡነ ዘበሰማያትን" ይጸልያሉ

ይ.ዲ፡- ተንሥኡ ለጸሎት

ይ.ሕ፡- እግዚኦ ተሣሃለነ

ይ.ካ፡- ሰላም ለኩልክሙ

ይ.ሕ፡- ምስለ መንፈስከ

ይ.ካ፡- ወካዕበ ናስተበቁዕ ... ሲል ካህኑ ስለ ምእመናን አንድነት ጎብረት ምልጃ ያደርጋል። ተዘክር እግዚኦ ማኅበረነ ባርኮሙ ሲል ሕዝቡን በመስቀል ይባርካል

ይ.ዲ፡- ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ወማኅበረነ ዘውስቴታ በማለት በምዕራብ በር ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ ያዝዛል።

ሕዝቡም "ማኅበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም" ሲል ይመልሳል። በዚህ ጊዜ ካህኑ ማዕጠንቱን ተቀብሎ በመሥዋዕቱ ላይ ያጥናል፤ ዕጣን ማሳረጉ ነው፤ እንዲሁም በ 4 ቱ ማዕዘንም ያጥናል፤ በሚያጥንበትም ጊዜ "ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወይዘረው ፀርከ" የሚለውን ይጸልያል።

ይ.ዲ፡- ንበል ኩልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሃይማኖት ሲል ያውጃል፤ በሰው ጥበብ ሳይሆን በመንፈሳዊ ጥበብ እግዚአብሔር በገለጠልን ጥበብ ሆነን የሃይማኖትን ጸሎት ሁላችን እንበል ሲል ዲያቆኑ ያዝዛል።

ጸሎተ ሃይማኖት

ይ.ሕ፡- ጸሎተ ሃይማኖት የኦርቶዶክሳዊ እምነት ያለው የአንድ ትምህርት ተከታይ የመሆኑ ምልክት ጸሎተ ሃይማኖትን ጨኽና አሰምቶ ሁሉም በጎብረት ይጸልያል፣ ይምራል። ጸሎተ ሃይማኖት የሚጸለየው ቅዳሴው የሊቃውንት ሲሆን ነው ቅዳሴው ቅዳሴ ሐዋርያት፣ ቅዳሴ እግዚእ፣ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣ ቅዳሴ ማርያም ከሆነ "አመክንዮ ዘሐዋርያት ይጸለያል።" ከዚህ በኋላ ካህኑ እጁን ሲታጠብ እንዲህ ይላል "ንጹሕ የሆነ ከቁርባኑ ይቀበል ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል፤ ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ በተዘጋጀው በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል በልቦናው ቂምን የያዘ ልዩ ሃሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ"

ምንም ሥጋውና ደሙ ከናዛዡና ከተናዛዡ የቀረውን ኃጢአት የሚያሳይ ቢሆንም ማንኛውም ምእመን ሥጋውንና ደሙን ከመቀበሉ አስቀድሞ የተጣላው ካለ ታርቆ፣ የበደለው ካለ ክስ የወሰደው ነገር ካለ መልሶ፣ ዝሙትንና የተለያዩ ነፍስን የሚጎዱ ክፉ ነገሮችና ሃሳቦች እንዳሉበት እነርሱን ሠርዞ ትቶ ፍጹም ንጹሕ ሆኖ እንዲቀርብ ካህኑ በየጊዜው ያውጃል ምእመኑ ደግሞ ይኸንን ሰምቶ ለዛሬ ሳያመቸው ቢቀር ለሚቀጥለው ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የሚያስጠነቅቅ እንጅ እንዲወጣ እንዲቀር የማስፈራሪያ የማባረሪያ ቃል አለመሆኑን ተገንዝቦ መቅረብ አለበት።

ካህኑ፡- እጁን ከታጠበ በኋላ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ የታጠበበትን ውኃ እየረጨ እንዲህ ይላል "እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጽሕ እንዳደረግሁ ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ፤ ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከእርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም፤ በደላችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጅ በንጽሕና ሁናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ" ማለት ነው።

ይኸ በቅዳሴ መካከል እጅ መታጠብ ወደ ፍሬ ቅዳሴው የሚገባ ስለሆነ ከዚህ በኋላ ግን በእጅ ምንም መንካት የለበትም፤ ጎብስቱንና ወይኑን ከመባረክ ከመዳሰስ በቀር። ይህም ጲላጦስ "በክርስቶስ ሞት አልተባበርኩም ከደሙ ንጹሕ ነኝ" ብሎ በአደባባይ እንደመሰከረውና እጁን እንዲታጠብ ካህኑም ንስሐ ሳይገቡ ከበደላቸው ሳይነጹ ለሚቀርቡ እርሱ በደማቸው የማይገባ፤ ለራሳቸው ተጠያቂዎች መሆናቸውን ለመግለጥ ነው።

ይኸንንም ካህኑ የተናገረውን በመስማት ያፈዘ የሣቀ ዋዛ ፈዛዛ የተነጋገረ ቢኖር ጌታን እንዳሳዘነ እጁንም በእርሱ ላይ እንዳነሳ በቡራኬም ፈንታ መርገምን፣ በኃጢአት ሥርዓት ፈንታ ገሃነመ እሳትን እንደሚወርስ ዲያቆኑ ገልጦ ያውጃል።

ጸሎተ አምኃ ቅድሳት

ጸሎተ አምኃ ቅድሳት ማለት ከይሁዳ በተለየ ሰላምታ ሰላም እንድንባባልና እጅ እንድንነሣሣ ካህኑ የሚጸልየው የሰላምታና የመሳሳም ጸሎት ነው። ይህ ጸሎት የጸሎተ አኮቴት ወይም የትምህርተ ቅዳሴ መደምደሚያ ነው።

ይ.ዲ፡- "ተንሥኡ ለጸሎት"

ይሕ፡- "እግዚኦ ተሣሃለነ"

ይ.ካ፡- "ሰላም ለኩልክሙ"

ይ.ሕ፡- "ምስለ መንፈስከ"

ይ.ካ፡- እግዚአብሔር ዐቢይ ዘለዓለም... የሚለውን ይጸልያል

ካህኑ፡- “ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ“ በማለት ሲቀድስ ሕዝቡም በእርሱ እየተመራ አብሮ ይቀድሳል። ይኸን ቅዳሴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሰሙት መላእክት ናቸው። (ሉቃስ 2፡14)

ይ.ዲ፡- “ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት ወፍቅር ተአምኑ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድስትሂ ዲያቆኑ በፍጹም ፍቅር በፍጹም ሰላም ሰላም ተባባሉ“ ብሎ ያዝዛል። በዚህም ጊዜ የፍቅር ሰላምታና እጅ መንካት ይደረጋልሂ ይህም የሁለተኛው ክፍል ቅዳሴ ፍጻሜ ነው። ይኸም ሥርዓተ ቅዳሴ ተብሎ በአጠቃላይ የተጠራው ነው።

ፍሬ ቅዳሴ

ፍሬ ቅዳሴ ማለት ዋናው የሥጋ ወደሙ መለወጫ ጸሎትና ቡራኬ ያለበት ቅዳሴ ማለት ነውሂ ፍሬ ቅዳሴ ሦስተኛዉ ክፍለ ቅዳሴ ነው።

አኮቴት ቁርባን፣ (የቁርባን ምስጋና)

“አኮቴተ ቁርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት“ እያንዳንዱ ቅዳሴ በዚህ መልክ ሲጀምር ይገኛል። ትርጉሙም የቁርባን ምስጋና (አናፎራ) ማለት ነው። ይኸው 3ኛ ክፍል ቅዳሴሂ ፍሬ ቅዳሴ በመባል ይታወቃልሂ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ይዘነው የመጣነው ክፍል የሥርዐተ ቅዳሴ ክፍል ነውና። በፍሬ ቅዳሴ ውስጥ ያሉት የተለያዩ ክፍሎች ቅዳሴ ሐዋርያትን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ይገለጻሉ።

ሀ. ጸሎተ አስተብቁዖት

ጸሎተ አስተብቁዖት ማለት የምልጃ ጸሎት ማለት ነው። የምልጃ ጸሎት የሚቀርበው ፍሬ ቅዳሴው ሲጀመር ነው።

ይ.ዲ፡- “በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ ... “ በዚህ የምልጃ ጸሎት አሁን በቤተ ክርስቲያን ከሚገኙት አባቶች ጀምሮ እስከ 4ቱ ወንጌላውያንን፣ 12 ሐዋርያት፣ 72 አርድእት፣ ስለሌሎች ቀሳውስትና ዲያቆናት ስትል “ማረን፣ ተማለደን“ በማለት ምልጃ ያደርጋል። ይህንንም የምልጃ ጸሎት ዲያቆኑ በዜማ በምንባብም ያሰማዋል። ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን የሠሩትን አባቶች ሁሉ በጸሎት ያስታውሳል።

ለ. ጸሎተ ቡራኬ

ጸሎተ ቡራኬ ማለት የቡራኬ ጸሎት ማለት ነው ንፋቁ ካህን “ኦ ሥሉስ ቅዱስ“ የሚለውን የቡራኬ ጸሎት ይጸልያል። በዚህም ጊዜ ሠራኢው ካህን በሕዝቡ ላይ ቡራኬ ያደርጋልሂ አየሩ፣ ሰማዩ፣ ምድሩ፣ ዝናሙ፣ የምድሩም ፍሬ ሁሉ የተባረከ፣ የተስማማ ይሆን ዘንድ ሁሉን ይባርካል። የሕዝቡም ቡራኬ በመስቀል ሳይሆን በእጅ ነው የሚባረከው መባዕ ስላመጡ፣ ስጦታ ስለሰጡ ምእመናን በግል ስም ጠርተው፣ በማኅበርም ይጸለይላቸዋልሂ ቡራኬም ይሰጣቸዋል። አሁንም አጠቃላይ ቡራኬ ይሰጣል። ለሞቱትም “አዕርፍ ነፍሶሙ“ በማለት ይጸልያል ዲያቆኑ (ንፋቁ) “መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት...“ በማለት ይጸልያል።

ዲያቆኑ “የተቀመጣችሁ ተነሡ፣ ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ፣ እናስተውል“ እያለ ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ ምዕመኑ ሌላ ትርፍ ሃሳብ እንዳይመጣበት ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ ያስጠነቅቃል።

ዲያቆኑ፡- "አውሥኡ፤ ተሰጥዎን መልሱ" ብሎ

ሕዝቡን በማከታተል ያዝዛል በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በአንድ ድምፅ ሆኖ "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍፁም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ" እያለ ይቀድሳል። ይኸን የምስጋና ቃል አስቀድመው ካህናተ ሰማይ መላእክት ተናግረውታል። በዚህም ቃል ሲያመሰግኑ በራእዩ አይቶ የፃፈው ነቢዩ ኢሳይያስ ነው። (ኢሳ 6፡3) ሕዝቡ እንደገና እንዲህ ሲል ይቅርታና ምህረትን ከእግዚአብሔር ይለምናል "ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግስትከ..."

ዲያቆኑ "አን/ሥኡ እደዊከሙ ቀሳውስት" በማለት ካህኑ ኅብስቱን፣ ንፍቁ ካህን ማኅፈዱን ከጻሕሉ ላይ እንዲያነሡ ያሳስባል።

ሐ. <u>ውላጤ ኅብስት ወወይን</u>

ይ.ካ፡- "ይእዜኒ እግዚእ ንዜከር ሞተከ" የሚለውን የምልጃ ጸሎት ካህኑ እየጸለየ "ዛሬም እንደዕለተ ዓርብ ይኸ ኅብስት ሥጋህ ይሁንልን ይኸም ፅዋዕ ደምህን ይሁንልን ስለዚህም ይኸን ኅብስት ባርክ አክብር ይኸንም ፅዋዕ ባርክ" እያለ ወደ ኅብስቱም ወደ ፅዋውም በእጁ እያመለከተ "ይረስዮ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ዓለም" ብሎ ይባርካል። በዚህም ምልጃ በዚህም ጸሎት "ልክ እንደዚያን ጊዜው ሥጋህና ደምህን አድርግ" ብሎ ሲባርከው ውላጤ ኅብስቱ ወይን ይሆናል።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ "የክርስቶስ ሥጋና ደም" እየተባለ እንጅ "ኅብስትና ወይን" እየተባለ አይጠራም። ዲያቆኑ ወደ ምዕራብ በር ሄዶ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ "በኩሉ ልብ ናስተብቁዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ" ብሎ ያዝዛል።

ሕዝቡም "በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልድ ትውልድ ለዓለም ዓለም" ይላል። "ደሚረከ ተሃቦሙ ..." የሚለውን ካህኑ ይጸልያል፤ አያይዞም "ህበነ ንኅበር በዘዘኢከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርስፎራ ከመ ብከ ንሕየው ዘለኩሉ ዓለም ወለዓለም ዓለም" ይላል።

ይኸንኑ ሕዝቡ ከካህን ተቀብሎ እንደገና ይጸልያል ካህኑ በመቀጠል "ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር..." ይላል። ይኸንም ሕዝቡ ተቀብሎ ያመሰግናል። ካህኑ እንደገና ፈኑ "ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ" ይላል ሕዝቡም ይኸንኑ ተቀብሎ ይጸልያል።

መ. <u>ጸሎተ ፈትቶ</u>

ጸሎተ ፈትቶ ማለት ካህኑ ሥጋውን እየፈተተ የሚጸልየው ጸሎት ማለት ነው።

ይ.ዲ፡- "ጸልዩ" (ዲያቆኑ ወደ ሕዝቡ ብቅ ብሎ ጸልዩ ብሎ ጸሎት ያዝዛል።)

ይ.ሕ፡- "አቡነ ዘበሰማያት..." በማለት ጌታ ያስተማረውን ጸሎት በዜማ ወይም በንባብ ይጸልያል

ይ.ሕ፡- "በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ" የሚለውን ይጸልያል አያይዞም በተባርዮ "ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔዓለም ዬ ዬ ዬ ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔዓለም። ወይኬልዎ ለመድኃኔዓለም ዬ ዬ ዬ ሥጋሁ ወደሙ ለመድኃኒዓለም። ወንብጸሕ ቅድመ ገጹ ለመድኃኒዓለም ዬ ዬ ዬ በአሚነ ዚአሁ ለክርስቶስ ንገኒ (ሐዋርያት ተለው ዓሠሮ) ይህን ሠራዊት የሚሉት ሠራኢ ካህን፣ ሠራኢ ዲያቆን ሦስተኛ ዲያቆን በውስጥ በመቅደስ፣ ንፍቅ ካህንና ንፍቅ ዲያቆን በውጭ በቅድስት ሆነው እየተቀባበሉ ነው።

ይ.ዲ፡- ንፋቅ አርጎው ኖኃተ መኳንንት ይላል።

በዚህ ጊዜ በውስጥ ያሉት መጋረጃውን ይገልጣሉ። ጌታ በአደባባይ የመሰቀሉ ምሳሌ ነው።

ይ.ዲ፡- "እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእስክሙ" ዲያቆኑ "የቆማችሁ ሁሉ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" ሲል ወደ ሕዝቡ ብቅ ብሎ ያውጃል፤ ሁሉም በአጽንኖ ሆኖ ጸሎቱን ይሰማል።

"ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት" ሲል ዲያቆኑ ፊቱን ወደ ምዕራብ አድርጎ ያውጃል ይኸውም የንሰሐ ጸሎት የሚጸለይ ነውና ሕዝቡ "ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ" ሲል ለእግዚአብሔር መስገድ እርሱንም ማመስገን ተገቢ መሆኑን አምኖ እየተናገረ ይሰግዳል።

ሠ. <u>ጸሎተ ንሰሐ</u>

ጸሎተ ንሰሐ ማለት ንሰሐ የገቡ ሰዎች ሥርየተ ኃጢአት እንዲያገኙ ካህኑ የሚጸልየው ጸሎት ነው። በዚህ ጊዜ ሁሉም ወድቆ የኃጢአቱን ሥርየት ይለምናል የአምላክን ይቅርታ ደጅ ይጠራል። ካህኑም የንሰሐ ጸሎትን ይጸልያል።

ይ.ዲ፡- "ነጽር" ዲያቆኑ አስተውል ብሎ ቄሱን ያሳስበዋል ቄሱ "ቅድሳት ለቅድሳን" ይኸ ቅዱስ ሥጋና ደም ለተቀደሱት ምእመናን ነው ብሎ ያውጃል ሕዝቡ ደግሞ "አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ይላል።

ይ.ካ፡- "እግዚአብሔር ምስለ ኩልክሙ" ይላል

ይ.ሕ፡- "ምስለ መንፈስከ" ይላሉ

በዚህ ጊዜ ካህኑ ሥጋውን አንሥቶ በሁለት እጆቹ ይዞ "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" ይላል፤ ሕዝቡም እርሱን ተከትሎ "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ፣ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" ሲል ሥጋውን ከጻሕሉ ላይ ወደ ላይ ማንሣቱ የጌታ ዕርገት ምሳሌ ነው።

ረ. <u>2ኛ ጸሎተ ንሰሐ</u>

ዲያቆኑ "እለ ውስተ ንሰሐ ሀለውክሙ አትሐቱ ርእስክሙ" ሲል ያውጃል፤ ካህኑም "እግዚአብሔር አምላክነ ነጽር ዲበ ሕዝብከ" የሚለውን ይጸልይላቸዋል

ሰ. <u>ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ የሃይማኖት ምስክርነት</u>

ይ.ዲ፡- "ተንሥኡ ለጸሎት" (በንባቡ)

ይ.ሕ፡- "እግዚኦ ተሣሃለነ"

ይ.ካ፡- "ሰላም ለኩልክሙ"

ይ.ሕ፡- "ምስለ መንፈስከ"

ይ.ካ፡- "ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን..." ከሚለው ጀምሮ ካህኑ መታመን የሚገልጹ ምንባባትን ያስባልል፤ ሕዝቡም "አሜን" በማለት እምነቱን ይገልጻል፣

ቀ. <u>ለቁርባን መዘጋጀት</u>

ከዚህ በኋላ የሚቆርበው ወገን ሁሉ ይዘጋጃል እያንዳንዱም ከመቁረቡ በፊት ካህኑ ይኸን የሚከተለውን ይጸልያል።

"እግዚአብሔር አምላክየ ናሁ ሥጋ ወልድከ ..." የሚለውን ይጸልያል። ሕዝቡ ደግሞ "ኦ እግዚእየ ኢየሱስ" የሚለውን ይጸልያል።

ከዚህ በኋላ ካህኑ ይቆርባል ቀጥሎም ለረዳቱ ካህን ይሰጣል ረዳቱ ካህን ደግሞ ደሙን ይሰጠዋል ካህኑም ጽዋውን መልሶ ለረዳቱ ካህን ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ 1ኛ ስለ መለኮትና ሥጋ ተዋሕዶ የሚገኝ የአባቶች ምስክርነት (ሃይማኖተ አበው) 2ኛ ምሥጢር ቁርባንን የሚመለከቱ ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን የሚገልጡ ምንባቦች ይነበባሉ። ከዚህም ቀጥሎ ስለ ሥጋውና ደሙ ክብር ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተዘጋጀ መልክዐ ቁርባን የተባለ የሚዘመር አለ።

ቦ. <u>መልክዐ ቁርባን</u>

መልክዐ ቁርባን ማለት በቁርባን ጊዜ የሚጸለይ እንደ ቅዱሳን የመልክ ጸሎት 5 /አምስት/ ቤት እየገጠሙ የተደረሰ ጸሎት ነው። ቁርባኑን ከመቀበል አስቀድሞ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉ ሁሉ እንዲህ ይላሉ "አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ርኩሰት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለሁም። እኔ አሳዝኜሃለሁና በዚህም ክፋ ሥራን ሠርቻለሁና በአርአያህና በምሳሌህ የፈጠርከውን ሥጋዬንና ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌአለሁና ምንም ምግባር የለኝም ነገር ግን ስለመፈጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለመሆን፣ ስለ ክቡር መስቀልም ማሕየዊት ስለምትሆን ሰላምታህ በሦስተኛ ቀን ስለመነሣትህም ጌታዬ ሆይ ከበደልና ከመርገምም ሁሉ ከኃጢአትም ከርኩሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፤ እማልድሀለሁ።

የቅድስናህን ምሥጢር በተቀበልህበት ጊዜ ለወቀሳ ለመፈራረጃ አይሁንብኝ ማረኝ ይቅርም በለኝ እንጂ የዓለም ሕይወት ሆይ በእርሱ የኃጢአቴን ሥርየት የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም፣ በመጥምቁ በዮሐንስም አማላጅነት ክቡራን በሚሆኑ መላእክትም በሰማዕታትና ለበጎ ነገር በሚጋደሉ በዓድቃን ሁሉ ጸሎት እስከ ዘለዓለሙ አሜን"

እንዲሁም ቆራቢው "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ዘኢይትነገር ሀበኒ ...." የሚለውን ጸሎት ሥጋ ወደሙ ከመቀበሉ በፊት ይጸልያል፡

ተ. <u>ድርገት</u>

ድርገት ማለት አንድነት ማለት ነው። ድርገት ወረደ ማለት በአንድነት ሆነው ሥጋውንና ደሙን ይዘው ወደ ሕዝቡ ወጡ ማለት ነው። በመቅደስ ያሉት ቀዳሾችም በአንድነት ሆነው ወደ ውጭ ወደ ምእመናኑ ይወጣሉ በዚህ ጊዜ ድርገት ወረዱ ይባላል። ይኸም በአንድነት ወጡ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የዳዊት 150 ኛው መዝሙር እንዲዘመር ያዛል። እንዲሁም "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ሥሉስ ዘኢይትነገር..." የሚለውን ቆራቢዎች ይዘምራሉ።

አ. <u>አኮቴተ ቅድሳት</u>

አኮቴተ ቅድሳት ማለት የተለየ ምስጋና ማለት ነው። አምላክ የምሥጢር ተካፋዮች፣ የሥጋውና የደሙ ተቀባዮች ስላደረገን የተለየ ምስጋና ይቀርብበታል፤ ይኸም የተለየ ምስጋና የተባለው የሚቀጥለው ነው።

ዲያቆኑ "ነአኩቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውሰ ዘተመጠነ ንስእል ወንትመሐጸን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላክነ" እያለ በቅድስቱ አንድ ጊዜ ይዞራል። ካህኑ ደግሞ "ስብሐት ለእግዚአብሔር..." ይላል ሕዝቡም "አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት" ይላል እንደገናም ዲያቆኑ "ተመጠነ እምሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ" ይላል፤ ካህኑም ያንኑ ቃል "ስብሐተ እግዚአብሔር..."

የሚለውን ደግሞ ይናገረዋል ሕዝቡም ያንኑ "አቡነ ዘበሰማያት..." ይላል ዲያቆኑ እንደገና "ወናእኩቶ ይደልወነ ከመ ንሳተፍ ምሥጢረ ክብርተ ወቅድስተ" ይላል።

ከ. <u>ሐዳፌ ነፍስ</u>

ሐዳፌ ነፍስ ማለት ነፍስን የሚያሻግር ማለት ነው። ይህ ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ሲወርድ በአካለ ነፍስ ወደ ሲዖል ወርዶ ነፍሳትን ነፃ ማውጣቱን የሚያመለክት ጸሎት ነው። ስለዚህም ሐዳፌ ነፍስ ተብሎአል።

ይ.ካ፡- "ወካዕበ ናስተበቁዕ...."የሚለውን ካህኑ ወደ ምሥራቅ ይጸልያል።

ይኸም ጸሎት እንደተፈጸመ የቁርባኑ ሥርዓት ተፈጸመ ድርጊት የወጡት ሁሉ በአንድነት ይመለሳሉ፤ ወደ መቅደሱም ይገባሉ። ሐዳፌ ነፍሱ ጸልዮት ከአለው "ጸልዩ" እስከሚል ያለው ጸሎት ወደ ምዕራብ ይባልና "ጸልዩ" ካለ በኋላ ወደ ምሥራቅ ይመለሳል። ይህም ነፍሳት በሲዖል 5 ሺህ 500 ዘመን ከቆዩ በኋላ በክርስቶስ መስቀልና በአፈሰሰው ደሙ ከሲዖል ወደ ገነት የመመለሳቸው ምሳሌ ነው፣ ሲኦል በምዕራብ፣ ገነት በምሥራቅ ናቸውና።

ወ. <u>አንብሮ እድ</u>

ሂንብሮ እድ ማለት ካህኑ በታቦቱ ላይ እጁን አስቀምጦ የሚጸልየው ጸሎትና ቡራኬ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕርገቱ ጊዜ በአንከሮተ ዕድ ሐዋርያትን ባርኮአቸው የማረጉ ምሳሌ ነው።

ይ.ካ "እግዚአብሔር ዘለዓለም ብርሃነ ሕይወት..." የሚለውን ካህኑ ይጸልያል። አንብሮ እድ ያለበት ምክንያት ሁሉን ከፈጸመ በኋላ እጁን በታቦቱ ላይ ጭኖ የሚጸልየው ጸሎት ስለሆነ ነው። ይህም ጌታ በዕርገቱ ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ ባርኮ የማረጉ ምሳሌ ነው። ተራዳኢ ካህኑ ደግሞ "ወዕቀቦሙ በርትዕት ሃይማኖት" የሚለውን የቡራኬ ጸሎት ይጸልያል።

ይ.ሕ "ኦ ንጉሠ ሰላም ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመከ ህበነ ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ" የሚለውን ይጸልያሉ።

<u>ሠርሆተ ሕዝብ</u>

ሠርሆተ ሕዝብ ማለት ሕዝቡን ማሰናበት ማለት ነው ካህኑ የማሰናበቻውን ቡራኬና ጸሎት ከአደረገ በኋላ ዲያቆኑ "እትው በሰላም በሰላም ወደ ቤታችሁ ተመለሱ" ብሎ የሚያሰናብታቸው ስለሆነ "ሠርሆተ ሕዝብ" ይባላል።

ይ.ዲ "አድንኑ አርእስቲከሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርከሙ" ይላል።

ሕዝቡም "በእደ ገብሩ ካህን አሜን ይባርከነ" ይላል በዚህ ጊዜ ካህኑ በመጾር መስቀሉ 3 ጊዜ "ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝብከ ወባርክ ርስትከ" እያለ ሕዝቡን ይባርካል

ይኸን ጸሎት እንደፈጸመ በእጁ ሁሉንም እየባረከ ያሰናብታል፤ ይኸም ጌታ በአረገ ጊዜ ሐዋርያትን በአንብሮተ ዕድ ባርኮ የመሔዱ ምሳሌ ነው ሉቃ (24) ቀሳውስት እጅ ለእጅ እየተያያዙ ይሳለማሉ። ሕዝቡን ግን በእጁ ፊታቸውን ይባርካል።

ይ.ካ "እግዚአብሔር ምስለ ኩልከሙ"

ይ.ሕ "ምስለ መንፈስከ"

"አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ . . . " ይላል

ይ.ዲ "እትው በሰላም" ይላል

በሰላም በጤንነት ወደ ቤታችሁ ግቡ ብሎ ዲያቆኑ ያሰናብታል። የቅዳሴ ሥርዓት በዚህ መልክ ይፈጸማል ሁሉም በሰላም ወደየቤቱ ይሄዳል።

<u>ማጠቃለያ ሥለ ሥርዓተ ቅዳሴ</u>

1. ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት አብሮት የሚቀድሱ ዲያቆን መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፣
2. ካህኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ በታቦቱ ፊት ከመጋረጃ ውጪ አንድ ጊዜ በመጋረጃ ውስጥ በመሠዊያው ፊት ሦስት ጊዜ ይሰግዳል (ሕዝ 46፥3)
3. ካህን በክብር በፍርሃት ሆኖ "ተንሥኡ ጸልዩ" እያለ ሕዝቡን የሚሰብክለት ዐዋጅ የሚናገርለት ዲያቆን ሳይዝ እንዳይቀድስ ተከልክሏል። ዲያቆኑም አሰምቶ የሚያነብና የሚያዜም ሊሆን ይገባል።
4. ሕዝቡ እንዳይፈዙ፣ እንዳያንቀላፉ ዲያቆኑ ያነቃቃቸዋል (ፍት.መን.አን 12፣ ጽልቅ 12)
5. ካህኑ ቅዳሴ ሲገባ ከሁሉ በፊት አንድ ጊዜ በታቦቱ ፊት ሰግዶ አንድ ጊዜ ቀሳውስቱን አንድ ጊዜ ዲያቆናቱን እጀ ይነሣል።
6. ዲያቆን በቤተልሔም ጎብስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት ከሠራና ካዘጋጀ በኋላ ንፍቁ ዲያቆን ጎብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ላይ አድርጎ ወይኑን ሠራዒው ዲያቆን በጽዋዕ ይዞ ቃጭል እየቃጨለ በፊት በፊቱ ንፋቁ ቄስ መስቀልና ማዕጠንተ ይዞ እያጠነ በኃላ በኃላው፣ ሁኖ ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ይገባሉ (ፍት.መን 12፣ ረስጠብ 92)
7. ቅዳሴ ሲገቡ ቀዳሲያን መንበሩን ከብበው ይቆማሉ ሠራዒ ካህን ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ በምዕራብ ይቆማል፤ ሠራዒ ዲያቆን ፊቱን ወደ ምዕራብ አድርጎ በምሥራቅ ይቆማል፤ ንፋቅ ካህን ፊቱን ወደ ሰሜን አድርጎ በደቡብ ይቆማል፤ ንፋቅ ዲያቆን ፊቱን ወደ ደቡብ አድርጎ በሰሜን ይቆማል፤ ሦስተኛው ቄስ በስተግራ ቆሞ ለሠራዒው ካህን መብራት ያበራለታል፤ መጽሐፍ ይገልጥለታል። ሦስተኛ ሆኖ የሚገባ ቄስ ባይኖር ዲያቆን መብራት ያብራል መጽሐፍ ይገልጣል ይህን ሲሠራ ግን ዲያቆን መንበሩን እንዳይጠጋና እንዳይዳስስ መጠንቀቅ ይገባል።
8. ዲያቆናት በዐውደ መንበሩ ቆመው ተሰጦውን ይቀበላሉ፤ በተለይ 2 ዲያቆናት ከልዝብ ሐር የተሠራ መነሳንስ ይዘው አንዱ በቀኝ፣ አንዱ በግራ ቆመው ወደ ጽዋው ምንም ምን እንዳይገባ ተሐዋስያንን ይከለክላሉ (ፍት.መን.ኢን. 12፣ ረሰጣ 52)
9. በቤተ ክርስቲያን የተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ የእግዚአብሔርን ነገር (ትምህርቱን ጸሎቱን) ለመስማት በጸጥታ መቀም አለባቸው። ተሰጥዎ ከመቀበል በቀር መናገር መሳቅ አይገባቸውም በቅዳሴ ጊዜ ፈጽሞ የሚስቅ አይኑር (ፍት.መን.ኢን 12፣ ጽስቅ 12፣ ኒቅያ 61፣ በሰ 72)
10. ወንጌል ሲነበብ መቆም ነው እንጂ መቀመጥ ክልክል ነው።
11. ወንጌል ሲሰለሙም "ነአምን በቃለ ወንጌል ቅዱስ" እያሉ ነው
12. ወንጌል ከተነበበ በኃላ ኤጲስ ቆጶስ ከሌለ ወንጌሉን በእጁ ይዞ በክፍሎቹ የተነበበውን ለሕዝቡ ተርጉሞ መንገር ይገባዋል፤ ኤጲስ ቆጶሱ ከሌለ ትርጓሜውን የሚችል ካህን እንዲያስተምር ታዝዋል። (ፍት.መን 19፣ በደስ 99)
13. ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ወንጌልን ከማንበቡ በፊት ንፋቅ ቄስ "ርኁቀ መዓት" የሚለውን ጸሎት ይጸልያል።

14. ካህኑ በሥርዓተ ቅዳሴ መጀመሪያና በፍሬ ቅዳሴ መጀመሪያ ሁለት ጊዜ እጅን ይታጠባል። እንዲሁም ሌሎች ካህናትና ዲያቆናት ከቁርባን አስቀድሞ እጃቸውን ይታጠቡ።
15. በቅዳሴ ጊዜ በ 2 ጧፍ እንጅ በአንድ ጧፍ አይቀድስም
16. በቅዳሴ ጊዜ ዕርገት ዕጣን አይቀርም የሚደረገውም ዕርገተ ዕጣን አምስት ጊዜ ነው (አብጥሊስ 3)
17. ማጠንቱን /ጥና/ የሚይዝና የሚያጥን ቄስ ነው እንጅ ዲያቆን በእጁ ይዞ አያጥንም ኤጲስ ቆጶስ መሥዋዕቱን ከአጠነ በኃላ ሕዝቡንና ካህናቱን፣ ቤተ ክርስቲያኑን እየዞረ እንዲያጥን ጥናን ለቄስ ይሰጣል (ድስቅ 12፣ 23፣ 38)
18. የቅዳሴ ቡራኬያት 42 ናቸው። እነዚህም 21 የአፍአ 21 የውስጥ ቡራኬያት ናቸው፤ የአፍአ ቡራኬ ለካህናትና ለሕዝብ ነው፤ የውስጥ ቡራኬ ግን በሥጋ ወደሙ ላይ ነው፤ የአፍኦ ቡራኬ በመስቀል ነው፤ የውስጥ ቡራኬ ግን ካህኑ በእጁ በሥጋውና በደሙ ይባርካል፤ ንፋቅ ካህን ግን አይባርክም ሠራዒው ካህን ሥጋ ወደሙን በእጅ እንጂ በመስቀል አይባርክም ጽዋውንም ሲባርክ የጽዋውን ከንፈር በግራ እጅ መያዝ አይገባውም። በቀኝ እጁ በትእምርተ መስቀል አምሳል መወዝወዝ አለበት።
19. በቅዳሴ ጊዜ የሠራዒው ካህን ዑደት ሰባት ነው ይኸውም በመጀመሪያው ጸሎተ ዕጣን በመቅደሱ ውስጥ 3፣ በአንቀጸ ምዕራብ "ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ" እያለ አጥኖ ከፈጸመ በኋላ "እግዚአብሔር አምላክነ በከመ እንህልከ ቅድመ ጥቅማ ለኢያሪኮ" እያለ ሲዞር አንድ፣ በ 2 ኛው ጸሎተ ዕጣን 3፣ በድምሩ 7 ዑደት ይሆናል።
20. የንፋቅ ካህን ዑደት ሦስት ነው። ግብረ ሐዋርያት አንብቦ ሲገባ 1 "ወንጌል " ተነብቦ ሲገባ 1 ጊዜ "ሠራዊተ መላእክቲሁ" ተብሎ ሲገባ አንድ ጊዜ ይዞራል በድምሩ 3 ይሆናል።
21. እማሬያት 11 ናቸው። እነዚህም በጸሎተ ዕንፎራ 2፣ "አዕኩተ " ሲል በሥጋው አንድ በደሙ 1፣ "ይረስዮ " ሲል 2፣ "ሥጋ ቅዱስ" ሲል አንድ፣ "ደም ክቡር" ሲል 1፣ "እስመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ" ሲል 1፣ በመጀመሪያው "አአምን " 1፣ በመጨረሻው "አአምን " 1 ሲደመር 11 ይሆናል።
22. ጸሎተ ቅዳሴ ከተጀመረ በኃላ ዲያቆን "ዕትው በሰላም" ብሎ ሳያሰናብት በከባድ ችግርና በሕመም ከአልሆነ በቀር ከቤተ ክርስቲያን መውጣት ክልክል ነው (ፍት.መን.አን.12፣ በስ 92)
23. ዲያቆን "ጸልዩ በእንተ ሰላም" ብሎ ስለ ሰላም እንዲጸልዩ በቅዳሴ ጊዜ ትእዛዝ ሲሰጥ ወንዶች ወንዶችን፣ ሴቶች ሴቶችን ሁሉም በየጸሎታቸው እጅ ይነሣሣሉ፤ ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ወንዶችን እጅ አይነሡም (ፍት.መን.12፣ ረሰጣ 103፡32፣ 53)
24. ካህኑ ጎብስቱን ሲፈትት ከላይ ወደ ታች፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከታች ወደ ላይ በትክክል መስቀሉን ተከትሎ ይፈትተዋል። ሲፈትትም እንዳይነጥበው መጠንቀቅ አለበት (ፍት.መን. 12፣ በስ 99)

9.ማጣቀሻ መጻህፍት/ References/

1. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ
2. ኖኅተ ሰማይ፣ቀሲስ ያሬድ ገብረ መድህን፣ 1996 ዓ.ም
3. 14 ቱ ሥርዓተ ቅዳሴ መጽሐፍ

4. 81 አዱ መጽሐፍ ቅዱስ
5. የመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊዮርጊስ/ሰ/ት/ቤት መማርያ መጽሐፍ